USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Ministry of Education

ሪድ-II የተማሪዎች ውጤታማነት እና ድጋፍ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት (Toolkit)

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Ministry of Education

ሪድ-|| የተማሪዎች ውጤታማነት እና ድጋፍ የትግበራ መሣሪያዎች/ስልቶች ቋት

ኢትዮጵያ

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስአበባ

ስምምነት

ይህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት እውን የሚሆነው በአሜሪካ ህዝብ ድጋፍ በዩናይትድ ስቴትስ ዓለምአቀፍ የልማትድርጅት (USAID) አማካይነትነው:: የትግበራ መሳሪያዎቹ/ስልቶቹ ቋት ይዘቶች ብቸኛ ኃላፊነት የክሪኤቲቭ አሶሽትስ ኢንተርናሽናል እና ተባባሪ ድርጅቶቹ (Creative Associates International and its consortium) ሲሆኑ ይዘቶቹ የአሜሪካ መንግስትን አመለካከትና አቋም አያንፀባርቁም::

የሪድ-II ፕሮጀክት

የሪድ-II ፕሮጀክት አጠቃላይ ዓላማው ኢትዮጵያ የ15 ሚሊዮን ተማሪዎችን የንባብ ችሎታ እና የመማር ውጤት እስከ 2014 ዓ.ም ለማሻሻል የጣለችውን/ያስቀመጠችውን ግብ በዩናይትድ ስቴትስ ዓለምአቀፍ የልማትድርጅት አማካይነት እንዲሳካ አስተዋፅኦ ለማድረግነው። ፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራባቸው ስድስት ክልሎች አዲስአበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብህዝቦች እና ትግራይ ሲሆኑ በፕሮጀክቱ ውጤት ህብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤውን ያሻሽላል በሂደትም በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የላቀ ተሳትፎ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

ሪድ-II ፕሮጀክት ተግባራዊ የሚደረገው በክሬኤቲቭ አሶሽትስ ኢንተርናሽናል እና ተባባሪ ድርጅቶቹ በሆኑት EDC፣ WVI፣ IRC፣ Viamo እና The BlueTree Group አማካይነት ነው።

ምሥጋና

ይህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት የተዘጋጀው በአሜሪካ ህዝብ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን ዝግጅቱን ያከናወነው የሪድ-II ፕሮጀክት ከትምህርት ሚኒስቴር (MoE)፣ ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር ነው።

የሪድ-II ፕሮጀክት ሰራተኞች የተማሪዎች ውጤታማነትና ድጋፍ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋትን (SSST) በማዘጋጀታቸው ድርጅቱ ጥልቀት ያለው አድናቆቱን ይገልፃል። በተጨማሪም በዳሰሳ ጥናቱ ለተሳተፉ ትምህርት ቤቶች፣ መረጃ ለሰጡ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ለትምህርት ቤትርዕሰ-መምህራን፣ ለመምህራን፣ ለወላጆች እና ለተማሪዎች ምስጋና እናቀርባለን። እንዲሁም ደግሞ ለሪድ-II የክልል ዳይሬክተሮች፣ የቅድሚያ ትኩረት መርሀ ግብር አስተባባሪዎች (Cross-Cutting Coordinators) እና ሌሎች የተለያዩ የትምህርት ሚኒስቴር ዳይሬክቶሬቶች ልዩ ምስጋና ይገባቸዋል።

በትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ዝግጅቱን በመገምገም የተሳተፉ የፌደራል እና የክልል ባለሙያዎች

ያሳቡ ብርቅነህ	ት/ሚር
ፀሀይ ምስግና	ት/ሚር
ሳሙኤል አሳምነው	ት/ሚር
ጌታሁን ሀይለሚካኤል	ት/ሚር
ግርማ ደምሴ	ት/ሚር
ሞገስ ደርበው	ዩኒሴፍ የትምህርት ጥምረት - UNICEF-Education Cluster
ዳንኤል ዳርቺ	ከስደተኞችና ተመላሾች አስተዳደር ጉዳይ - ARRA
አስቻለው አድራሮ	አ/አ ት/ቢሮ
አበባ ዘውዴ	አ/አ ት/ቢሮ
በትግሉ ግዛው	አ/አ ት/ቢሮ
ጌታቸው ታለማ	አ/አ ት/ቢሮ
አምላኩ ተበጄ	አ/አ ት/ቢሮ
አንዱአለም ጤናው	አማራ ት/ቢሮ
ስንታየሁ እምሩ	አማራ ት/ቢሮ
ፈንታሁን ፀጋ	አማራ ት/ቢሮ
አዳሙ ገብረሀይዎት	አማራ ት/ቢሮ
ጀማል ሙፍቲ	ኦሮሚያ ት/ቢሮ
ገመዳ ኢፋ	ኦሮሚያ ት/ቢሮ
አምሳሉ ደበሎ	ኦሮሚያ ት/ቢሮ
ሀብታሙ ቶማስ	ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ት/ቢሮ
ተስፋየ ፈንታሁን	ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ት/ቢሮ
ሙሉአለም መኮንን	ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ት/ቢሮ

ሙሉ ዋቅቶላ	ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ት/ቢሮ
ፋድህ አብዱላሂ	ሶማሌ ክልል ት/ቢሮ
አህመድኑር የሱፍ	ሶማሌ ክልል ት/ቢሮ
ተክሉ እቸር	ትግራይ ክልል ት/ቢሮ
አለምአፅብሐ	ትግራይ ክልል ት/ቢሮ
ሙሉጌታ ግደይ	ትግራይ ክልል ት/ቢሮ
ስላስ አርአያ	ትግራይ ክልል ት/ቢሮ
ብርሀን ገብረማርያም	ትግራይ ክልል ት/ቢሮ

የሪድ-II ፕሮጀክት ሰራተኞች

ካሳዬ ይመር

ብሪጄት ሎምባርዶ

ጆኒ ኮኸን

ሜጋን ሰቹግ

ሊንድሰይ ሾርት

ሊሳ ድዮ

ጃነት ሺሪበርግ

ስንዱ ፈቃዱ

የልፍኝ አዬነው

ሙሉብርሀን አበራ

በላይነህ ወልደማርያም

አብዲራዛቅ አሊ

ብሩክ ተሰማ

አስቴር ምንውዬለት

እድሪስ ዮዋና

ሳዲቅ ሀሰን

አቢይ አዲሱ

መቅድም

የተማሪዎች ማቋረጥ የትምህርት ሥርዓቱን በአለም አቀፍ ደረጃ እየጎዳ ያለ ተግዳሮት ሲሆን ችግሩን አስቀድሞ ለመከላከል በሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተገቢ ነው። በችግር ላይ ያሉና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ በአብዛኛው ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ እንደሚችሉ ይታመናል። እነዚህ ተማሪዎች በተለያየ የዕድሜ ክልልና የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ሲሆን የጤና፣ የአዕምሮ፣ የጦርነትና የመፈናቀል ችግሮች ተጠቂ ስለሚሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች ደህንነታቸውን እንዳይጠብቁ ያደርጓቸዋል። ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች እራሳቸውን ከጉልበት ብዝበዛና ሌሎች ጎጅ ከሆኑ ነገሮች እራሳቸውን መጠበቅ የማይችሉ በመሆኑ ከትምህርት ቤቶች የተለየ እና ተጨማሪ የሆነ ድጋፍና ክትትል ያስፈልጋቸዋል። በኢትዮጵያ ሁኔታም በከተማና በገጠር በተመሳሳይ ሁኔታ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች ያሉ ሲሆን የሚደርሱባቸውን ችግሮች ተቋቁሞ መማር ስለሚከብዳቸው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ይገደዳሉ።

የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ከተለለያዩ አጋር የልማት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለችግር ተጋላጭ የሆኑና በተለያዩ የእርስበርስ ግጭትና መፈናቀል ምክንያት ትምህርታቸውን መማር ያልቻሉ ተማሪዎችን በመደገፍ ላይ ይገኛል። ድጋፉ የትምህርት ቁሳቁስ፣ የተማሪዎች የደንብ ልብስ እና የተለያዩ አልባሳትን፣ የአደጋ ጊዜ የትምህርት ቤት ምገባ እንዲሁም ጊዜያዊ የሆኑ የመማሪያ ቦታዎችን ያጠቃልላል።

ሪድ-II ባሁኑ ጊዜ የተማሪዎችን በአፍ መፍቻ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የማንበብና የመፃፍ ክህሎት ለማሻሻል ከፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር እና ከአዲስአበባ፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ህዝቦች፣ ከሶማሌና ከትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በቅርበት እየሰራ ሲሆን ፕሮጀክቱ 15 ሚሊዮን ተማሪዎችን ተደራሽ ለማድረግ ግብ ጥሏል። በተጨማሪም ሪድ-II በያዘው የቅድሚያ ትኩረት መርህ ግብር መሠረት በተለያየ ግጭት ለተፈናቀሉና በችግር ላይ ላሉ ተማሪዎች ልዩ ልዩ ድጋፎችን ያደርጋል።

ስለሆነም ይህ የተማሪዎች ውጤታማነትና ድጋፍ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ዝግጅት በተገቢው ጊዜ የተከናወነ ነው። የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋቱ ዓላማም ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ ማድረግ ሲሆን ድጋፉ በተለይም ችግር ውስጥ ያሉና ተጋላጭ በሆኑ ተማሪዎች የመማር ውጤት ማሳደግ ላይ ትኩረት ይሰጣል።

እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ለተማሪዎች የትምህርት ውጤታማነት ችግሮች ሊሆኑ የሚችሉ መሰናክሎችን ሁሉ በማወቅ ተማሪዎች ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚያስችል ድጋፍ ሳይሳቀቁ እየጠየቁ የሚማሩበትን ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠርና ተማሪዎች ያለ ምንም የኢኮኖሚ፣ የችሎታ እና የፆታ ልዩነት ከሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ነው። በዚህም መሠረት የሪድ-II ቀዳሚ ትኩረት ተማሪዎች እንዲማሩ ማድረግ ሲሆን ከትምህርት ቤቶች ጋር በጋራ እና በትብብር በመስራት የተማሪዎችን የመማር ተግዳሮቶች በመቀነስ የትምህርት ውጤታማነታቸውን ማሳደግ ስለሆነ ሁሉም ተግቶ መስራት ይጠበቅበታል።

ያሳቡ ብርቅነህ

የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም እና ድጋፍ ዳይሬክተር ጀኔራል (MoE)

የተማሪዎች ውጤታማነትና ድጋፍ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ምንድን ነው?

ይህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት የተዘጋጀው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አደጋ ላይ ያሉና ለችግር የተጋለጡ ተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላት ለሚሹ ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ በማጣቀሻነት እንዲያገለግል ነው። በእያንዳንዱ ሞጁል ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቡ የተማሪዎችን ማቋረጥ መከላከል፣ አካቶ ትምህርትን ተግባራዊ ማድረግ፣ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን መከላከል እና ሌሎች የመማር ችግሮችን መከላከል የሚያስችሉ መሣሪያዎች (tools) ተካተዋል። በስምንቱ ሞጁሎች የተካተቱት ስልቶችና ተግባራት በአደጋ ላይ ያሉ ተማሪዎችን የትምህርት ተግዳሮቶች ለመከላከል ብቻ የተነደፉ አይደሉም። ይልቁንም ስልቶቹንና ተግባራቱን በሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ ጥቅም ላይ በማዋል የመማር ውጤትን በላቀ ሁኔታ ማሻሻል የሚያስችል ልምድ እንዲዳብር ለማድረግ ነው። በዚህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት የቀረቡት ስልቶችና ተግባራት ስደተኞች በሰፈሩባቸው ቦታዎች (refugee camps) እና አካባቢያዊ በሆኑ የእርስበርስ ግጭት ምክንያት ተፈናቃይ ተማሪዎች በሚገኙባቸው መጠለያ ጣቢያዎች ጥራት ያለው ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ ተግባራዊ ይሆናሉ።

የተማሪዎች ውጤታማነትና ድጋፍ የትግበራ መሳሪያዎች ቋት ያካተታቸው ስምንት ሞጁሎች፡-

1. የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት
2. የመጀመሪያ ደረጃ ልዩታ
3. ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት
4. ለተማሪዎች ምቹና ተስማሚ አካባቢ በትምህርት ቤት መፍጠር
5. ግብረ-ገብነት እና የትምህርት ቤት ህግና ደንብ
6. የማህበራዊ ስሜት ትምህርት
7. አካቶ ትምህርት
8. የፆታ እኩልነትን ያረጋገጡ ትምህርት ቤቶች

የትግበራ መሳሪያዎች ስልት ማኑዋሉ እንዴት ተዘጋጄ?

ሪድ- II ይህን የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ሲያዘጋጅ አዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ህዝቦች እና ትግራይ ክልሎችን ትኩረት አድርጎ የተሰራውን የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት በማድረግ ነው። በዳሰሳ ጥናቱ ወላጆች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የክልልና የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ባለሙያዎች ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል። ትምህርት ቤቶች በቱል ኪቱ በስምንቱም ሞጁሎች የተካተቱትን ርዕሰ ጉዳዮች በአግባቡ ተግባራዊ ካደረጉ የተማሪዎችን ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ ለማሻሻል ተስፋ ሰጭ ልምዶች ይገኛሉ ተብሎ ይታመናል።

ይህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ጥቅም ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ አግባብነት ባላቸው የትምህርት ሚኒስቴር እና ለዳሰሳ ጥናቱ ከተመረጡት ስድስት ክልሎች በተውጣጡ ባለሙያዎች በአውደ ጥናት እንዲተች ተደርጎ የተሰጡ አስተያየቶች ተካትተው እንድዘጋጅ ተደርጓል።

የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋቱን የሚጠቀሙት እነማን ናቸው?

ይህን የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት የትምህርት ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት፣ ሥርዓተ ፆታ ክበብ አስተባባሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች፣ የማህበረሰብ መሪዎች እና በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

የዚህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ዓላማ በትምህርት ቤት፣ በመምህራን፣ በወላጆች፣ በተማሪዎች እና አጠቃላይ በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር ለተማሪዎች ተገቢ ድጋፍ በማድረግ ውጤታቸውን ማሳደግ ነው፡፡ በመጨረሻም በችግር ላይ ያሉ ተማሪዎች ድጋፍ አግኝተው በትምህርታቸው ውጤታማ በመሆናቸው ሪድ-|| በዚህ ተግባር ለተሳተፉ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ይህን የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ለምን እንጠቀማለን?

የዚህ የትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋት ዋና ግቡ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ "ለተማሪዎች የተሟላ ስዕብና" ማደግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ለማድረግ ነው፡፡ በትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ድጋፍ ማድረግ ሲባል በትምህርት ውጤታቸው የተሻሉ እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን በደህንነታቸውና አጠቃላይ የእድገት ፍላጎታቸው ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ፍላጎቶቻቸው ከተሟሉ የትምህርት አቀባበላቸው፤ ውጤታቸውም በዚያው ልክ ስለሚጨምር ነው፡፡ ቀጥሎ የሰዎች ሁለንተናዊ ደህንነትና የዕድገት ፍላጎቶች የተዘረዘሩ ሲሆን እነዚህን ጉዳዮች በትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋቱ ሁሉም ይዘቶች ላይ የምንጠቀምባቸው ይሆናል፡፡

የሰዎች ሁለንተናዊ ደህንነትና የዕድገት ፍላጎቶች

አካላዊ ደህንነት	● ከአካል ጉዳትና አካላዊ ጥቃት የመጠበቅ መብት ● የሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት (ውኃ፣ ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ ጤና፣ ወዘተ) ● የመጫወት ችሎታና የተነቃቃ አካላዊ ሁኔታ መኖር
ስሜታዊ ደህንነት	● ከደህንነትና ከጉዳት የመጠበቅ ስሜት መኖር ● ስሜትን በነፃነት የመግለጽና የዕለት ተዕለት ኑሮ እርካታ መኖር ● ማንነትን የመገንዘብ፣ በራስ የመተማመንና ለራስ ክብር የመስጠት ስሜት መኖር ● የኃላፊነትና የሰው ችግርን እንደራስ የማየት ስሜት መኖር ● መልካም ነገርን የመጠበቅ ስሜት መኖር
ማህበራዊ ደህንነት	● ደህንነቱ በተጠበቀና ሰላማዊ በሆነ አካባቢ መኖር ● ከአቻ ጓደኛና ከሌሎች ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ● በሰዎች ላይ እምነት መጣል ● የባለቤትነት ስሜትመኖር
አዕምሮታዊ ደህንነት	● የመማር ዕድል መኖር፣ ያለማቋረጥ መሥራትና ውጤታማ መሆን ● በንቃት ማሰብና መመራመር ● ራስን ከሁኔታዎች ጋር የማስማማት እና የመፍጠር ችሎታን ማዳበር ● የማስተባበር ችሎታ መኖር

በትግበራ መሳሪያዎች/ስልቶች ቋቱ ውስጥ ምን ምን ርዕሰ ጉዳዮች ተካተዋል?

ሞጁል 1:- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት 1

ሞጁል 2:- የመጀመሪያ ደረጃ ልዩታ 19

ሞጁል 3:- ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት 31

ሞጁል 4:- ለተማሪዎች ምቹና ተስማሚ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር 39

ሞጁል 5:- ግብረ-ገብነት እና የትምህርት ቤት ህግና ደንብ 45

ሞጁል 6:- የማህበራዊ ስሜት ትምህርት 53

ሞጁል 7:- አካቶ ትምህርት 63

ሞጁል 8:- የፃታ እኩልነትን ያረጋገጡ ትምህርት ቤቶች 75

ሞጁል 1:- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት

ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለዜጎች በማዳረስ በኩል ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ትልቅ እድገት ማስመዝገቧን በትምህርት ሚኒስቴር የ2010 ዓ.ም ዓመታዊ የትምህርት መረጃ መፅሄት ላይ በአጠቃላይ በሀገሪቱ በ2010 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት 20,661,021 እንደነበር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች አዘውትሮ ትምህርት ቤት ያለመገኘት እና ማቋረጥ አስከ አሁንም ድረስ ያልተሻገርናቸው ችግሮች ናቸው፡፡ እንደማሳያ የአንደኛ ክፍል የማቋረጥ ምጣኔ 19.5 ፐርሰንት ሲሆን ይህም አሀዝ ከሁሉም የክፍል ደረጃዎች ከፍተኛ እንደሆነ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም ከሁለተኛ እስከ 5ኛ ክፍል አማካይ የማቋረጥ ምጣኔ 10 ፐርሰንት መሆኑን ያሳያል፡፡

በኢትዮጵያ የተማሪዎች አዘውትሮ ትምህርት ቤት የመገኘት ምጣኔ:-

- እንደሀገር 1ኛ ክፍል ተመዝግበው 5ኛ ክፍል የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ምጣኔ 53 ፐርሰንት ያህል ነው፡፡ የተማሪዎች እስከ 5ኛ ክፍል የቆይታ ምጣኔ ከክልል ክልል እንዲሁም በፆታ ልዩነት ይታያል፡፡
- በትግራይ ክልል 1ኛ ክፍል ተመዝግበው 5ኛ ክፍል የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ምጣኔ 84 ፐርሰንት ነው፡፡
- በደቡብ ህዝቦችና በኦሮሚያ ክልሎች 1ኛ ክፍል ተመዝግበው 5ኛ ክፍል የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ምጣኔ 46 ፐርሰንት ነው፡፡
- በሶማሌ ክልል 1ኛ ክፍል ተመዝግበው 5ኛ ክፍል የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ምጣኔ 52 ፐርሰንት ነው፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 1ኛ ክፍል ተመዝግበው 5ኛ ክፍል የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ምጣኔ በአማካይ 80 ፐርሰንት (ወንዶች 83 ፐርሰንት፣ ሴቶች 77 ፐርሰንት) ነው፡፡

የተማሪዎች ማቋረጥ ሲከሰት እንደቤተሰብ ብሎም እንደ ሀገር ከትምህርት ኢንቬስትሜንት የሚገኘውን ጥቅም ከማሳጣቱም በላይ የሀብት ብክነትን ያስከትላል፡፡ ስለሆነም በአንድ ትምህርት ቤት የተማሪ ማቋረጥ ችግር ከተከሰተ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ችግሩን አስቀድሞ ለመከላከል ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ይህ ሞጁል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በትምህርት ቤት መጀመርና ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ መሳሪያዎችን/ስልቶችን ይዟል፡፡

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ምንድን ነው?

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ችግር ላይ ያሉና ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ የሚችሉ ተማሪዎችን ለመለየት፣ ለመከታተልና ለመደገፍ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን መጠቀም የትምህርት ቤቶችን፣ የማህበረሰቡንና የወላጆችን ግንኙነት ከማጠናከሩም ባሻገር በችግር ላይ ያሉ ተማሪዎችን ፍላጎቶች በሚሟላት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስችላል፡፡

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ፕሮግራም (USAID, 2015) እንደጠቀሰው የተማሪዎች ማቋረጥ በድንገት የሚከሰት ሳይሆን ቀስ በቀስ በጊዜ ሂደት የሚመጣ ክስተት ነው፡፡ ይህም ማለት የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን መጠቀም የተማሪዎችን የማቋረጥ አዝማሚያዎች ወይም ምልክቶች አስቀድሞ ማወቅ ስለሚያስችል የሚመለከታቸው አካላት ከትምህርት ቤቶች ጋር በጋራ በመስራት ለማቋረጥ ጫፍ ላይ ያሉ ተማሪዎችን በመደገፍ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስችላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ እና በምን ዓይነት መንገድ ወደሥራ ብንገባ ለውጥ እናመጣለን የሚሉትን ጉዳዮች በስፋት እናያለን፡፡

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በትምህርት ቤቶች እንዴት ተግባራዊ እናደርጋለን?

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ማድረግ የልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የጋር ጥረት ይጠይቃል። ይህም የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንን፣ የክፍል ስም ጠሪዎችን፣ ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረትን፣ የሀይማኖትና የጎሳ መሪዎችን፣ ክበባትን፣ ወላጆችን፣ወዘተ ያጠቃልላል። ስለሆነም የተማሪዎችን ማቋረጥ ለመከላከል ማንኛውም አካል የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው።

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ሦስት ዋና ዋና ተግባራትን ማከናወን አለብን። ከሦስቱ ተግባራት ውስጥ አንዱ ቢጓደል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም። እነዚህም ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

1. ችግር ላይ ያሉ ተማሪዎችን መለየት
2. የቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ
3. በተማሪዎች ማቋረጥ ዙሪያ ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ ምክክር ማካሄድ

ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዱን ተግባር ለመፈጸም የምንከተላቸውን መንገዶች፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች በዝርዝር እንመለከታለን።

ተግባር 1፡- ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ስጋት ላይ ያሉ ተማሪዎችን መለየት

የተማሪዎች አዘውትሮ በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘት የማቋረጥ ዋና አመላካች ነው። ከትምህርት ቤት አዘውትሮ ያለመገኘት ደግሞ በምክንያት ወይም ያለምክንያት ከትምህርት ገበታ መለየትን ያጠቃልላል። ተማሪዎች ከምህርት ገበታ ላይ ለበርካታ ጊዜ መለየት የራሳቸውንም ሆነ የክፍል ጓደኞቻቸውን የመማር ሁኔታ ያሰናክላል። በተጨማሪም አዘውትረው በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘታቸው በትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፣ የመማር ፍላጎታቸውን ይቀንሳል፣ በመጨረሻም ለማቋረጥ ተጋለጭ ይሆናሉ። ስለሆነም ተማሪዎች አዘውትረው ትምህርት ቤት እንዲገኙ በሚያደርጉ ተግባራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ለማቋረጥ የተጋለጡትን ለመለየት ብሎም ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለመከላከል ይረዳል።

ተግባር 1ሀ፡- ተማሪዎች በየቀኑ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘታቸውን መከታተል

ይህ ተግባር ከክፍል ኃላፊ መምህራንና ከየትምህርት ዓይነቱ መምህራን መጀመር ይኖርበታል። ምክንያቱም እነዚህ አካላት ተማሪዎችን ለመከታተል ቅርበት ያላቸውና ቅድሚያ ኃላፊነት የሚጣልባቸው ስለሆነ ነው። ተግባሩን የክፍል ኃላፊ መምህራንም ሆኑ የየትምህርት ዓይነቱ መምህራን እስከ አሁንም ድረስ እየሰሩት እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም የሥም መቆጣጠሪያ ቅጽ በአግባቡ በማዘጋጀት ኃላፊ መምህራንና የየትምህርት ዓይነቱ መምህራን በየቀኑና በየክፍለ-ጊዜው ተማሪዎችን የመከታተሉን ተግባር አጠናክረው በመሥራት በየሳምንቱ መጨረሻ የተማሪዎችን የትምህርት መከታተል ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ማጠናቀር ተገቢ ይሆናል። የክፍል ኃላፊ መምህራን ደግሞ የተገኘውን መረጃ በየሳምንቱና በየወሩ በማደራጀት እና በመተንተን፤ ለማቋረጥ ስጋት ላይ ያሉ ተማሪዎችን ለይቶ ለትምህርት ቤቱ በማቅረብ ተገቢና ወቅቱን የጠበቀ ድጋፍ ተደርጎላቸው ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ይህ ተግባር በትምህርት ቤቶች እንደ ባህል ተወስዶ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ከተሠራ የአቋራጭ ተማሪዎችን መጠን በእጅጉ በመቀነስ የትምህርት ውጤታማነትን ማሳደግ ይቻላል።

ተግባር 1ለ፡- በአመቱ መጀመሪያ የተማሪዎችን ውጤት በመመዝገብ ደረጃ ማውጣት

የክፍል ኃላፊ መምህራን በአመቱ መጀመሪያ ላይ የተማሪዎችን የቀደመውን ዓመት ውጤት መግለጫ በስም መቆጣጠሪያ መዝገብ ላይ በማስፈር ደረጃ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ ደረጃ መሠረት ተማሪዎችን ምንም ችግር የሌለባቸው፣ በዝቅተኛ ችግር ላይ ያሉ፣ በመካከለኛ ችግር ላይ ያሉ፣ በከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ እና በጣም ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ በሚል መረጃውን ማጠናቀር፤ በዚህ የውጤት ደረጃ መሠረት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን መለየት ይችላሉ፡፡

ይህን መረጃ በመጀመሪያ ወር ላይ መዝግቦ መያዝ የማቋረጥ ተጋላጭነት ምልክት የሚታይባቸውን ተማሪዎች ለመለየት ያስችላል፡፡ በዚህም መሠረት በመጀመሪያ ወር የስም መቆጣጠሪያ መዝገብ ላይ ትምህርት ለመከታተል የተቸገሩትን ተማሪዎች ከማቋረጣቸው በፊት የተለየ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ያስችላል፡፡ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን እና ምክትል ርዕሰ መምህራን የሁሉንም ተማሪዎች ውጤትና ደረጃ በቋሚነት መከታተል ይገባቸዋል፡፡

ማሳሰቢያ

- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ተማሪዎችን ለይቶ ለማግለል መሥራት ማለት አይደለም፡፡
- ሁሉም የምንከታተላቸው ተማሪዎች ትምህርት ያቋርጣሉ ማለት አይደለም፡፡
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት የትምህርት ቤትን የሥራ አፈጻጸም መገምገም ማለት አይደለም፡፡

የክፍል ኃላፊ መምህርን የተማሪዎችን ውጤትና ደረጃ ለመስጠት የሚከተሏቸው መመሪያዎች

የክፍል ኃላፊ መምህራን የተማሪዎቹን መገኘትና አለመገኘት የሚያሳይ መረጃ ለሚከታተል አካል ማስተላለፍ አለባቸው፡፡ በመቀጠልም በትምህርት አመቱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት መጨረሻ እና የቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት ያለውን የተማሪዎች በትምህርት ቤት የመገኘትና ያለመገኘት ሁኔታን የሚያሳይ መረጃን የስም መቆጣጠሪያ በመጠቀም ማስላት አለባቸው፡፡

መምህራን የያንዳንዱን ተማሪ ውጤት እንደ ችግራቸው መጠን ማለትም ምንም ችግር የሌለባቸው፣ ዝቅተኛ ችግር ላይ ያሉ፣ መካከለኛ ችግር ላይ ያሉ፣ ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ እንዲሁም በጣም ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉተ ብለው ይመደባሉ፡፡

የእያንዳዱ ተማሪ ውጤት ሲታይ

0 - ምንም ችግር የሌለባቸው፣

1 - ዝቅተኛ ችግር ላይ ያሉ፣

2 - መካከለኛ ችግር ላይ ያሉ፣

3 - ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ፤

4 - በጣም ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ ተብሎ ይመደባሉ፡፡

የክፍል ኃላፊ መምህራን የተማሪዎችን ደረጃ የሚያሳይ ውጤት ማጠናቀሪያ ሰነድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም የሚሰራው እንደየተማሪዎቹ ውጤት ይሆናል /ምንም ችግር የሌለባቸው፣ ዝቅተኛ ችግር ላይ ያሉ፣ መካከለኛ ችግር ላይ ያሉ፣ ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ እና በጣም ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ ተማሪዎች/፡፡ በጣም ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ ተማሪዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ትምህርት ከማቋረጣቸው በፊት ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

በመቀጠል የተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘት አለመገኘታቸውን የሚያሳይ መረጃ እና ውጤታቸው እንደገና ይገመገማል:: በግምገማው ውጤት መሠረት የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ የክፍል ኃላፊ መምህራንና የየትምህርት ዓይነቱ መምህራን በጣም ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉና ትምህርት ሊያቋርጡ የሚችሉ ተማሪዎችን በመለየት ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: የተለየ ድጋፍና ክትትል ለአንደኛ ክፍል ተማሪዎች መደረግ ይኖርበታል:: ይህም የሚሆነው አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርት ለማቋረጥ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ስለሆኑ ነው:: የትኞቹ ተማሪዎች ችግር እንዳለባቸው ለመለየት የቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልቶችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በቀጣይ ክፍል ይቀርባል::

ትግባር 1 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነት

የክፍል ኃላፊ እና የየትምህርት ዓይነቱ መምህራን ተግባርና ኃላፊነት

- ተማሪዎች በየቀኑ ክፍል ውስጥ መገኘታቸውን መከታተል
- በየሳምንቱ መጨረሻ የተማሪዎችን ውጤትና ደረጃ በስም መጥሪያ መዝገብ ላይ ማስፈር
- የተማሪዎችን የችግር መጠንና የደረጃቸውን ሁኔታ የሚያሳዩ ቅጾችን መሙላት
- ሦስት ቀንና በላይ ቀሪ ያለባቸውን ተማሪዎች በቅጹ መሠረት ክትትል ማድረግ

የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንና ምክትል ርዕሰ መምህራን ተግባርና ኃላፊነት

- የክፍል ኃላፊ መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መገኘትና አለመገኘታቸውን ለማወቅ የሚያደርጉትን ጥረት ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ
- የተማሪዎችን የማቋረጥ መጠን ለመቀነስ ከወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረትና ከዎላጆች ጋር ተቀራርቦ መሥራት
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ዘመቻ በማካሄድ ችግሮችን መለየትና እርምጃ መውሰድ

የተማሪዎች ችግር መከታተያ ቅጽ

መመሪያዎች፡- የክፍል ኃላፊ መምህራን በአመቱ መጀመሪያ የተማሪዎችን ሥምና የክፍል ቁጥራቸውን ከሥም መጥሪያ መዝገብ ላይ በመውሰድ ቀጥሎ በተቀመጠው በተማሪዎች ችግር መከታተያ ቅጽ ላይ ማስፈር ይኖርባቸዋል። መምህራን የስም መቆጣጠሪያ መዝገባቸውን በመጠቀም የተማሪዎችን የሁለት ወር የቀሪ ሁኔታ ያሰላሉ፤ ይህንም ከትምህርት ቀናት አንፃር በማስላት ተማሪዎች ምን ያህል ቀናት ትምህርታቸውን እንዳልተከታተሉ መረጃ ይይዛሉ። የክፍል ኃላፊ መምህራን በአንድ ሳምንት ውስጥ 3 ቀንና በላይ ከትምህርት ገበታቸው ካልተገኙ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጋር ምክክር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ነጥብ	የተማሪዎች የማቋረጥ ችግር ደረጃ
3	ከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ (ከ 9 - 19 ቀናት ቀሪ የሆኑ)
2	መካከለኛ ችግር ላይ ያሉ (ከ 5 - 8 ቀናት ቀሪ የሆኑ)
1	ዝቅተኛ ችግር ላይ ያሉ (ከ 1 - 4 ቀናት ቀሪ የሆኑ)

የተማሪ የክፍል ቁጥር	የተማሪውሰም	በመጀመሪያው ወር ተማሪው በክፍል ውስጥ ይልተገኜባቸው ቀናት	+	በሁለተኛው ወር ተማሪው በክፍል ውስጥ ይልተገኜባቸው ቀናት	=	የቀሪ ቀናት ድምር	ነጥብ	የችግር መጠን	ምክንያቶች

የተማሪዎች የደረጃ መስጫ ቅጽ

<table>
<tr><td colspan="4" rowspan="6">*መመሪያ፡-* የክፍል ኃላፊ መምህራን በመጀመሪያው ወር መጨረሻ የተማሪዎችን የትምህርት መከታተል ሁኔታ የሚያሳየውን መረጃ ከመዘገቡ በኂላ የተማሪዎችን የደረጃ መስጫ ቅጽ ማሟላት አለባቸው። ተማሪዎችም 0፣ 1፣ 2፣ 3 እና 4 በሚል ደረጃ በቅድመ ማስጠንቀቂያ የተማሪዎች ችግር መከታተያ ቅጽ ላይ ይቀመጣሉ። ይህም ተማሪዎችን እንደችግራቸው ሁኔታ ለመለየት ያግዛል። የተማሪዎች ውጤት ከትልቁ በመጀመር ወደታች ይመዘገባል። ይህንም መረጃ የክፍል ሥም ጠሪ መምህራን ለርዕሰ መምህሩ/ሯ በቀጣይ ለሚወሰደው እርምጃ እንዲያግዝ በሚል ያስረክባሉ።</td><th>ውጤት</th><th>ጠቅላላ የተማሪዎች ድምር</th></tr>
<tr><td>4</td><td></td></tr>
<tr><td>3</td><td></td></tr>
<tr><td>2</td><td></td></tr>
<tr><td>1</td><td></td></tr>
<tr><td>0</td><td></td></tr>
<tr><th>ደረጃ</th><th>የተማሪ ስም</th><th>የቤተሰብ ስልክ ቁጥር</th><th>ወንድ</th><th>ሴት</th><th>ምክንያቶች</th></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
</table>

ተግባር 2፡- የቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ (Deploy First Response Strategies)



ቀደም ባለው ክፍል ትምህርት ለመቋረጥ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን በዳሰሳ ጥናት እንዴት መለየት እንደሚቻል አይተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ በዳሰሳ ጥናቱ የተገኙ መረጃዎችን ለተማሪዎች ትምህርት መከታተል እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል እናያለን።

የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ መከታተል፣ ውጤት መመዝገብና ደረጃ ማውጣት ተማሪዎች ችግር አጋጥሟቸው ትምህርት ከማቋረታቸው አስቀድሞ መስራት የሚገባንን ተግባራት ለማከናወን የሚያግዝ መረጃ ለማግኘት ያስችላል። በመረጃው መሰረት ወደ ተግባር ለመግባት የምንጠቀምባቸው ስልቶች ደግሞ የቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልቶች በመባል ይታወቃሉ። ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ከለየን በኋላ በፍጥነት ድጋፍ ወደማድረጉ ተግባር እንገባለን። ለዚህም የሚከተሉትን ሦስት የቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልቶች እንጠቀማለን።

1. የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ የሚከታተል ኮሚቴ ስብሰባ ማካሄድ
2. የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካርድ ማዘጋጀት
3. ወደቀሪ ተማሪዎች ቤት መሄድ

የእነዚህ ቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልቶች ማብራሪያ ቀጥሎ በዝርዝር ይቀርባሉ።

ተግባር 2ሀ፡- ተማሪዎች ለተከታታይ ሦስት እና ከዚያ በላይ ቀናት በትምህርት ገበታ ላይ ካልተገኙ ወዲያውኑ ክትትል መጀመር

በየትምህርት ሳምንቱ መጨረሻ የክፍል ኃላፊ መምህራንና የየትምህርት ዓይነቱ መምህራን ስለተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ መገኘት/አለመገኘት በስም መጥሪያው መዝገብ መሠረት ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህን ማድረጋቸው ደግሞ ለማቋረጥ በቋፍ ላይ ላሉ ተማሪዎች ወቅቱን የጠበቀ ድጋፍ በመስጠት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ያደርጋል። ተማሪዎች ሦስት እና ከዚያ በላይ ቀናት በትምህርት ገበታ ላይ ካልተገኙ ትምህርት ቤቱ ፈጣን የሆነ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል።

ተግባር 2ለ፡- የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ የሚከታተል ኮሚቴ በወር ሁለት ጊዜ ስብሰባ ማካሄድ አለበት

የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ የሚከታተል ኮሚቴ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ በሆኑ ተማሪዎች ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል። ይህ ኮሚቴ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህር፣ ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት ተወካይ እንዲሁም በክፍል ኃላፊ መምህራን የጋራ ትብብር የሚከናወን ተግባር ነው። በኮሚቴው ስብሰባ ላይ አባላት ትምህርት ለማቋረጥ በስጋትነት ለተለዩ ተማሪዎች የተከናወኑ ተግባራትን ይገመግማሉ፣ያቅዳሉ፤ በተጨማሪም ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን እርዳታ የሚሟላበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ።

የመማር ሁኔታ የሚከታተለው ኮሚቴ እንደ ትምህርት ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ ከ3-5 አባላት ይኖሩታል፡፡ ምክትል ርዕሰ መምህር እና የክፍል ኃላፊ መምህራን በአባልነት ይካተታሉ፡፡ ከኮሚቴ አባላት ውስጥ ቢያንስ አንዷ ሴት መሆን አለባት፡፡ ኮሚቴው በወር ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ በእነዚህ ተማሪዎች ላይ መምከር አለበት፡፡

ቀጥሎ ኮሚቴው በስብሰባ ወቅት ሊወያይባቸው የሚችል የናሙና ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ኮሚቴው በየጊዜው የሚያካሂደውን ስብሰባ የቀሪ ተማሪዎችን ሁኔታ ለመከታተል በተዘጋጀው ቃለ-ጉባኤ መዝገብ ማስፈር ይኖርበታል፡፡ ይህንንም ቃለ-ጉባኤ መዝገብ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ፋይል አድርጎ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡ ድጋፍ የተደረገላቸው ተማሪዎች ያሳዩትን ለውጥ ለመከታተል እና ወቅታዊ መረጃ በመያዝ የድጋፉ ሁኔታ በቀጣይ ምን መሆን እንዳለበት በአዲስ ለማቀድ ይጠቅማል፡፡ ኮሚቴው በስብሰባ ወቅት ቀጥሎ የቀረበውን የተማሪዎችን የክፍል ተግባቦት የሚያሳየውንቅጽ ("Classroom Communication Log") መገምገም ይኖርበታል፡፡

የተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ሁኔታን መከታተያ ቅጽ

ቀን	
የትምህርት ቤቱ ስም	
የመምህር ስም	
የሌሎች ተሳታፊዎች ስም	**የሥራ ድርሻ**

የተማሪ ሙሉ ስም	የታየው እድገት/መሻሻል	በቀጣይ የሚከናወኑ ተግባራት

የተማሪዎች የክፍል ተግባቦት ቅጽ (“Classroom Communication Log”)

መመሪያዎች፡- የክፍል ኃላፊ መምህራን የክፍል ተግባቦት ቅጽ በመሙላት ለመቋረጥ ከፍተኛ ችግር ላይ ካሉ የተማሪ ወላጆች ጋር መመካከር አለባቸው። ቅጹ የውይይቱን አጭር መግለጫና የቀጣይ የክትትል ሁኔታን የሚያሳይ ሊሆን ይገባል። ይህ ቅጽ የተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ሁኔታን የሚከታተለው ኮሚቴ ለማቋረጥ ከፍተኛ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን ለመደገፍና ለመከታተል ሊጠቀምበት ይገባል። ኮሚቴው ክንውኑን በየ15 ቀኑ በሚደረገው ስብሰባ ወቅት መገምገም ይኖርበታል።

ቀን	የተማሪ ስም	የመምህር ስም	የግንኙነት አግባብ				የውይይቱ ማጠቃለያ እና ቀጣይ የክትትል አግባብ
			የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካርድ	የአቻ ጓደኛ መረጃ (Peer Check-In)	ለማቋረጥ በስጋት ላይ ወዳሉ ተማሪዎች ቤት መሄድ	ከወላጆች/ አሳዳጊዎች ጋር የሚደረግ ስብሰባ	

ተግባር 2ሐ፡ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካርድን ማሰራጨት

የቅድሚያ ችግር መፍቻ ስልት የሚጀምረው ከመልካም ተግባቦት ነው፡፡ የመጀመሪያው የክፍል ኃላፊ መምህራን ተግባር ቀላል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ለምን ከትምህርት ገበታቸው ይቀራሉ የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ መረጃ ማሰባሰብ ነው፡፡ የክፍል ኃላፊ መምህራን ስለተማሪዎች በክፍል የመገኘት/አለመገኘት ሁኔታን ለማወቅ የሚያግዝ ቀጥተኛ መረጃ ለማግኘት የተማሪ ቤተሰብ አባላትን፣ ጓደኞቻቸውን፣ ጎረቤቶችን እንዲሁም ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረትን መጠየቅ አለባቸው፡፡

ሁለተኛው የስም ጠሪ መምህራን ተግባር ደግሞ ከቀሪ ተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡ ወላጆችና አሳዳጊዎች ትምህርታቸውን ለማቋረጥ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን በቤት ውስጥም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ ይህም ተግባር ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የተማሪዎችን ማቋረጥ በመከላከሉ ሂደት ዋና ተዋናይ እንዲሆኑ ይረዳል፡፡ በትምህርት አመቱ መጀመሪያ የተማሪዎችን ውጤት መሠረት አድርጎ በወጣው ደረጃ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተጋላጭ ተማሪዎችን ከለየን በኋላ ስም ጠሪ መምህራን የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካርድ በማዘጋጀት ወደ ተማሪዎች ቤት በተማሪዎች ወይም በጎረቤት አማካይነት ይልካሉ፡፡

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካርዱ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ስለ ተማሪው/ዋ የችግር ተጋላጭነት መጠን የሚገልጽ እና በትምህርት ቤት ተገኝተው በልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ ላይ ከስም ጠሪ መምህር እና ከርዕሰ መምህራን ጋር የምክክር ስብሰባ እንዲያደርጉ ጥሪ የሚያስተላልፍ ጭምር ነው፡፡

ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊዎች ጋር የስልክ ግንኙነት ማድረግ ደግሞ ሌላኛው ውጤታማ የሆነና ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሲቀሩ ከቤተሰብ ጋር የመጀመሪያ ግንኙነት በመፍጠር መረጃ ለማግኘት የሚጠቅም መንገድ ነው፡፡ ጥሪው በመምህራን ወይም በማህበረሰቡ ባሉ የበጎ ፈቃደኛ ሰዎች ሊከናወን የሚችል ሲሆን በስልክ ውይይቱ ላይ ተማሪዎች በትምህርት ዘመኑ ስለተመደበላቸው የትምህርት ቀናት ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ግልጽ ይደረጋል፡፡ በስልክ ውይይቱ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ስለቀሩበት ምክንያቶች ጭምር መረጃ ይገኛል፡፡ የተማሪዎቹ መቅረት ከስልክ ግንኙነቱም በኋላ የሚቀጥል ከሆነ የቅድሚያ ችግር ስልቶች አንዱ ወደሆነው ወደ ተማሪዎች ቤት የመሄድ ተግባር እናመራለን፡፡

ተግባር 2መ፡- ለማቋረጥ በስጋት ላይ ወዳሉ ተማሪዎች ቤት መሄድ

የተማሪችን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለው ኮሚቴ የተማሪዎች የቀሪ ሁኔታ እየተባባሰ መምጣቱን በሚያካሂደው ስብሰባ ከወሰነ ወደተማሪዎች ቤት የመሄድ ስልት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ወደተማሪዎች ቤት የመሄዱ ሁኔታ በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት ተወካዮች እንዲሁም በአካባቢው ማህበረሰብ አማካይነት ሊካሄድ ይችላል፡፡

ለማቋረጥ በስጋት ላይ ወዳሉ ተማሪዎች ቤት ለመሄድ የምንከተላቸው መመሪያዎች፡-

- ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን ስለሰጡን ጊዜ ምስጋና ማቅረብ
- ልጆቻቸው ትምህርት ቤት የቀሩባቸውን ምክንያቶች መጠየቅ

- ልጆቻቸው ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የሚያደርጉ ድጋፎችን ለማግኘት በሚያስችሉ መንገዶች ላይ ከመምህራን ወይም ርዕሰ መምህራን ጋር ተገናኝተው መምከር እንዳለባቸው ማሳሰብ።

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ቁልፉ ተግባር በወላጆችና በትምህርት ቤት መካከል ያለውን ግንኙነት በቀጥታና በተገቢው ጊዜ በማከናወን እንዲጠናከር ማድረግ ነው። ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ለማምጣት በሚደረገው ወደቤት የመሄድ ስልት የተማሪ አቻ ጓደኞች ቢሳተፉ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን ለመደገፍ ስላለው ቁርጠኝነት ያላቸው ግንዛቤ ከፍ ይላል።

ተግባር 2 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነት

የክፍል ኃላፊ እና የየትምህርት ዓይነቱ መምህራን

- የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ በሚከታተለው ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ
- የክፍል ተግባቦት ቅጽን (“classroom communication log”) በወቅቱ መሙላት
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካርድ (“rapid alert cards”) አሟልቶ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች መላክ
- ተማሪዎችን ቤት ለቤት ሄዶ ወደ ትምህርት ቤት የማምጣቱን ተግባር ማመቻቸት
- የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ ስብሰባ መርሀ ግብር ማውጣትና ማመቻቸት
- የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ መዝገብ ማሟላት
- ከወላጆች ጋር በሚደረጉ ስብሰባዎች መሳተፍ።

የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን

- የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ ስብሰባ መምራት
- የተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ የሚያከናውናቸውን ተግባራት መከታተልና መደገፍ

ማሳሰቢያ

- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጥሩ ሥራ እንደማይሰሩ መፈረጅ ማለት አይደለም።
- ተማሪዎችን ከፍተኛ የማቋረጥ ተጋላጭ ብሎ መለየት ተማሪዎቹን መቅጣት፣ ማግለል ወይም መምህራን በልጆቹ የትምህርት ውጤታማነት ላይ ዝቅ ያለ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ማለት አይደለም።
- ለትምህርት አቋራጭነት ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችና የተማሪ ወላጆች ለማቋረጥ ምክንያቶች ናቸው ባሏቸው ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ከፈጠሩ የመረጃውን ሚስጢራዊነት መጠበቅና በግል መያዝ ተገቢ ነው።



የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ካርድ

የማንበብና የመፃፍ ክህሎቶችን አስቀድሞ ማወቅ በቀጣይ ለሚኖረው የመማር ውጤት ወሳኝ ናቸው።

ልጅዎን በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት ይላኩ!

የትምህርት ቤቱ ስም፡- ______________________________

ክፍል፡- ______________________________

ወሰነ-ትምህርት፡- ______________________________

ውድ ____________________

ልጅዎ (ስም) ____________________ በ __________ ወር ለ __________ ቀናት በትምህርት ገበታ ላይ አልተገኘም/አልተገኘችም፤ ስለሆነም ትምህርቱን/ትምህርቷን የማቋረጥ ችግር ይገጥመዋል/ይገጥማታል።

እባክዎ ይህ የጥሪ ካርድ እንደደረስዎ ከልጅዎ መምህር ጋር ይገናኙ።

ልጅዎ እንዲማር/እንድትማር ድጋፍ በማድረግዎ እናመሰግናለን።

______________________________ ______________________________

የመምህር ስምና ፊርማ ቀን

ተግባር 3፡- በተማሪዎች ማቋረጥ ዙሪያ ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ መምከር

የትምህርት ማቋረጥን ለመከላከል ከምናከናውናቸው የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ተግባራት መካከል አንዱና የመጨረሻው እርምጃ ማህበረሰቡ በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በጋራ እንዲመክር ማድረግ ነው። ማንኛውም የማህበረሰብ አባል በተማሪዎች መማር ተጠቃሚ በመሆኑ ሁሉም አካላት በተለይም ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት፣ የሴቶች ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ፣ የሥርዓተ ፆታ ክበብ እና ሌሎች በትምህርት ቤቱ ያሉ ክበባት የተማሪዎችን ማቋረጥ ለመከላከል የበኩላቸውን ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል።

ተግባር 3ሀ፡- ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት ተማሪዎች ትምህርት እንዳያቋርጡ ያግዛል

- ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት የተማሪዎች ማቋረጥን ለመከላከል የቅስቀሳና የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘመቻ ከማከናወን ባሻገር በቀጣይ ምን ምን ተግባራትን መሥራት እንዳለብን በመጠቆም ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡
- ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ አዘውትረው እንዲገኙ ለማደረግ የሚከናወኑ ተግባራትን ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት በባለቤትነት ቢይዘው ውጤታማ ሥራ ይሰራል ተብሎ ይታመናል፡፡
- ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው እንዲቆዩ የሚያግዝ ኮሚቴ ለማቋቋም ትምህርት ቤቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ መሪዎች ጋር በቅርበት መሥራት አለበት፡፡
- ይህ ኮሚቴ ቀደም ሲል የተማሪዎች ማቋረጥን ለመከላከል ከተጠቀሱት ስልቶች በተጨማሪ ማቋረጥን ለመከላከል ትምህርት ቤቱ ያለበትን ጫና ለመቀነስ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- ኮሚቴው የተማሪዎች የማቋረጥ ሁኔታን ከተገነዘበ ልዩ ልዩ ቅጻቅጾችን እና የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ውሳኔዎች መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ በመገኘት ውይይቱን መከታተል ይኖርበታል፡፡
- በተጨማሪም የኮሚቴው አባላት የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሰራተኞች በሚያካሂዱት ልዩ ልዩ ስብሰባዎች በመሳተፍ ወደ ተማሪዎች ቤት ድረስ በመሄድ ከወላጆች ጋር ውይይት ማድረግ፣ ከወላጆች ጋር መወያየቱ ለምን እንደሚያስፈልግ፣ የቅስቀሳ/ውይይት ጊዜው መቼ መሆን እንዳለበት እንዲሁም ችግሮቹን ለመፍታት ምን ምን የመፍትሄ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው በሚጠቁሙ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

ሌሎች በኮሚቴው መከናወን የሚገባቸውና ትምህርት ቤቱን ሊደግፉ የሚችሉ ተግባራት ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

- ከቀሪ ተማሪ ወላጆች ጋር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መወያየት፡፡
- የአካባቢው ማህበረሰብ ተማሪዎችን በትምህርት ቀን ከትምህርት ቤቱ ግቢ ውጪ ቢያገኟቸው ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ምክር መስጠት፡፡
- ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተጋላጭ ከሆኑ የተማሪ ወላጆች ጋር በመወያየት ወላጆች ከውይይቱ በኋላ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለማምጣት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መከታተልና መገምገም

ተግባር 3ሰ፡- የውይይት መድረክ ማዘጋጄት

የውይይት መድረክ የቅስቀሳ እና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ለመስራት የምንጠቀምበት መሳሪያ ነው። ምንም እንኳን የተማሪ ማቋረጥ ፅንሰ-ሀሳብ ምን እንደሆነ ቢታወቅም ማህበረሰቡ ማቋረጥ በተማሪዎች የወደፊት ህይወት ሊያስከትል የሚችለውን የአጭርና የረጅም ጊዜ ችግር በማወቅ ላይ ውስንነት ይታያል፤ ይህም ሁኔታ በማህበረሰቡ ዘንድ ማቋረጥን ለመከላከል በሚደረገው ዝቅተኛ ተሳትፎ ይገለፃል። ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት በትምህርት ቤቶች በየወሰነ ትምህርቱ የሚደረጉ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና በመምራት የተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የመገኘት ጠቀሜታን ለማህበረሰቡ ማስገንዘብ ይችላል። በትምህርት ቤት ደረጃ ለወላጆችና ለአሳዳጊዎች የሚዘጋጀው መድረክ ትምህርታዊ እና አዝናኝ ሊሆን ይገባል። መድረኩ በጨዋታ ፣ በቀልድ፣ በቲያትር፣ በድራማ፣ በተማሪዎች ንባብና ሌሎች የቀለም ትምህርት ውድድሮች፣ ወዘተ መልክ ሊከናወን ይችላል። ይኸንም ድርጊት ለአካባቢው ማህበረሰብ በማቅረብ በትምህርት ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ አድርጎ መጠቀም ተገቢ ነው።

የውይይት መድረክ ፈጠራው በወሰነ ትምህርት አንድ ጊዜ ሊከናወን ይገባል። ሌላው የመድረኩ ጠቀሜታ ተማሪዎች ምን ምን እንደተማሩ፣ ያላቸውን ተሰጥኦና ክህሎት ለማህበረሰቡ በማቅረብ የማነሳሳት ሥራ ለመፍጠር ነው። ከዚህ ቀጥሎ ጥቂት ገላጭ የሆኑ ተግባራት በምሳሌነት ቀርበዋል።

የፕሮጀክት ሥራዎችን ማቅረብ፡- የተማሪዎችን ልዩ ልዩ የክፍል ሥራ ውጤቶችን በመማሪያ ክፍል ግድግዳዎች ላይ መስቀል።

ብቃት፡- በተማሪዎች መካከል የጨዋታ፣ የሙዚቃ ወይም የዳንስ ወይም ትምህርታዊ ውድድሮች ማካሄድ።

የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ የሚከታተል ኮሚቴ ውይይት፡- መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና ሥምጠሪ መምህራን በዚህ ኮሚቴ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በመጠቀም ከተማሪ ወላጆች ጋር የተናጠልም ሆነ የጋራ ምክክር በማካሄድ የተማሪዎችን በቀጣይ የማቋረጥ ምጣኔ ለመቀነስ በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርባቸዋል።

ይህ የውይይት መድረክ ወላጆች ስለትምህርት ጠቀሜታ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ብሎም የወላጅ-ትምህርት ቤት ግንኙነትን ለማጠናከር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ተግባር 3 ማጠቃለያ፡- ተግባርና ኃላፊነት

መምህራን

በየጊዜው የሚካሄዱ የውይይት መድረኮችን መከታተል።

ርዕሰ መምህራንና ምክትል ርዕሰ መምህራን

- የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ የስብሰባ መርሀ ግብር ማውጣትና ስብሰባዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።
- የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተለውን ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ መዝገብ ማሟላት።
- በስብሰባዎች መሳተፍ።

ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት

በወሰነ-ትምህርት አንድ ጊዜ ከማህበረሰቡ ጋር የሚካሄደውን የምክክር መድረክ በመጠቀም ተማሪዎች አዘውትረው ትምህርት ቤት መገኘታቸው ስለሚሰጠው ጠቀሜታ የግንዛቤ ማሳደግ ተግባራትን ማከናወን::

ግምገማና ማጠቃለያ

- *የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ያልንበት ምክንያት ትምርታቸውን ለማቋረጥ ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች ችግሩ ከመከሰቱ አስቀድሞ ፈጣን የሆነ ድጋፍ በማድረግ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለመታደግ ተብሎ ነው::*
- *የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ማለት ቀደም ብሎ ትምህርታቸውን ያቋረጡትን ተማሪዎች ወደትምህርት ቤት ማስመለስ ማለት አይደለም::*
- *የሚዘጋጀው የምክክር መድረክ ሁሉንም የማህበረሰብ አካል ማሳተፍ አለበት:: ከምክክር መድረኩ የሚገለል ግለሰብ መኖር የለበትም::*

ይህ ሞጁል የተዘጋጀው በትምህርት ቤቶች የቅድመ ማስጠንቀቂያ *ሥርዓትን* ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ የሆኑ የሂደት ደረጃዎችን እንዲያመላክት ተብሎ ነው:: ተግባራዊ በሚደረገው የቅድመ ማስጠንቀቂያ *ሥርዓት* የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሰራተኞች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ቀደም ሲል መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን የተማሪዎችን *ሥም* መዝግቦ የመያዝ፣ ትምህርታቸውን ስለመከታተላቸው ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ እና ሌሎችንም ተግባራት አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያግዝ መሆን አለበት:: የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት ተማሪዎችን በቁርጠኝነት ቁጥጥርና ክትትል ካደረጉ ለማቋረጥ ቋፍ ላይ ላሉ ተማሪዎች ድጋፍ በማድረግ ትምህርታቸውን ያለስጋት እንዲከታተሉ ማድረግ ይችላሉ::

በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች የቅድመ ማስጠንቀቂያ *ሥርዓትን* በአግባቡ ተግባራዊ ካደረጉ ድጋፍ ያጡና ሊያቋርጡ ችግር ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን አስቀድሞ ለይቶ በመደገፍ ትምህርታቸውን ተረጋግተው እንዲቀጥሉ በማድረግ የአቋራጭ መጠንን መቀነስ ያስችላቸዋል።

ሞጁል 2፡- የመጀመሪያ ደረጃ ልየታ

የመጀመሪያ ደረጃ ልየታ

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ልየታ ስልት የተነደፈው በዓመቱ መጀመሪያ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ቅበላ በምናደርግበት ወቅት ስለልጆቹ አጠቃላይ መረጃ እንዲኖረን ታስቦ ነው፡፡ የመረጃው ዓላማም መምህራን የልጆቹ መሠረታዊ የሂሳብና የንባብ ክህሎታቸው ምን እንደሚመስል አስቀድሞ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡

መረጃው መምህራን በትምህርት ዕቅድ ዝግጅታቸው ወቅት የእያንዳንዱን ህፃን የመማር ፍላጎት በመለየት ተገቢ ድጋፍ ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ልየታ ተግባር በፍጥነት ወይም በአጭር ጊዜ (ከ10-15 ደቂቃ) የሚከናወን ሲሆን ውጤቱ ስለልጆቹ መሠረታዊ የሂሳብና የንባብ ክህሎት መረጃ ለማወቅ ይረዳል፡፡

ይህ የልየታ ተግባር መምህራን አዲስ ገቢ ተማሪዎች በመሠረታዊ የሂሳብና የንባብ ክህሎት ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ያስችላቸዋል፡፡ እነዚህም የክህሎት ዓይነቶች፡-

- መቁጠር
- ቁጥሮችን መለየት
- መለየትና መመደብ
- መደመርና መቀነስ
- የተንደሉ የቁጥሮች ወይም የቅርጾች ድርድር ማሟላት
- ፊደላትን መለየት
- ትርጉም መስጠትና ቃላትን መገንዘብ
- አንብቦ መረዳት የሚሉት ናቸው፡፡

ማሳሰቢያ፡- የመጀመሪያ ደረጃ ልየታ

✗ የህፃናትን የእውቀት ደረጃ መለካት አይደለም፡፡ ውጤቱም በተማሪዎች ሪፖርት ካርድ ላይ ተፅእኖ አያሳድርም፡፡

✗ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ህፃናት መለየት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ህፃናት አንድን የተወሰነ ተግባር በተገቢው የእድሜ ደረጃ ለማከናዎን እጅግ በጣም ችግር ያለባቸው መሆኑን ለመለየት ይረዳል፤ በቀጣይም እነዚህን መምህራን መከታተልና መደገፍ ያስችላቸዋል፡፡

✗ እንደተከታታይ ምዘና በየቀኑ የሚከናዎን ሂደት ተደርጎ መቆጠር የለበትም

✓ የማስተማር ተግባር ውጤታማ እና ትርጉም ያለው የሚሆነው በትብብር ሲሰራ ነው

የቅድመ ልየታ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡- የተማሪዎችን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ ሰነድ እና እርሳስ

ልየታውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ጊዜ፡- ለእያንዳንዱ ህፃን ልየታ የሚወስደው ጊዜ ከ10-15 ደቂቃ መሆን ይኖርበታል፡፡

የአሰራር ቅደምተከተል፡- ቅድመ ልየታው የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት በመገምገም ያለባቸውን ክፍተት ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ማሳሰቢያ፡-

- የቅድመ ልየታውን ተግባር አስመልክቶ ተማሪዎች አስቀድሞ መረጃው እንዲኖራቸው ማድረግና ሁሉም ተማሪዎች በልየታው ወቅት የሚያውቁትን ሁሉ የማቅረብ ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡
- የቅድመ ልየታውን ተግባር ለማከናወን የተመረጠው ቦታ ምንም የሚረብሽ ሁኔታ የሌለበትና ፀጥታው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

የአሰራር መመሪያዎች፡-

- ተማሪዎችን ሥማቸውን በመጥራት ሰላምታ ማቅረብ፡፡
- የቅድመ ልየታ ተግባሩ ከ10-15 ደቂቃ እንደሚወስድ ለተማሪዎች በግልጽ መንገር፡፡
- ተማሪው/ዋ ስለመዘጋጀቱ/ቷ መጠየቅ አዎ ተዘጋጅቻለሁ ካለ/ካለች ወደ ተግባር መግባት፡፡
- እያንዳንዱ ተማሪ የሚሰጠው ምላሽ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ መስፈር አለበት፡፡
- ተማሪዎች እርሳስ በአግባቡ ይዘው መፃፍ የማይችሉ ከሆነ እንዲፅፉ ማስገደድ ተገቢ አይደለም፡፡ መፃፍ ባይችሉም እንኳን በቃላቸው ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ ወይም ደግሞ መልሱን በተዘጋጀው ሰነድ ላይ በጣታቸው ጠቁመው ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎች የተሰጧቸውን የቁጥሮች ወይም የቅርፆች ድርድር የሠሩበትን መንገድ በመመልከት ግንዛቤ ከወሰዳችሁ በኋላ ምን ምን እንደሚያውቁና እንደማያውቁ ትገነዘባላችሁ፡፡

የውጤት ትንተና መሥራት

በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት የተማሪዎችን ልየታ ተግባር ካከናወን በኋላ የእያንዳንዱን ተማሪ የሂሳብና የንባብ መሠረታዊ ክህሎት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህን የውጤት ትንታኔ የማስተማሩን ሂደት ቅርጽ ለማስያዝ መጠቀም አለብን፡፡ በተደረገው የልየታ ሥራ አብዛኛው ተማሪ ፊደልን ወይም ቁጥርን መለየትና መገንዘብ ካልቻለ ወደ ከፍተኛ ክህሎት ከመሸጋገር አስቀድሞ ተጨማሪ ጊዜ ወስዶ ድጋፍ በማድረግ በልጆቹ ላይ የታየውን የክህሎት ክፍተት መሙላት ተገቢ ነው፡፡

ማሳሰቢያ፦

- ይህ የቅድመ ልየታ መሳሪያ ስለተማሪዎች መሠረታዊ የሂሳብና የንባብ ክህሎት መነሻ የሚሆን መረጃ ሊሰጠን ይችላል እንጅ የተማሪዎቹን አጠቃላይ የመማር ችሎታ ያንፀባርቃል ማለት አይደለም።
- ልየታው ከተጠናቀቀ በኋላ በውጤቱ መሠረት ፊደልና ቁጥር የለዩትን ካለዩት ጋር በማቀናጀት ልጆቹ ፊደላትንና ቁጥሮችን በድምጽ እየጠሩ እንዲለማመዱ እድል መስጠት ተገቢ ነው። ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ከመምራን ይልቅ ጓደኞቻቸው ሲደግፏቸው ውጤታማ ሲሆኑ ይታያል።
- ልየታው ከተጠናቀቀ በኋላ በውጤቱ መሠረት ተማሪዎች ድምፅ እያወጡ እንዲጠሩና የሥማቸውን ስርዓተ ሆሄያት መለየት እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል። አዘውታሪ ቃላትን በፍጥነት መማር ስለሚቻል ልጆቹ ወዲያውኑ ውጤታማ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል።

ሰነድ-1 ሂሳብ፦ የቁጥር ትርጉም (Number Sense)

	ቁጥሮችን ደጋግሞ መቁጠር፦ ተማሪዎች እስከ 20 እንዲቆጥሩ አድርጉ። **ማስታወሻ፦** እያንዳንዱ ተማሪ ያለምንም ስህተት የደረሰበትን/ችበትን ቁጥር አክብብ/ቢ። ከ20 በላይ መቁጠር አይጠበቅም። ተማሪዎቹ ሳያቋርጡ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መቁጠር ከቀጠሉ የደረሱበትን ቁጥር ቀጥሎ ባለው አስተያየት መስጫ ቦታ ላይ መፃፍ ይቻላል።	
	2 3 4 5 6 7 8 9 10 11 12 13 14 15 16 17 18 19 20	
	አስተያየት፦	

1	2	3	4	5	6	
7	8	9	10	11	12	13
14	15	16	17	18	19	20

ሰነድ-2 ሂሳብ፡- የቁጥር ትርጉም-ቁጥሮችን መለየት

	የቁጥር ልየታ፡- ተማሪዎች ቀጥሎ ከ1-20 የቀረቡትን ቁጥሮች በቅደም ተከተል እንዲጠሩ አድርጓቸው፡፡ በትክክል የጠሯቸውን ቁጥሮች አክብቧቸው፡፡	
	3 13 9 17 5 19 6 2 10 14 12 1 18 8 16 6 20 15 4 11	
	አስተያየት፡-	

3	13	9	17	5	19	6	2
10	14	12	1	18	8	16	
6	20	15	4	11			

ሰነድ-3 ሂሳብ - ቅድመ አልጀብራ-ድርድሮች (shape patterns)

	ድርድሮች፡- የቅርጾችን ድርድር ለተማሪዎች አሳዩ። ተማሪዎች በቀጣይ የሚመጣውን የቅርጽ ዓይነት ጠይቋቸው። በመቀጠልም ቅርጾቹን በመሳል ድርድሩን እንዲያሟሉ አድርጉ።	
	የሚከተለውን የቅርጾች ድርድር ተመልከቱ፡- የቅርጾቹ ድርደር ክብ፣ ካሬ፣ ክብ፣ ካሬ፣ እያለ ቢቀጥል በዚህ ድርድር መሠረት በቀጣይ ሊከተሉ የሚችሉት ሁለት ቅርጾች ምን ምን ናቸው? ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ካዳመጥን በኂላ በትክክል እንዳልመለሱ ካወቅን ክብ፣ ካሬ በማለት እንገራቸው። በመጨረሻም የክብና የካሬን ቅርጾች በመሳል እናሳያቸው።	
	አስተያየት፡-	

ሰነድ-4 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ክህሎት፡- ሆሄያትን መለየት

	ተማሪዎች የአማርኛ ሆሄያትን እንዲያነቡ ጠይቋቸው:: በመቀጠል በትክክል የተነበቡትን ፊደላት ይክበቧቸው:: ተማሪዎች የአማርኛ ሆሄያትቱን ማንበብ ካልቻሉ እርስዎ ያንብቡላቸው::	
	አስተያየት፡-	

የአማርኛ ሆሄያት

	ä	u	i	a	e	ï	o
h	ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
l	ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ
h	ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ
m	መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
r	ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
s	ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
sh	ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ
q	ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
b	በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
t	ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ch	ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ
n	ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
n	ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
a	አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ
k	ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ

	ä	u	i	a	e	ï	o
h	ኸ	ኹ	ኺ	ኻ	ኼ	ኽ	ኾ
w	ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
a	ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ
z	ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ
zh	ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ
Y	የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ
d	ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
j	ጀ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ
g	ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
t	ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
ch	ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ
p	ጰ	ጱ	ጲ	ጳ	ጴ	ጵ	ጶ
s	ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
f	ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
p	ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ

ሰነድ-5 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት፡- ፊደላትን መለየት

	ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ፊደላትን እንዲያነቡ ጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል በትክክል የተነበቡትን ፊደላት ይክበቧቸው፡፡ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ፊደላቱን ማንበብ ካልቻሉ እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡	
	አስተያየት፡-	

የእንግሊዝኛ ሆሄያት



ሰነድ 6 - የቋንቋ ክህሎት፦ የፊደላትን ቅርጽ በመለየት ትርጉም መስጠት፣ ቃላትን መገንዘብ እና አንብቦ መረዳት

	ተማሪዎች የሚከተለውን ጽሁፍ በትክክል እንዲያነቡና ትክክለኛውን ስዕል እንዲያከቡ ወይም እንዲያመለክቱ ጠይቋቸው። በትክክል ያነበቧቸውን ቃላት ምልክት አድርጉባቸው። መምህር ተማሪዎቹ ጽሁፉን ማንበብ ካልቻሉ እርስዎ ያንብቡላቸው። ጽሁፉን ሊገልጽ የሚችለውን ስዕል ያክብቡላቸው ወይም በጣትዎ ያመልክቷቸው።	
	አስተያየት፦	

The cat fell in the mud - ድመቷ ጭቃ ሳይ ወደቀች



ሞጁል 3፡- ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ

በኢትዮጵያን የትምህርት ስርዓት ካሉት የትምህርት ተግዳሮቶች መካከል የተማሪዎች ማቋረጥ አንዱ ነው:: በመሆኑም ይህን ችግር ለመቀነስ የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው:: በዚህም መሠረት ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ በትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ቢደረግ ወላጆች እና አሳዳጊዎች ተማሪዎችን በተገቢው ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት መጥተው እንዲመዘገቡ እንዲሁም አቋራጭ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ የማድረግ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያበረታታል:: በተጨማሪም በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች ማለትም ስደተኞች በሰፈሩባቸው ቦታዎች (refugee camps) እና አካባቢያዊ በሆኑ የእርስበርስ ግጭት የተነሳ የተፈናቀሉ፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው፣ የጎዳና ተዳዳሪ እንዲሁም የአርብቶ አደር ልጆች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ለማድረግ የተለየ ድጋፍና ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው::

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ ምንድን ነው?

የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት የተማሪዎችን ማቋረጥ አስቀድሞ በሚከናወኑ ተግባራት መከላከል ሲሆን ይህ ሞጁል ደግሞ በአመቱ መጀመሪያ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ አዲስና ነባር ተማሪዎችን እንዲሁም አቋርጠው የቆዩ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት በማምጣት ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ በአዲስ መጀመርና ተግባራዊ ማድረግ በአመቱ የትምህርት መጀመሪያ የተማሪዎች ምዝገባ በተገቢው ጊዜ ለማካሄድና አቋራጭ ተማሪዎችን ለማስመለስ ቁልፍሚና ይጫወታል ተብሎ ይታመናል::

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻን የሚመሩትና የሚያስተባብሩት አካላት፡-

- ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች
- የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ
- የትምህርት ቤት አመራር
- ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት
- የቀበሌ አስተዳደር
- መምህራን
- ተማሪዎች
- የኃይማኖትና የማህበረሰብ መሪዎች
- የትምህርት ቤት ክበባት
- ሌሎች

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻን እንዴት ተግባራዊ እናደርጋለን?

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻን በትምህርት ቤቶች እውን ለማድረግ ሦስት ተግባራትን መፈጸም ይኖርብናል:: እነዚህም ተግባራት፡-

1. የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር
2. ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ መለየት
3. ተማሪዎችን መከታተልና የተሻለ ሥራ ለሰሩ ወላጆች ዕውቅና መስጠት

1. የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር

ተግባር 1ሀ:- ቡድን መመስረት

ተማሪዎች በየአመቱ ወደ ትምህርት ቤት መጥተው እንዲመዘገቡ ለማድረግ የገጠርም ሆነ የከተማ ቀበሌ አስተዳደሮች የዘመቻ ቡድን ያቋቁማሉ:: ስለሆነም ዘመቻውን በአግባቡ ለማካሄድ ከቀበሌ አስተዳደሮች ጋር በቅርበት መሥራት ተገቢ ነው:: በቡድን አባልነት መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት፣ ወላጆች፣ የማህበረሰብ ተወካዮች፣ አርአያነት ያላቸው የተማሪ ወላጆች፣ የሀይማኖት ተወካዮችና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት የሚካተቱ ይሆናል::

የዘመቻ ቡድኑ ዋና ኃላፊነት ወላጆችና አሳዳጊዎች ስለትምህርት ጠቀሜታ ተገንዝበው ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ለማነሳሳት ነው:: እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዘመቻውን የሚመራና ዘመቻው የታለመለትን ዓላማ በትክክል ማሳካቱን የሚያረጋግጥ የቡድን መሪ መሰየም ይጠበቅበታል::

ተግባር 1ለ:- ዘመቻውን ማስጀመር

ዘመቻውን እውን ለማድረግ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር ጠቃሚ ተግባር ነው:: የዘመቻው ግብ ማህበረሰቡ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልክ ለማነሳሳት ነው:: የዘመቻ ቡድኑ ዘመቻው የሚጀመርበትን እና የሚጠናቀቅበትን ቀን በመወሰን ወላጆች፣ ማህበረሰቡ፣ በየደረጃው ያሉ አመራርና ባለሙያዎች ያለመታከት እንዲሰሩ በማስቻል ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ያደርጋል::

ተፅዕኖ ፈጣሪ የማህበረሰብ አባላት እና ሌሎች አርአያነት ያላቸው ግለሰቦች፣ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን እና መምህራን የዘመቻ ማስጀመሪያ እና በዘመቻው ሂደት ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት የዘመቻውን ዓላማ ለማህበረሰቡ ማሳወቅ፣ መመዝገብ ያለባቸውን ተማሪዎች ብዛት መረጃ መስጠት እንዲሁም በጎ ፈቃደኛ ግለሰቦች በተማሪዎች ምዝገባና አቋራጮችን ወደ ትምህርት ቤት ለማስመለስ በሚደረገው ጥረት ድጋፍ እንዲያደርጉ የመጠየቅ ሥራ ማከናወን ይኖርባቸዋል::

በተጨማሪም በዘመቻው ወቅት ያሉትን አጋጣሚዎች ለምሳሌ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን፣ እድሮችን፣ በሀይማኖት ተቋማት የሚካሄዱ ስብሰባዎችን በመጠቀም ወላጆችና አጠቃላይ ማህበረሰቡ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ መልዕክት ማስተላለፍና የአህዝቦት ሥራ መሥራት ይጠበቃል::

ተግባር 1ሐ: አካባቢያዊ እና ክልላዊ ሚዲያዎችን መጠቀም

የዘመቻ ቡድኑ አካባቢያዊ እና ክልላዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ማህበረሰቡ፣ የማህበረሰብና የሀይማኖት መሪዎች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ እና በትምህርት ገበታ ላይ ያሉት ተማሪዎች ደግሞ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የማድረግ ተግባራትንማከናወን ይጠበቅበታል:: ጠንካራ የአካባቢ ሚዲያ ዘመቻ ደግሞ እንደ ፖስተር፣ ባነር፣ ብሮሸር፣ የራዲዮና የቴሌቪዥን መልዕክቶችን፣ የህትመትና የኤሌክትሮኒክ ውጤቶችን በመጠቀም አስፈላጊ መልዕክቶችን በስፋትና በጥራት ማስተላለፍ ይችላል::

አካባቢያዊ እና ክልላዊ ሚዲያዎች ስለትምህርት ጠቀሜታ በተማሪዎችና በመምህራን የሚፈልቁ ይዘቶችን በማስተላለፍ፣ በትምህርታቸው አርአያነት ያላቸውን ተማሪዎች ግለ-ታሪክ በማቅረብ እና በልጆቻቸው

ትምህርት ውጤታማ የሆኑ ወላጆችን ምስክርነት እንዲሰጡ በማድረግ የአህዝቦት ሥራ መሠራት ይችላሉ:: የሚዲያ ውጤቶች በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ለትምህርት ቤቱና ለአካባቢው ማህበረሰብ ማሰራጨት ይቻላል:: የተማሪዎችን የምዝገባ ቀን በዋና ዋና መንደሮች እና ማህበረሰቡ በብዛት እየተገናኘ የተለያዩ ተግባራትን በሚያከናውንባቸው ቦታዎች ማስታወቂያ ወረቀት በመለጠፍ ማሳወቅ ይኖርብናል:: በተጨማሪም የተማሪዎችን የምዝገባ ቀን በትምህርት ቤት ግቢ በሚገኝ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ የተማሪ ወላጆች እንዲያነቡትና ማስታወሻ በመያዝ በሚኼዱበት አካባቢ ሁሉ ስለምዝገባው ቀን እንዲያሳውቁ አስቀድሞ ለወላጆች ግንዛቤ መፍጠር ጠቃሚ ነው::

የዘመቻ መሪ/ አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት

- ዘመቻውን የሚጀመርበትን ቀን ማስቀመጥ
- ማህበረሰቡን በመሰብሰብ የዘመቻውን መጀመር ማብሰር

የዘመቻ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

- ዘመቻውን አስመልክቶ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ለተመረጡ ወላጆችና የማህበረሰብ ክፍሎች ማዘጋጀት
- ለማህበረሰቡ ምስጋና ማቅረቢያ መድረክ መፍጠር
- በትምህርት ጉዳይ ማህበረሰቡ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ስብሰባ በማካኼድ ቃል ማስገባት

2. ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ መለየት

ተግባር 2ሀ:- ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ያላኩ ወላጆችን መለየት

ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ የመለየት ተግባር በቀበሌ ደረጃ ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ እንዲሁም ትምህርታቸውን ያቋረጡ እና እንደገና ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ችግር ላይ ያሉ ተማሪዎችን ማወቅ ጠቃሚ ነው:: ይህ ተግባር በማህበረሰቡ ውስጥ እየኖሩ በልዩ ልዩ ችግር ምክንያት ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ነገር ግን ሁኔታዎች ቢመቻቹላቸው መማር የሚችሉ ተማሪዎችን ለመለየት ጭምር ያግዛል:: በተጨማሪም ተግባሩ በዘመቻው ወቅት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸውን ወላጆች ለማግኘት ይረዳል::

የዘመቻ ሂደቱ ማህበረሰቡ ሁሉም ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን የአርብቶ አደር ተማሪዎችና ጎዳና ተዳዳሪ ህጻናትን ጭምር ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመምከር የተለያዩ ስልቶችንና አቀራረቦችን እየነደፈ እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ልጆቹ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ያስችላል::

ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ አስቀድሞ ለይቶ ማወቅ የዘመቻውን ሂደት በመከታተል የሚያመጣውን መሻሻል ቦታው ላይ በአካል ተገኝቶ ማረጋገጥ ያስችላል::

የዘመቻው መሪ/አስተባባሪ የዘመቻ ቡድኑን ጨምሮ የቀበሌ አመራሮችንና በቀበሌው ክልል ውስጥ ያሉ የበጎ ፈቃደኛ ሰራተኞችን በመሰብሰብ ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ ለይቶ የማወቅ ስልት ልጆቹን ለማምጣት ስላለው ጠቀሜታ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሰራል::

በስብሰባው ላይ ተሳታፊዎቹን በአነስተኛ ቡድን በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን በቀበሌው ክልል ውስጥ የተወሰነ አካባቢ እንዲይዝ ይደረጋል። ለእያንዳንዱ ቡድን ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎች ዝርዝር ይሰጣል። እያንዳንዱ ቡድን ወረቀትና እርሳስ በመያዝ፡-

- የተሰጠውን አካባቢ ከነምልክቶቹ (ለምሳሌ፡ - መንገድ፣ ወንዝ፣ ጎጥ፣ መንደር፣ አጎራባች አካባቢ ወይም ወሰን) የያዘ ካርታ መሥራት አለበት።
- አካባቢውን ሊገልጽ ይችላል የተባሉ መለያ ምልክቶችን (ለምሳሌ፡- ትምህርት ቤት እና የእምነት ተቋማት) በካርታው ላይ ማካተት ይኖርበታል።
- በአካባቢው ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ያላኩ ወላጆችን ምልክት አድርጎ በጥንቃቄ መያዝ አለበት።

ማሳሰቢያ

- በዘመቻ ቡድኑ ወንዶችም ሴቶችም መካተታቸውን ማረጋገጥ አለብን።
- በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለዘመቻው አስፈላጊ የሆኑ መልዕክት ማስተላለፍ አለብን።
- በአካባቢው ከሚገኝ ሚዲያ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስለትምህርት አርአያነት ያላቸውና ተማሪዎችን ለትምህርት የሚያነሳሱ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ተገቢ ነው።

ተግባር 2ለ፡- ቤት ለቤት አሰሳ ማካሄድ

አርአያ የሆኑ ወላጆችን መምረጥ፡- በቤት ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የላኩ ወላጆችን በፈቃደኝነት ወደ ዘመቻ ቡድኑ ማካተት ያስፈልጋል።

ለቅስቀሳ ቤት ለቤት በሚሄዱበት አካባቢ ሁሉንም ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ የተጠቀሙባቸውን ስልቶች ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ ለዘመቻው ውጤታማነት ያግዛል።

ማሳሰቢያ

- ወጣት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ በመለየቱ ተግባር እንዲሳተፉ ማድረግ።
- አርአያነት ያላቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ያላኩ ወላጆችን በማነሳሳት ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ ማድረግ።

ቤት ለቤት አሰሳ ማካሄድ፡- በቡድን በቡድን በመሆን ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ያላኩ ወላጆችን ቤት ለቤት አሰሳ በማካሄድ ከወላጆች ጋር ግንኙነት መፍጠር አለብን። በወላጆች/በአሳዳጊዎች ቤት በምንገኝበት ጊዜ ተገቢውን ክብርና ሠላምታ በማቅረብ ተግባቦትን መፍጠር ይጠበቅብናል። በመቀጠል በተማሪዎች ፍላጎትና ምዝገባ ዙሪያ ያሉትን ተግዳሮቶች በተመለከተ ውይይት በማካሄድ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ማበረታታት ይኖርብናል። በተጨማሪም የተማሪዎችን የትምህርት ቤት ምዝገባ ቀናት ለወላጆች ማስገንዘብ ይጠበቃል። በመጨረሻም የዘመቻ ቡድኑ በካርታው መሠረት በሄደባቸው አካባቢዎች ያከናወናቸውን ተግባራት በማስታወሻ መዝግቦ መያዝ አለበት።

የቤት ለቤት ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ከዘመቻው ተሳታፊዎች ጋር እንደገና በመገናኘት ስላለው መሻሻል ግምገማ ማካሄድ አስፈላጊ ነው። በመቀጠልም ተሳታፊዎቹ ቀደም ሲል በነበራቸው የአነስተኛ ቡድን ክፍፍል መሠረት አንድ ላይ እየሆኑ በቤት ለቤት አሰሳው ወቅት ስላገኙት ልምድ እንዲወያዩ ማድረግ አለባቸው። ተሳታፊዎቹ እርስበርሳቸው በመጠያየቅ በየሄዱበት አካባቢ በተደረገ ምልከታ ተመሳሳይነትና ልዩነት ስላላቸው ጉዳዮች፣ በወላጆች/ በአሳዳጊዎች ፍላጎቶች ዙሪያ፤ በአጠቃላይ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት በማምጣት ዙሪያ ስለተሰጠው ትኩረት በተመለከተ ውይይት በማድረግ ልምድ እንዲለዋወጡ ማበረታታት ተገቢ ነው።

ለውይይት ምሳሌ የሚሆኑ ጥቂት ጥያቄዎች ቀጥሎ ቀርበዋል።

- አሰሳ በተደረገባቸው አካባቢዎች ምን ምን ተመሳሳይነት ያላቸው ጉዳዮች ተለይተዋል?
- ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ የሚያደርጋቸው ነገሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? እንዴት?
- ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የማይልኩባቸው ምክንያቶች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መጥተው እንዲመዘገቡ ለማድረግ በወላጆች/በአሳዳጊዎች በኩል የተሰጡ ምክረ-ሀሳቦች ምን ምን ናቸው?

የሁሉም ቡድኖቹ ማጠቃለያና ፅብረቃ፡- ሁሉንም የቡድን አባላት በአንድ ላይ እንዲሰበሰቡ በማድረግ እያንዳንዱ ንዑስ ቡድን የሰራበትን ቦታ የሚያሳየውን ካርታ በሚታይ ቦታ ላይ በማቅረብ ተራ በተራ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ ልምድ መለዋወጥ አለባቸው።

- ከተከናወኑት ተግባራት እንደማህበረሰብ ምን ተማርን?
- የተገኘውን መረጃ ለዘመቻው ሥራና ተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?
- ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት በማምጣት እንዲያስመዘግቡና ትምህርታቸውን አዘውትረው እንዲከታተሉ ለማድረግ በቀጣይ ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው?

ለምሳሌ፡- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ያግዛል።

> **ማሳሰቢያ**
>
> የዘመቻውን ሥራ በይፋ እንዳስጀመርነው ሁሉ የዘመቻውን መጠናቀቅና ያስመዘገበውን ውጤት በተደራጀ ሪፖርት ለማህበረሰቡ በይፋ ማሳወቅ ተገቢ ነው።

ተግባርና ኃላፊነት

የዘመቻው መሪ/አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት

- በጎ ፈቃደኛ ሰራተኞችን፣ የማህበረሰብ፣ የቀበሌና ንዑስ ቀበሌ መሪዎችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎችን አካባቢ በመለየት ተግባር ላይ ማሳተፍ።
- የዘመቻውን ዓላማና ጠቀሜታ ለቡድኑና ለንዑስ ቡድኖቹ ገለፃ ማድረግ፤ ከዘመቻው በኋላ የተካሄዱ የንዑስ ቡድኖችና የቡድኑ ማጠቃለያዎችን መምራት።
- ተማሪዎች ለምዝገባ ስላላቸው ዝግጁነት፣ አዲስ ገቢ፣ ነባርና አቋራጭ ተማርዎችን ምዝገባ ሂደት በወቅቱ እንዲከናወን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ።

የዘመቻ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

የንዑስ ቡድን አባል በመሆን ቤት ለቤት በመሄድ፣ የጎዳና ተዳዳሪ ተማሪዎች ባሉበት አካባቢ በመሄድ፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ ተማሪዎች በሚገኙበት አካባቢ፣ በስደተኛ ካምፖች (refugee camps) እና አርብቶ አደሮች በሚገኙበት አካባቢ በመሄድ ነዋሪዎችንና ከትምህርት ቤት ውጭ የሆኑ ተማሪዎችን የመለየት ተግባራትን ማከናወን አለባቸው፡፡

ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎች የሚገኙበትን አካባቢ በመለየቱ ተግባር በየቡድኑ ተመሳሳይነት ያላቸውን ጉዳዮች ማወቅ፣ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጡ የሚያደርጓቸውን ተግዳሮቶች በአንድ ላይ ማሰባሰብ እንዲሁም እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት ጥቅም ላይ የሚውሉ ስልቶችን የመጠቆም ሥራ ማከናወን አለባቸው፡፡

3. ተማሪዎችን መከታተልና የተሻለ ሥራ ለሰሩ ወላጆች ዕውቅና መስጠት በሪፖርቱ የተገኙ ውጤቶች/ግኝቶች

የእያንዳንዱን ህፃን ምዝገባ ሁኔታ በሥምና በአድራሻ እንዲሁም ወላጆችና ተማሪዎች ስለዘመቻው ያላቸውን አስተያየት መቀበል ጠቃሚ ነው፡፡ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለላኩ ወላጆች በስብሰባ ወይም ደብዳቤ በመላክ ክብርና መስጋና መስጠት፡፡

ከዘመቻው በኋላ የማጠቃለያ ስብሰባ በማካሄድ ትምህርት ቤቶች አዲስ ገቢ፣ ነባርና አቋራጭ ተማሪዎችን ምዝገባ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲከናወን ዝግጁ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡

ተግባርና ኃላፊነት

የዘመቻ መሪ/አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት

- ሁሉንም የዘመቻ ተሳታፊዎች ሰብስቦ ውይይቱን በመምራት ስለዘመቻው ውጤታማነት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና ስለቀጣይ አቅጣጫዎች መወያየት ተገቢ ነው፡፡
- የሪፖርት ፅሁፉን ተግባር በበላይነት መምራት፤ የዘመቻው ሂደትና ያጋጠሙ ችግሮች በሪፖርቱ ላይ መካተታቸውን መከታታል፤ተማሪዎች አዘውትረው ትምህርት ቤት እንዲገኙ የሚረዱ ስልቶችና ምክረ-ሀሳቦች ጭምር በሪፖርቱ ማካተት ይጠበቅበታል፡፡

የዘመቻ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

የዘመቻ ቡድኑ ለተማሪ ወላጆችና አሳዳጊዎች እንዲሁም ተባባሪዎች ዘመቻው በውጤታማነት እንዲጠናቀቅ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ላደረጉት ተሳትፎ ክብርና ምስጋና መሥጠት አለበት፡፡



ሞጁል 4:- ለህጻናት ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር

ለህጻናት ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር

ለህፃናት ምቹ የሆነ ትምህርት ቤት ለጉዳት የተጋለጡና በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙትን ጨምሮ ሁሉም ተማሪዎች የአካል ደህንነታቸው የተረጋገጠና ስነልቦናቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችና የመምህራን ደህንነት የተጠበቀባቸው ተቋማት መሆን አለባቸው፡፡ ተፈናቃዮችንና ስደተኞችን የሚያስተናግዱ ትምህርት ቤቶችም በተመሳሳይ ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲኖራቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

ለህፃናት ምቹ የሆኑ ትምህርት ቤቶች የሚከተሉት ጠቀሜታ ይኖሯቸዋል፡፡

- የትምህርት ውጤት ይሻሻል፡፡
- ተማሪዎች በተለይም ሴቶች አዘውትረው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይረዳሉ፡፡
- ለመማርና ለመስራት የሚተጉ ተማሪዎችና መምህራን ይፈጠራሉ፡፡

በዚህ ሞጁል ውስጥ ያለው ምንድን ነው?

ይህ ሞጁል ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ .

መምህራን እንዴት ለህፃናት ምቹ የሆኑ ክፍሎችን ያደራጃሉ?

- ከተማሪዎቻቸው ጋር አወንታዊ ግንኙነት ይፈጥራሉ፡፡
- ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች በትምህርታቸው እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡
- አሳታፊ የሆነ የማስተማር ስልት ይጠቀማሉ፡፡
- በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የትምህርት መርጃዎችን ያደራጃሉ፡፡
- ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

በመጀመሪያው ክፍል፣ በትምህርት ቤት መሻሻልና በሌሎች ስብሰባዎች ወቅት የወላጆች የመምህራንና የተማሪዎች ህብረትና የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ አባላት እንዴት ት/ቤቶችን ለህጻናት ምቹ ማድረግ እንዳለባቸው መገምገም የሚያስችል ቸክሊስት (Chick List) እናስተዋውቃለን፡፡

ቸክ ሊስቱ ራሳችን የምንመዝንበት አምስት ክፍሎች አሉት፡፡

አካቶት ትምህርት፣ ውጤታማና ጠቃሚ ትምህርት፣ ጤናማ ምቹና አስተማማኝ ደህንነት ያለው የትምህርት ቤት አካበቢ፤ ፆታን ያማከለ ትምህርት፣ ተማሪዎችን ወላጆችን, ማህበረሰቡንና ክበባትን ማሳተፍ ከነዚህም ሌላ ራስን ለመገምገም የሚያስችሉ ተጨማሪ ክፍሎችን ማካተት ይቻላል፡፡

በሁለተኛው የሞጁሉ ክፍል፣ ተፈናቃዮችና ስደተኞች ለሚያስተናግዱ ትምህርት ቤቶች የሚያግዙ ውስን ተግባራትን አካተናል፡፡ እነዚህ ተግባራት ተፈናቃዮችና ስደተኞች ተማሪዎች ደህንነትና ምቾት እንዲሰማቸውና በባከኑት የትምህርት ቀናት የቀረባቸውን ትምህርት ለማካካስ እንዲችሉ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ክፍል 1፡- ትምህርት ቤትን ለህጻናት ምቹ በሆነ የትምህርት አካባቢ ቸክሊስት መገምገም

የወላጆች፣የመምህራንና የተማሪዎች ህብረትና የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴዎች ትምህርት ቤቱ ለህፃናት ምቹ መሆኑን በተዘጋጀው ቸክ ሊስት ለመገምገምና ውጤቱን በድርጊት መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት ይችሉ ዘንድ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

ትምህርት ቤቱን በቸክሊስቱ መሰረት ለመገምገም የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ የሚሰራበትን መርሃ ግብር አዘጋጅ/ጂ፡፡ በመቀጠልም በትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴው ስብሰባ ለእያንዳንዱ ዘርፍ አምስት ንኡሳን ክፍሎችን አደራጅ/ጂ፡፡ (ለምሳሌ አካቶ ትምህርትወዘተ…) በያንዳንዱ ዘርፍ ስር ያሉትን ንዑሳን ክፍሎች

ለመተንተን ትምህርት ቤትህ/ሽ ለህጻናት ምቹ የመሆን ባህርያትን የሚያሟላ ከሆነ "**አዎ**" የሚል ምልክት አስቀምጥ/ጭ። ትምህርት ቤቱ ለህጻናት ምቹ የመሆን ባህርያትን የማያሟላ ከሆነ "**አይደለም**" የሚለውን ምልክት አስቀምጥ/ጭ። ተግባሩ በትምህርት ቤቱ ተፈጻሚ ካልሆነ "**ተግባራዊ ያልሆነ**" በሚለው ስር ምልክት አስቀምጥ/ጭ።

እያንዳንዱ ትንሽ ቡድን ውይይቱን ካጠናቀቀና ሳጥኖቹን በየዘርፋቸው ምልክት ካደረገ በኋላ ሁሉንም ወደ ትልቅ ቡድን በማምጣት በግኝቶቹ ዙሪያ ውይይት አድርጉ።

በትምህርት ቤቱ መሻሻል በሚኖርባቸው በቸክሊስቱ አንድ ወይም ሁለት ክፍሎች ላይ አትኩሮ ለመስራት የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በድርጊት መርሃ ግብሩ ላይ እንደመሰረት የሚያገለግሉ ነጥቦችን ማካተት ተገቢ ይሆናል።

የወላጆች፣ የመምህራንና የተማሪዎች ህብረት፣ የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባራት በየሩብ አመቱ በመፈተሽ የድርጊት መርሃ ግብሩን ዕድገትና መሰረቶች መገምገም ይኖርበታል። በትምህርት ዘመኑ መጨረሻ ደግሞ የተግባራት አፈጻጸም ያለበት ደረጃ ለወላጆች ለመምህራንና ለተማሪዎች ህብረት እንዲሁም ለትምህርት ቤቱ አመራር ሪፖርት ማድረግ እንደሚስፈልግ መዘንጋት የለበትም።

የተደረሰበትን መሻሻል ለማረጋገጥ፣ በአዲሱ የድርጊት መርሃ ግብር ላይ ትኩረት የሚደረግባቸውን ለመለየትና የቸክሊስቱን ሌሎች ክፍሎች ለመምረጥ ግለ ግምገማውን በተከታታይ አመታት ማካሄድ ያስፈልጋል። አመታት በተቆጠሩ ጊዜ የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ አዳዲስ አባላት ሊኖሩት ይገባል፡፤

ለህፃናት ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ ቼክ ሊስት

ለህፃናት ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ ባህርያት			
	አዎ	**አይደለም**	**ተግባራዊ ያልሆነ**
ክፍል 1: አካቶ ትምህርት			
ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍ			
ራሳቸውን ለማሻሻል የሚጥሩ ተማሪዎች የጥናት ጓደኛ እንዲኖራቸው ማድረግ			
መማር ማስተማሩ ተማሪዎችን መሰረት ያደረገ የዕውቀት ደረጃ፣ ዘር፣ ቋንቋ፣ ፆታን ያገለለ...መሆን የለበትም። ፡			
የያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት አቀባበል መሰረት ያደረገ ህፃናት ተኮር የማስተማር ዘዴ			
ክፍል 2: ውጤታማና ጠቃሚ የማስተማር ሂደት			
በቂ የሆነ የትምህርት ሃብት (ምሳሌ፡- የተማሪዎች መማሪያ መፃህፍት)			
በቀዳሚ ክፍሎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት መከናወን			

ለህፃናት ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ ባህርያት			
	አዎ	አይደለም	ተግባራዊ ያልሆነ
መምህራን፣ የተማሪዎችን ብቃትና ዕድገት ለመለካት ተከታታይ ምዘናን መጠቀም			
ክፍል 3: ጤናማ ምቹና በጤንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ			
ከዕድሜ ጋር የተገናዘበ የትምርት ቁሳቁስ መጠቀም			
የትምህርት ቤት ምድረ ግቢና መማሪያ ክፍሎች ንፁህና በአግባቡ የተደራጁ ናቸው::			
ከሁከት ነጻ የሆነ ስነምግባርና የአመራር ስልቶች (አካላዊ ቅጣት የሌለበት፣, ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ወይም በመምህሮች ፊት የማይቀጡበት፣ ከጩኸት ነጻ የሆነ)			
ንጹህ ውሃ			
በአጥር የተከለለ ምድረ ግቢ			
ሁሉንም ህጻናት ከግንዛቤ ማስገባት፣ እንደጤናና ምግብ ያሉ ትምህርታዊ ያልሆኑ የተማሪዎች ፍላጎቶችን ማካተት			
መምህራን ለተማሪዎች ያላቸው አቀባበል የሞቀ፣ መልካም፣ አበረታችና አስደሳች ነው::			
የተማሪዎች መብቶች ይከበራሉ::			
በጥባጭ ወይም ሁከተኛ ተማሪዎች በመቆጣጠር ማስተካከያ ይደረጋል			
የስነምግባር መርሆዎች ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ ናቸው::			
ክፍል 4: ፆታን ያማከለ አሰራር			
ለሴቶችና ለወንዶች የውሃ አቅርቦት ያላቸው የተለያዩ መጸዳጃ ክፍሎች ተደራጅተዋል::			
ብስለት ያለው ሃሳብ ለማመንጨትና ችግር ፈች ጥያቄዎችን ለመመለስ ለወንዶችና ለሴቶች እኩል ዕድል ይሰጣል::			
ወንዶችና ሴቶች ተግባራትን እንዲመሩ እኩል ዕድል አግኝተዋል::			

ለህፃናት ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ ባህርያት			
	አዎ	አይደለም	ተግባራዊ ያልሆነ
የትምህርት ቤቱ የመጫዎቻ ቦታ ለሁሉም ፆታዎች እኩል አገልግሎት ይሰጣል::			
ፆታዊ ትንኮሳ የለም::			
ክፍል 5: ተማሪዎችን ወላጆችን ማህበረሰቡንና ልዩ ልዩ ክበባትን ማሳተፍ			
ትምህርት ቤቱ በተማሪዎቹ አፈጻጸም ዙሪያ ለወላጆችና ላሳዳጊዎች መረጃ ይሰጣል::			
ወላጆችና አሳዳጊዎች ትምህርት ቤቱን በመጎብኘት በልዩ ሁኔታ ተሳትፎ ደርጋሉ::			
ትምህርት ቤቱ ውጤታማ የወላጆችና የትምህርት ቤት ግንኙነት እንዲኖር የሚያበረታታ ሲሆን ወላጆችና መምህራን ሃሳባቸው የሚደመጥበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል::			
የወላጅ፣ የመምህራንና የተማሪዎች ህብረት ንቁ እንቅስቃሴ ያደርጋል::			
የሥርአተጾታና የሴቶች ክበብ በንቃት ይንቀሳቀሳል::			

ክፍል 2:- ለተፈናቀሉና ለስደተኞች ተማሪዎች ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ስደተኞችና የሃገር ውስጥ ተፈናቃዮች የምታስተናግድ አገር ናት::

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከጀመሩ ሁለት ስደተኞች መካከል አንደኛው ብቻ የትምህርት ዕድል ያገኛል::
- የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ከጀመሩ አራት ስደተኞች መካከል አንደኛው ብቻ የትምህርት ዕድል ያገኛል::
- የከፍተኛ ትምህርት ከሚጀምሩ አንድ መቶ ስደተኞች መካከል አንደኛው ብቻ የከፍተኛ ትምህርት ወይም የሙያ ስልጠና ትምህርት ዕድል ያገኛል::

ስደተኞችና ተፈናቃይ ተማሪዎችን በትምህርት ቤቶችና በትምህርት ላይ ለማቆየት አካታችና ሳቢ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር ወሳኝ ተግባር ነው:: እንደተባቡሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR[1]) በርካታ ስደተኞችና ተፈናቃይ ህጻናት የትምህርት ዕድል አያገኙም:: የተፈናቀሉና ስደተኞች ህጻናት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንዲረጋጉና ጤናማ ህይወት እንዲመሩ ያስችላቸዋል::

ትምህርት ቤት የአዎንታዊ ስነ-ልቦናና የማህበራዊ ጤናማ ስሜት ድጋፍ ምንጭ ሊሆን ይገባል:: ከዚህም ሌላ የትምህርት ቤት ህይወት የወሲብ ብዝበዛን፣ አካላዊ ጥቃትና ሌሎች ጥቃቶችን ጨምሮ የህጻናትን ለችግሮች የመጋለጥ ሂደት ይቀንሳል:: ለተፈናቃይና ለስደተኞች ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ማግኘት ከአካባቢው

1 UNHCR. (2017). UNHCR report highlights education crisis for refugee children. Retrieved from http://www.unhcr.org/news/press/2017/9/59b6a3ec4/unhcr-report-highlights-education-crisis-refugee-children.html

ማህበረሰብ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲፈጠርና በሰላም ወደ ዘላቂ ህወታቸው እንዲመለሱ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ከተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ከቤተሰቦቻቸውም ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲፈጠር ዕድል ይሰጣል፡፡

መከናወን የሚገባው አንድ መሰረታዊ ተግባር ሁሉንም ስደተኞች፣ ተፈናቃዮች፣ የአካል ጉዳት ያለባቸውንና የጎዳና ተዳዳሪዎችን የሚስተናግድ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ማዘጋጀት ነው፡፡ ትምህርት ቤታችን ለተፈናቃዮችና ለስደተኞች ምቹ አካባቢ መሆኑን ለማረጋገጥ መምህራንና የወላጆች የመምህራንና የተማሪዎች ህብረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የአሰራር ደረጃዎች መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ስደተኞች፣ ተፈናቃዮች፣ አርብቶ አደሮችና የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት ድንገተኛ ሁኔታው እንደተከሰተ ብዙ ሳይቆይ የትምህርት ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ በዘርፉ ከሚሰሩ አካላት ይጠበቃል፡፡

የማካካሻና የሽግግር ክፍሎችን ማደራጀት

ስደተኛ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ስለተለዩ፣ የህሊና እረፍት ስለማይኖራቸውና የስርአተ ትምህርቱ አቀራረብ ከለመዱት ሊለይባቸው ስለሚችል በትምህርታቸው ላይ ክፍተት ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም ርእሳነ -መምህራን መምህራንን በማስተባበር በየትምህርት ቤቶቻቸው በልዩ ልዩ ምክንያቶች የባከኑ ክፍለ-ጊዜያት የማካካሻና የሽግግር ፕሮግራሞችን በማደራጀት ተማሪዎች አዲሱን ትምህርት ቤት እንዲለምዱትና ውጤታማ እንዲሆኑ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የመዝናኛ ተግባራትን ማቅረብ

ጨዋታ፣ መዝሙር፣ ባህላዊ ጨዋታ፣ ስፖርት፣ ሥነጥበብ፣ ተውኔትና ተመሳሳይ የመዝናኛ ተግባራት በጭንቀትና በጉዳት ውስጥ ያሉ ህፃና ትእንዲረጋጉ ይረዳሉ፡፡

ማህበራዊ ስሜትን የሚነኩ የትምህርት ተግባራት ማቅረብ

ማህበራዊ ስሜትን የሚነኩ የትምህርት ተግባራትን የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚማሩባቸው ክፍሎች መተግበር ይህን ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ በሞጁል 6 የሰፈረውን ይመልከቱ፡፡



ሞጁል 5፡ ግብረ-ገብነት (Positive Discipline) እና የትምህርት ቤት ህግና ደንብ

ግብረ-ገብነት (Positive Discipline) እና የትምህርት ቤት ህግና ደንብ

ግብረ-ገብነት (Positive Discipline) እና የትምህርት ቤት ህግና ደንብ የትምህርት ቤቶች ሁለንተናዊ ገፅታ ተማሪዎች እንዴትና ምን መማር እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል። ሰላማዊ፣ መልካም ስም ያላቸውና ከሁከት ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶችና መማሪያ ክፍሎች ህፃናት በጉጉት እንዲማሩና ዕምቅ ተሰጥኦአቸውን እንዲጠቀሙ ይረዳሉ።

አካላዊ ቅጣትን መጠቀም፣ ህፃናትን በማዋረድ ማሳቀቅና ሥነ-ልቦናዊ ጫና መፍጠር በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። እነዚህ ተፅዕኖዎች ተማሪዎች አዘውትረው ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጡ፣ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ፣ ጠብጫሪ እንዲሆኑና በትምህርታቸው እንዲደክሙ ያደርጋሉ።

አወንታዊ የትምህርት አካባቢ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ግን ተማሪዎች የትምህርት ጉጉት ያላቸው፣ ትምህርታቸውን አዘውትረው የሚከታተሉና በሰበብ አስባቡ የማያቋርጡ ያደርጓቸዋል። እንደዚህ ባሉ ትምህርት ቤቶች፡ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ባህርያት ይስተዋላሉ።

ማንኛውም ተማሪ ደህንነት የሚሰማው፣ የፈጠራ ባለቤትና ሃሳብ አመንጭ ይሆናል።	ማንኛውም ተማሪ ተሰጥኦውን ተግባራዊ የማድረግ አማራጭ ይኖረዋል።	ሴቶችናወንዶች እኩል ከበሬታና ተሳትፎ ይኖራቸዋል
ትምህርት ቤቱ ማንኛውንም ተማሪ ተሳታፊ እንዲሆን ያበረታታል።	የማንኛውም ተማሪ አመለካከትና ሃሳብ ዋጋ ይሰጠዋል።	ትምህርት ቤቱ ደህንነቱ የተረጋገጠና ለህፃናት ምቹ መሆን ይገባዋል።

የዚህ ሞጁል አላማዎች ምንድን ናቸው?

በዚህ ሞጁል ትምህርት ቤቶች ተቋማቸውን አወንታዊ የትምህርት አካባቢ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ሁለት ለውጦችን እና ለውጦቹን ለማስተዋወቅ ሊጠቀሟቸው የሚችሉ ርምጃዎችን እናስተዋውቃለን። ሁለቱ ለውጦችም ቀጥሎ ቀርበዋል፤

1. የግብረ-ገብነትን ጽንሰ ሃሳብ እንዲገነዘቡ ማድረግ፤
2. የትምህርት ቤቱን ህግና ደንብ ተግባራዊ ማድረግ እነዚህ ሁለት ነገሮች ትምህርት ቤቱን ለመለወጥ ወሳኝ ተግባራት ናቸው። እነዚህን በመተግበር ተማሪዎች በራሳቸው የሚተማመኑና ደህንነቱ የተጠበቀና ምቹና ተስማሚ ማድረግ እንችላለን።

የሚያስፈልጉን ግብአቶች ምንድን ናቸው?

ከግብአት አኳያ አስፈላጊ የሆነው መሰረታዊ ነገር ተማሪዎች ትምህርታቸውን አዘውትረው እንዲከታተሉና እንዲማሩ የሚያነቃቃ ቁርጠኝነትና ፍላጎት ማሳደር መቻል ነው፡፡ የተለየ ግብአትና በጀት ከዚህ ቀጥሎ ሊመጣ የሚያስችል ነው፡፡

ይህንን ተግባር የሚያከናውነው ማነው? ትምህርትቤት አመራሮች፡- አወንታዊ የትምህርት አካባቢን ለመፍጠርና የትምህርት ቤት የሥነ ምግባር መመሪያን በጥሩ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው አመራሮች ያስፈልጋሉ፡፡ የዚህም አላማ ሁሉም ተማሪ በሚከናወነው ተግባር እምነት እንዲያድርበትና ባለራዕይ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ ለውጥ ምንም እንኳ አወንታዊ ቢሆን አስቸጋሪ ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት የመጀመሪያው ተግባር የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሱትንና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ማከናወን ነው፡፡ አላማውም በአካታች ባህል ላይ የተመሰረተውን ፕሮጀክትና ለውጥን ለመለካትና ለማብሰር የሚያስችሉ መሳሪያዎችን መጠቀም ነው፡፡ ተግባሮች በትምህርት ቤቱ ባልደረቦች፣ በአመራሩ፣ በወተመህ፣ በማህበረሰቡና በተማሪዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ ወተመህን እና የተለያዩ የትምህርት ቤት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን መጠቀም ለውጦችን ለማስተዋወቅ ተገቢ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡

የጥሩ አመራር መገለጫ ባህርያት ምንምን ናቸው?

- ግልጽ የሆነና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን
- ከተማሪዎች ከመምህራን ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጥሩ ግንኙነት የሚፈጥረ
- ከእያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ የሚረዳ
- ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ የሚውቅ
- የጥሩ አስተዳደር ዕድገቶችን የሚከታተልና፤ አፈጻጸሞችን የሚያደንቅ

1. ግብረ-ገብነት ምንድን ነው?

የግብረ-ገብነትግብ ተማሪዎች የራሳቸውን ሥነ-ምግባር እንዲገነዘቡ ለምርጫዎቻቸው ተገዥ እንዲሆኑና ራሳቸውንና ሌሎችንም እንዲያከብሩ ማስቻል ነው፡፡ ጥሩና መጥፎ ሥነ-ምግባር እንጅ መጥፎ ተማሪዎች የሉም፡፡ አዎንታዊ ሥነ -ምግባር ከቅጣት ይለያል፡፡ ምክንያቱም ቅጣት የተማሪዎችን ሥነ-ምግባር ለመቆጣጠር የሚውል ሲሆን ግብረ-ገብነት ግን የተማሪዎችን ሥነ-ምግባር ለመቅረጽ የሚውል ነው፡፡ ግብረ-ገብነት ያልተገባ ባህሪን ማረም ሳይሆን መልካምሥነ-ምግባርን ማበረታታትና ምሳሌ መሆን ነው፡፡

የግብረ-ገብነት ጠቀሜታ



መምህራን ግብረ-ገብነትን በክፍላቸው እንዴት ተግባራዊ ያደርጋሉ?

የኢትዮጵያ ት/ቤቶች የክፍል ኃላፊ መምህር አላቸው። መልካም ሥነ-ምግባር መላበስን በተመለከተ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከክፍል ኃላፊ መምህር ጋር በሚደረግ ውይይት ግንዛቤ ይጨበጥበታል። የክፍል ኃላፊ መምህራን የክፍል ተማሪዎቻቸውን ዕለት በዕለት የሚያገኙ ሲሆን ክፍሉን የመምራት ሃላፊነት አላቸው። የክፍል ኃላፊ መምህራን የየዕለቱ ትምህርት በሰላም እንዲካሄድ የሚመክሩ ሲሆን የየትምህርት አይነቱ መምህራን ደግሞ በየክፍለ ጊዜያቸው ጥሩ ሥነ-ምግባር እንዲኖር ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ።

ተግባር 1ሀ: የግብረ-ገብነት ሥልቶችን ማካተት

ሁሉም መምህራን ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚችሉ መልካም ባህሪን ለማጉላት የሚረዱ የግብረ-ገብነት ስልቶች አሉ። ከነዚህም ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተጠቃሾች ናቸው።

- በአመቱ መጀመሪያ ላይ የክፍል መተዳደሪያ ደንቦችን ከተማሪዎች ጋር በጋራ ማዘጋጀት ወጥ ለሆኑ የጋራ ፍላጎቶች ትኩረት መስጠት፤
- በያንዳንዱ ክፍል መጀመሪያ ግቦችን ማስቀመጥ፤ ተገቢና ጥሩ ሥነ-ምግባርን ማበረታታት፤ በግጭት ጊዜ ገለልተኛ አቋም መያዝና ላልተገባ ባህሪ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን መለየት፤
- ለለተማሪዎች ጥሩ ሥነ-ምግባር ዕውቅና ለመስጠት ማበረታቻ መጠቀም፤ ተገቢ ባህርያትን ሁሉም ተማሪዎች እንዲላበሱ ማድረግና በምሳሌ ማስተማር፤

- ለተማሪዎች የተለያዩ አማራጮችን ማቅረብ፤
- የተማሪዎችን ሃሳብ በጽሞና ማዳመጥና መደገፍ፤

ተማሪዎችና መምህራን መጥፎ ባህሪ ምን እንደሆነና ባልተገባ ባህርይ የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ግብረገብነት ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው ያልተገባ ባህሪ ባጋጠመ ጊዜ ሁሉ ተገቢ ማስተካከያ ወጥ በሆነ ሁኔታ ተግባራዊ ሲደረግ ነው። በመጨረሻም፣ የክፍል መተዳደሪያ ደንቦችንና ተገቢ ግምቶችን በጠብ አጫሪ መልኩ ሳይሆን በተገቢ አቀራረብ በመተግበር ተማሪዎች መምህራንን እንደ ምሳሌ በመውሰድ ይማራሉ።

እያንዳንዱ ተማሪ ከሥነ-ምግባርና ከግላዊ ባህሪው ጋር የተገናዘበ ዕቅድ መሥጠት፤

ተግባር 1ለ: የመማሪያ ክፍል ደንቦችን ማዘጋጀት

መምህራን በትምርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከክፍል ተማሪዎች ጋር በመሆን የክፍል መተዳደሪያ ደንቦችን ዘርዝሮ መለየትና ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ተማሪዎች ራሳቸው በተሳተፉበት ሂደት ደንቦች መዘጋጀታቸውና ስለደንቦቹ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲረዱ ያደርጋል። ከዚህ ቀጥሎ የክፍል መተዳደሪያ ደንቦችን የማመንጨትና የማዘጋጀት ሂደት ምን እንደሚመስል ቀርቧል።

ትምህርት በሚጀመርበት የመጀመሪያ ሳምንት መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን የክፍል መተዳደሪያ ደንቦችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ከ8-10 የሚደርሱ ደንቦችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ህግ እንዲያወጣ ከተደረገ በኋላ በክፍል ውስጥ በጋራ እንዲነጋገሩባቸው ማድረግ ተገቢ ነው።

ተማሪዎችና መምህራን በጋራ የክፍል መተዳደሪያ ረቂቅ ደንቦችን ካዘጋጁ በኋላ ተማሪዎች የትኖቹ ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንደሚፈልጉ ድምፅ እንዲሰጡበት ማድረግ ጠቃሚ ነው። ይበልጥ ተፈላጊነትያላቸውን ከ 8-10 የሚደርሱ ደንቦችን በመምረጥ ደንቦቹ አስፈላጊ የሆኑበትን ምክንያትና ተማሪዎች ለምን ማክበር እንዳለባቸው መግለጽ የክፍል ሃላፊ መምህራን ተግባር ይሆናል።

የክፍል ውስጥ መተዳደሪያ ደንቦች ምሳሌዎች

- ከመናገር በፊት እጅን ማውጣት፤
- ሁልጊዜም በክፍል ውስጥ በሰአቱ መገኘት፤
- ለመምህራንና ለክፍል ጓደኞች በትህትና መናገር፤
- ሁልጊዜም ወደ ክፍል በቂ ዝግጅት አድርጎ መምጣት፤
- አመሰግናለሁ ማለትን መልመድ እና
- ሌሎች ሲናገሩ በጽሞና ማዳመጥ።

የክፍል መተዳደሪያ ደንቦች ከተዘጋጁ በኋላ ተማሪዎች ሁልጊዜም ሊገነዘቧቸውና ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ላይ በወረቀት ተጽፎ በክፍል ውስጥ በመለጠፍ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል። ደንቦቹን መለጠፉ ተማሪዎችና መምህራን አዘውትረው እንዲገነዘቡት ያግዛል።

ክዋኔ 1ሐ: ደንቦችን ማስከበር

ተማሪዎች ደንቦችን ሲጥሱ ለራሳቸውና ለጓደኞቻቸው ደህንነት ሲባል ጥሩ ሥነ-ምግባር እንዲላበሱ መምህራን አግባብ ያለው ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል። ደንቦችን ለማደራጀት አራት መሰረታዊ መርሆዎች አሉ። ደንቦቹም ቀጥሎ የቀረቡትን ያሟሉ መሆን አለባቸው።

ሀ - ያልተገባ ባህሪን ለመቆጣጠር ማስቻል
ለ - ከጥፋቱ ጋር የተመጣጠ መሆን
ሐ - ተማሪዎችን በማሸማቀቅ ሳይሆን ባህሪን በማረም ላይ ማተኮር
መ - ቅጣት ላይ ሳይሆን (ከጥፋቶች መማር) ወደ በጎ ባህሪ መመለስ ላይ ማተኮር

2. መተዳሪያ ደንቦች

ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መተዳደሪያ ደንቦች አሏቸው፡፡ መተዳደሪያ ደንብ መርሆዎችን፤ ህጎችንና እሴቶችን የያዘ የትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ ምን አይነት ባህሪ ማሳየት እንዳለባቸው የሚያመላክቱ መለኪያዎችን የሚጠብቁ ባህርያትን የሚይዝ በተለያየ መንገድ የሚደራጅ ፅሁፍ ነው፡፡ መተዳደሪያ ደንቡ ለሥነ-ምግባራዊ ባህርያትና እሴቶች መመዘኛዎች ይኖሩታል፡፡ ደንቡ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ህጎችና መመሪያዎች የሚጥስ ምን ሊሆን እንደሚችል ማመላከት ይጠበቅበታል፡፡

የትምህርት ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዴት እናስከብራለን?

ተግባር 2ሀ: ግልጽ የማስተካከያ ርምጃዎችን መቅረፅ

ከሁሉ በፊት አመራሩና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ህግን በመጣስና በቅጣት መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ቅጣት ህጋዊ በሆነ መልኩ ከስምምነት ላይ የተደረሰበት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የሰፈሩትን ህጎች መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ቢጥሱ የሚወሰድ ርምጃ ነው፡፡ በሌላ በኩል ህግን መጣስ ማለት መምህራንና የአስተዳር ሰራተኞች በተማሪዎችና በሌሎች ሰዎች ላይ ያልተገባ ባህሪ በማሳየት ጉዳት እንደማድረስ ያስቆጥራል፡፡

የትምህርት ቤቱ መሪና አመራሮች የመተዳዳሪያ ደንቡ ሲጣስ የተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ግልጽ የሆኑ የማስተካከያ ርምጃዎችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ሂደት ትምህርት ቤቱንና ተማሪዎችን ከጉዳት ለመጠበቅና ደህንነትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

ህግ መጣስ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- አካላዊ ጉዳት
- ፆታዊ ትንኮሳ
- በንግግር ማሸማቀቅ
- ተማሪዎችን ማስፈራራት
- መምህራን በክፍል ውስጥ ተገኝተው ያለማስተማር- ዘግይቶ መግባት ወይም ቀድሞ መውጣት
- ህፃናትን እኩል አለማስተናገድ
- ብልሹ አሰራር ወይም የሌሎችን ንብረት መቀማት

ተግባር 2ለ: የመተዳደሪያ ደንቡ በትምህርት ቤቱና በህብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ እንዲፈጥር መደገፍና ማስተዋወቅ

በትምህርት ቤቱ ምን አይነት ሥነ-ምግባር ተቀባይነት እንዳለው ከማህበረሰቡና ከትምህርት ቤቱ ባልደረቦች ድጋፍ በማግኘት መተዳደሪያ ደንቡን ማበልጸግ ያስፈልጋል:: ሁሉም መምህራንና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት የመተዳሪያ ደንቡን ቅጅ እንዲያገኙና ይንኑም በህጋዊ አሰራር በደብዳቤ ፈርመው ለደንቡ ተገዥ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ መልካም ተሞክሮ ነው:: ምሳሌ የሚሆን ደብዳቤ ከዚህ በታች ተሰጥቷል::

የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት በተገኙበት ስብሰባ ላይ የመተዳደሪያ ደንቡን ማስተዋወቅና ለአወንታዊ ባህርያት ዕውቅና መስጠት ያስፈልጋል:: እውቅና መስጠት የጥሩሥነ-ምግባር ባህል እንዲዳብር ያግዛል::

የትምህርት ቤቱን መተዳሪያ ደንብ መቀበልና ማክበር

የመምህራንና የትምህርት ቤቱን ሃላፊነቶች የያዘ መተዳደሪያ ደንብ ቅጅ መረከቤን አረጋግጣለሁ:: በጥልቀት ባነበብኩት መሰረት መስማማቴን እገልጻለሁ:: በመተዳሪያ ደንቡ መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎችና የአሰራር ሥርአት ላይ ያለኝን ስምምነት አረጋግጣለሁ::

በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ያልተገነዘብኩት ምንም አይነት ፖሊሲና ምክረ-ሃሳብ ቢኖር ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ጠይቄ ለመረዳት ተስማምቻለሁ::

እባክዎን ፊርማዎን በማስቀመጥና የክንውን ቀኑን በመግለጽ ይህን ማረጋገጫ ለርዕሰ-መምህሩ ይመልሱ::

የሰራተኛው ስም ______________________________

ፊርማ ______________________

/ ______________________ቀን



ሞጁል 6:- የማህበራዊ ስሜት ትምህርት
(Social - Emotional Learning)

የማህበራዊ ስሜት ትምህርት (Social - Emotional Learning)

የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ህፃናትና ጎልማሶች ስሜቶቻቸውን ለመገንዘብና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዕውቀት፣ አመለካከትና ክህሎት ለማግኘትና በውጤታማነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሂደት ነው።

ትምህርቱ በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት፣ ሥሜቶችና የግለሰቦች አዕምሮአዊ ክሂሎች በማዳበር ህይወታቸው የተቃና ይሆን ዘንድ ይረዳል። በአንዳንድ አገሮች የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርት ልክ እንደ ህይወት ክህሎት ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት አይነት በትምህርት ቤቶች ይሰጣል።

የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርት ለህጻናት አዕምሮአዊ ዕድገት በሚረዳ የአጠቃላይ ትምህርት አቀራረብ ላይ ተመስርቶ በት/ቤት ማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ በተማሪዎች የውይይት ጊዜ፣ በመማሪያ ክፍሎች የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርት ቋንቋና ተግባራትን በማካተት ከትምህርት ማህበረሰብ ጋር ተዋህዶ ተግባራዊ ይደረጋል።

በትምህርት ቤት የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርትን መደገፍ ለምን አስፈለገ?

የማህበራዊ ሥነ-ልቦና ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ በየዕለቱ ስለሚያጋጥሟቸው ጉዳዮች ርስበርስ ለመግባባትና የጋራ ሃሳቦች ለመገንባት እንዲችሉ ይረዳል። የማህበራዊ ሥነ-ልቦና ትምህርት ተግባራዊ የሆነው በድህነት የሚኖሩ፣ የተፈናቀሉና ሁከት የደረሰባቸው ህጻናት ስሜታዊ ምላሽ በመቆጣጠር፣ ከሌሎች ጋር እንዲግባቡ በመርዳት ጭንቀትና ችግሮችን ለመቋቋም እንዲችሉ በማድረግ የሚደርስባቸውን ስቃይና መከራ ለመቀነስ ነው። ትምህርቱ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ትምህርታዊ አፈፃፀም እንዲሻሻል ይረዳል። ይበልጥ ለመረዳት ከዚህ በታች በክቡ ውስጥ ያሉትን ቁምነገሮች ለማገናዘብ ይሞክሩ።



የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ልምዶች የመምህራንን ስነ-ልቦናዊ ጤናና ደህንነት ለማሻሻልም ይረዳሉ። የተማሪዎችን ባህሪና ደህንነት በማሻሻል መምህራን ብዙ ጊዜ ደስተኛ እንደሆኑ ይበልጥ የተደራጁና ምላሽ ሰጭ መሆን እንደቻሉና የተማሪዎችን ችግሮች እንደቀነሱ ይናገራሉ።

የማህበራዊ ስሜት ትምህርት አምስት ብቃቶች (competencies) ወይም ዘርፎች ይዟል። **በትምህርት መስክ ተግባራዊ የሚደረጉ** አምስቱ የማህበራዊ ስሜት ርዕሰ ጉዳዮች በካሴል (Casel) እንደተገለጹት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

1. የራስ ግንዛቤ
2. ራስን ማስተዳደር
3. ማህበራዊግንዛቤ
4. የግንኙነት ክህሎት
5. ሃላፊነት የተሞላበት ዉሳኔ መስጠት ናቸው።

መምህራን አምስቱን የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ብቃቶች ወይም ርዕሰ ጉዳዮች በትምህርት ዕቅዳቸውና በክፍል ውስጥ በማስተማር ስራቸው ላይ እንዴት ማካተት እንዳለባቸውና የእያንዳንዱ ዘርፍ በተማሪዎች ዘንድ የሚያመጣው አዎንታዊ ውጤት ከዚህ በታች እንዲቀርብ ተደርጓል፡

በዚህ ሞጁል የቀረቡት የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ብቃቶች እንዲያሳዩ የታሰበው፤

- የተማሪዎችን አዕምሮአዊ ችሎታዎች በመገንባት በትምህርት ቤትና በሙያ የተሻለ ውጤት እንዲኖራቸው ማስቻል፤
- የራስ ግንዛቤ መገንባት ይችሉ ዘንድ የተማሪዎችን ስሜታዊ ግንዛቤና ችሎታ ማስፋፋት፤
- በክፍል ውስጥ ጠንካራ አወንታዊ ግንኙነት እንዲገነቡና በትምህርት ቤታቸው ውስጥና በአካባቢያቸው አሉታዊ ግንኙነቶችን እንዲያስወግዱ የተማሪዎችን የርስበርስ ግንኙነትና ክሂሎችን ማሻሻል፤
- ተማሪዎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለአዎንታዊ ውጤት ተግተው እንዲሰሩ ችግርን መቋቋምንና የታቀዱ ግቦችን ተግባራዊ የማድረግ ልምድን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይገኙበታል።

የማህበራዊ ሥነ-ልቦና ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ 1: የራስ ግንዛቤ

የራስ ግንዛቤ ማለት የራሳችን የሆኑትን ስሜትና አስተሳሰቦች በትክክል የመገንዘብ ችሎታ እንዲሁም እነዚህ እንዴት ባህሪያችን ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድሩ መረዳት ነው። .

- በራስ ግንዛቤ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፤
- የራሳቸውን ስሜቶች በትክክል ያስቀምጣሉ፤
- ስሜቶች ጊዚያዊና ተለዋዋጭ መሆናቸውን ይገነዘባሉ፤
- ስሜቶች ባህሪያቸውን ሊጎዱ ወይም ሊያቃውሱ እንደሚችሉ ይረዳሉ፤
- ባህርይ በስሜቶች ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይገነዘባሉ፤
- ስሜቶች አካላዊ ተፅዕኖ እንዳላቸው ይረዳሉ።

ተማሪዎችን ስለራስ ግንዛቤ ለማስተማር መምህራን በክፍላቸው ውስጥ ምን ሊያደርጉይችላሉ?

ተማሪዎች ስለስሜታቸውና መንፈሳቸው እንዲናገሩ ለመርዳት ከዕድሜ ጋር የተገናዘበ ቃላት መስጠት	ተማሪዎች መንፈሶቻቸውን /ስሜቶቻቸውን ለመግለጽ የራሳቸውን ድርጊት በቃላትና በስዕል እንዲፈጥሩ ማስቻል	ስሜቶችን ለማመልከት በአካላዊና ስሜታዊ ምልክቶች ላይ ውይይት ማድረግ
ተማሪዎች ስሜታቸውን ለማሻሻል ሊያከናዉኗቸው የሚችሉ ተግባራት ራሳቸው እንዲናገሩ አድርጉ	ተማሪዎች የሚሉትን በፅሞና ማዳመጥና ስለስሜታቸው ባዳመጣችሁት ላይ የተሰማችሁን መግለፅ	

የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ 2፡- ራስን ማስተዳደር

ራስን ማስተዳደር ማለት የራሳችን ስሜቶች፣ ዕሳቤዎችና ባህርያት የመቆጣጠር ችሎታ ነው። ተማሪዎች ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ።

- ስሜታዊነትን በአግባቡ መከታተልና መቆጣጠር
- የስሜቶች ግንዛቤን በመጠቀም የራሳቸውን የውሳኔ አሰጣጥ ማጎልበት
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ራሳቸውን ማነቃቃት፤
- ጭንቀትና ስጋትን በሚገባ መቋቋምን መልመድ፤
- ራስን መቆጣጠርን መለማመድ
- በተገቢው መንገድ ስሜቶችን መግለፅ

መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ራስን ስለ ማስተዳደር ለማስተማር ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?



ርዕሰ ጉዳይ 3 ፦ ማህበራዊ ግንዛቤ

ማህበራዊ ግንዛቤ የራሳችን ግላዊ እይታ ከሌሎች ጋር አገናዝቦ (የሰውን ጉዳይ እንደ ራስ አድርጎ ዋጋ መስጠት) የመጠቀም ችሎታ ነው።

- ማህበራዊ ግንዛቤን በመጠቀም ተማሪዎች ራሳቸውን በሌሎች ሰዎች ተቀባይነት ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ይችላሉ፤
- የሌሎች ሰዎችን አመለካከት መገንዘብ፤
- የሌሎች ሰዎችን ስሜትና አስተሳሰብ እንዲሁም ለምን እንደዚያ እንዳሰቡ ለመረዳት መሞከር።

መምህራን በክፍላቸው ውስጥ ተማሪዎችን ስለማህበራዊ ግንዛቤ ለማስተማር ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

- ስዕል በማሳየት ወይም ተማሪዎች የፊት ገጽታቸውን እንዲያሳዩ በማድረግ ሌሎች ስላዩት ነገር ምን እንደተሰማቸው ለይ/ዩ፤
- ለተማሪዎች መጽሃፍ በማንበብ የተለያዩ ገጸ-ባህርያት ስለሚያስቡትና ስለሚሰማቸው ሁኔታ ጥያቄዎችን አቅርብ/ አቅርቢላቸው፤
- ተማሪዎች በታሪኩ ውስጥ የትኞቹ ቃላት ሃሳብና ስሜቶቹን ለመረዳት እንዳገዟቸው እንዲለዩ አድርግ/ጊ፤
- ተማሪዎች እንዴት እንደተሰማቸው ጥያቄ አቅርብ/ አቅርቢላቸው።

ከዚህ ቀጥሎ ጥቂት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ "አዲስ ጓደኛ ስትይዝ ምን ተሰማህ/ሽ?" ወይም "ዛሬ ወደ ትምህርት ቤት በመምጣትህ ምን ተሰማህ/ሽ?"

የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ርዕሰ-ጉዳይ 4: የግንኙነት ክሂሎች

የግንኙነት ክሂሎችን ማጠናከር ጤናማና የሚያበረታታ ግንኙነት ለመመስረትና ዘላቂ ለማድረግ ያግዛል፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች ከቤተሰባችን፣ ከጓደኞቻችን፣ ከእኩዮቻችን ወይም ከእንግዶች ጋር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የግንኙነት ክሂሎችን በማዳበር የሚከተሉትን መፈጸምይችላሉ፡፡

- ከሌሎች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት ይመሰርታሉ፡፡
- ምኞትና ፍላጎታቸውን ያካፍላሉ፡፡
- አድናቆታቸውን ይገልጻሉ፡፡
- ምክርና ድጋፍ ይሰጣሉ፤ ይቀበላሉ፡፡
- በቡድን እንዴት መስራት እንደሚቻል ይማራሉ፡፡
- ለቡድን ግቦች መሳካት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ለሌሎች ሰዎች ነጻነት ዕውቅና ይሰጣሉ፤ያከብራሉ፡፡
- በተራቸው ይጠቀማሉ፤ በጎነትን ያሳያሉ፤ ያካፍላሉ፡፡
- ለሌሎች ይቅርታ ማድረግን ያሳያሉ፡፡

ቀጣይነት ባለው የማስተማር ተግባሮች **መምህራን የሚከተሉትን ስልቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡**	ተማሪዎች የተቀመጡ ገደቦችን ሲያከብሩ ሽልማት መስጠት	**ጥቂት ምሳሌዎች**: - ከሌላ ተማሪ ጋር እየተነጋገርኩ በነበረበት ጊዜ በትዕግስት ስለጠበቅሽኝ አመሰግናለሁ፡፡ "እጃችሁን እያወጣችሁ በመናገራችሁ አመሰግናለሁ፡፡ "
	ተማሪዎች ግጭቶችን በሚፈቱበት ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍ ማድረግ	
	ድጋፍን በበጎ በመስጠታቸውና በመቀበላቸው ለተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ መስጠት	
	ተማሪዎች በትናንሽ ቡድን ተደራጅተው እንዲሰሩ ዕድል መስጠት	

የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ 5:- ሃላፊነት የተሳበሰ ውሳኔ አሰጣጥ

በሃላፊነት ስሜት የሚከናወን ውሳኔ አሰጣጥ ሊያስከትል ስለሚችለው ውጤት ማሰብ ጠቃሚ አሰራር ነው:: በውሳኔ አሰጣጥ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማከናወን ይችላሉ::

- ሥነ-ምግባር ስለተላበሰ ባህርይ ጠቃሚነት ዕዉቅና ይሰጣሉ፤ይረዳሉ::
- ቅንነት፣ እውነተኛነትና ተጠያቂነትን ለማጎልበት የራስ የሆነን ዕሴት ይለያሉ፤ያበለጽጋሉ:: :
- ለራሳችሁ እንክብካቤ እንዲደረግላችሁ የምትፈልጉትን ያህል ለሌሎችም እንክብካቤ ያድርጉ::

ተማሪዎችን ስለራስግንዛቤ ለማስተማር መምህራን በክፍላቸው ውስጥ ምን ማድረግ ይችላሉ?

ሃላፊነትንና ተዛማጅ ቃላትን አብራራ/ሪ (ደህንነት፣ እሴቶች፣ እውነተኛ፣ ሥነ-ምግባራዊ) ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት በሚረዱ የአሰራር ደረጃዎች ላይ ተማሪዎች ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ ሁሉ ድጋፍ አድርግ/ጊ::

በምሳሌዎች ተመራ/ሪ፤እንዲሁም ጥሩ ውሳኔ አሰጣጥን ተለማመድ/ጅ::

ርዕሳነ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች፣ መምህራን የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርትን በትምህርት ቤቶች ለማስተዋዎቅ እንዲችሉ ምንድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ ?

በተማሪዎች የራስ ግንዛቤ ፣ራስን ማስተዳደር፣ማህበራዊ ግንዛቤ፣ የግንኙነት ክህሎትና ሃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ ግንባታ ላይ መምህራንን በክፍል ውስጥ መከታተል

መምህራን የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርት ግቦችን በማሳካት ላይ የማስተማርና የማማከር ችሎታቸውን ለማዳበር እንዲችሉ ማበረታታት

ለትምህርት ቤቱና ለመምህራን የአፈጻጸም ግብና አላማዎች ማዘጋጀትና መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝ

በተማሪዎች የራስ ግንዛቤና የተዛማጅ እውቀትና ክህሎት ላይ ተማሪዎች ባሳዩት እድገት ከወላጆችና ከማህበረሰቡ መሪዎች ጋር በመቀራረብ መስራት

የጨዋታ ባንክ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ሶስት ጨዋታዎች የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ክህሎት በወጣት ህጻናት ዘንድ ለማስረጽ በአለም አቀፍ ከጉዳት ጠባቂ ኮሚቴ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ መምህራን እነዚህን ሶስት ጨዋታዎች የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ክሂሎችን እንዲገነዘና ስደተኞችና ተፈናቃይ ህጻናት በክፍል ውስጥ አንድነት እንዲፈጥሩ ለማስተዋወቅ እንዲጠቀሙበት እንመክራለን፡፡

ጨዋታ 1: እኔና አንተ

ግብ: ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጓደኝነት ይመሰርታሉ፤ አንዱ የሌላውን ስም ለይቶ ያውቃል፡፡

ጊዜ፡ 30 ደቂቃ

ቦታ: እያንዳንዳቸው አንድ ትልቅ ክብ ሰርተው ጥቂቶቹ በክቡ ውስጥ ይቆማሉ፡፡

የአጨዋወት ደንብ: ህጻናትን በትልቁ ክብ ውስጥ እንዲቆሙ ማድረግ፤ መምህሩ/ሯ በክቡ ውስጥ ይቀላቀላሉ፡፡

ማለማመድ: ተማሪዎች አንዱ ከሌላው መነካካታቸው ተገቢ ካልሆነ፣ ለምልክት አድራጊው/ዋ ህጻናት ላይ ምልክት ማድረግ ይችል ዘንድ ትልቅ ስህተት አመልካች ወረቀት ስጠው/ስጭው፡

የጨዋታው አካሄድ

አንድ ፈቃደኛ በክቡ ውስጥ እንዲቆም አድርግ/ጊ — እሱ ወይም እሷ ምልክት አድራጊ ይሆናሉ፡፡

ጨዋታውን ለመጀመር ከክቡ አንድ ህጻን ምረጥ(ጭ) (ለምሳሌ፣ ፋጡማ) እሷም “ፋጡማ ትላለች- ለሳሙኤል”፣ ጣቷ ወደ ሌላ ህፃን እያመለከተ፡፡ (በዚህም ለምሳሌ - ከበደ)፡፡ ስሙ ሁለተኛ ሆኖ የተጠራው (በዚህ ምሳሌ ውስጥ-ከበደ) ጨዋታውን ሳሙኤል በማለት ይቀጥላል፡፡ “ሳሙኤል ለህይወት”፣ ጣቱን ወደ ሌላ ህፃን እያመለከተ (በዚህ ምሳሌ፣ ህይወት)፡፡ ይህ ሁኔታ ሲቀጥል ምልክት አድራጊው በንቃት መቆምና በጽሞና ማዳመጥ ይኖርበታል፡፡ እሷ ወይም እሱ የመጀመሪያው ስም ከተጠራ በኋላና ሁለተኛው ስም ከመጠራቱ በፊት በክቡ ውስጥ ያለአንድ ሰው ምልክት ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ ፋጡማ “ፋጡማ -ሳሙኤል-”ስትል አጫዋቹ ፋጡማ ካለች በኋላና ከበደ ከማለቷ በፊት አንድ ሰው ላይ ምልክት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በክቡ ውስጥ ያሉ ህፃናት ከክቡ ውጭ መንቀሳቀስ አይችሉም፡፡ ካደረጉ ግን የሚያዙ ይሆናሉ፡፡ ይህን ግለጽ/ጪ/ላቸው፡፡ የራሳቸውንና የሌላ ጓደኛቸውን ስም በተቻለ መጠን በፍጥነት ማለት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም ምልክት አድራጊው በሆነ ሰው ላይ ምልክት ለማድረግ አነስተኛ ጊዜ ይኖረዋል፡፡ ምልክት አድራጊዎቹ በሆነ ሰው ላይ ሁለተኛውን ስም ከመናገራቸው በፊት ምልክት ካደረጉ፣ ምልክት የተደረገበት ሰው ወደ ክቡ መሃል ይገባና አጫዋች ይሆናል፡፡ የቀድሞው አጫዋች የሁለተኛውን አጫዋች ቦታ ይይዛል፡፡ ጨዋታውንም እንደገና ያስጀምራል፡፡ የጨዋታውን መልዕክት አካፍሉ፡፡ ይህ ሁላችሁም የያንዳንዳችሁን ስሞች እንድትማሩና ጓደኞሞች እንድትሆኑ የሚያስችል አዝናኝ ጨዋታ ነው፡፡

ጨዋታ 2፡ ነፋሱ ይነፍሳል...



ግብ: በክፍል ውስጥ የጓደኛሞችን ትስስር የሚያስፋፋ ጨዋታ

ጊዜ: 30 ደቂቃ

ቦታ: እያንዳንዱን በአንድ ክብ ውስጥ መቆም የሚያስችል ቦታ

ዝግጅት: ለጨዋታው የችግሮችን ዝርዝር ማዘጋጀት

ማደራጀት፡ ህፃናቱ በአንድ ትልቅ ክብ ውስጥ እንዲቆሙ አድርግ/ጊ፡፡ መምህሩ በክቡ መካከል ይ/ትቁም፡፡

የጨዋታው አካሄድ

ከበው ከሚገኙት ህጻናት አንደኛው በክቡ መሃል በመምጣት ከአንተ/ከአንች ጋር እንዲሆን አድርግ/ጊ:: ወደ ክቡ መሃል በገባው/ በገባችው ህጻን የተፈጠረውን ክፍተት ሌሎች ህጻናት ለመሸፈን ወደ ክቡ እንዲቀላቀሉ ጠይቅ/ቂ::

ጨዋታዉን "ነፋሱ ለሁሉም ነፈሰ:: ማን..." በማለት ጀምር/ሪ:: ከዚህም ሌላ በመሃልላይ ስለገባው ህፃን ትንሽ የሆነ እውነታ ጨምር/ሪ:: "... ካልሲዎችን አድርጓል/ጋለች:: " ወይም "...ጥቁር ፀጉር አለው/አላት!" የተገለጸውን ባህሪ ገጽታ የሚጋራ ማንኛውም ተማሪ በክቡ ውስጥ ቦታውን ለመቀየር መራመድ ይኖርበታል/ ይኖርባታል:: (መሮጥ ግን አይደለም::) በመሃል ላይ የሚገኘው ህጻን ደግሞ ቦታው ከመሞላቱ በፊት ክፍት ቦታ ለመያዝ በፍጥነት መንቀሳቀስ ይኖርበታል:: ከክቡ መሃል አንተን/አንችን የሚቀላቀል አንድ ህፃንመቅረትይኖርበታል::

ከቦታው ከሚንቀሳቀሱ ህፃናት መካከል በአንተ ወይም በአንች የተገለጸውን ባህርይ የሚያሟሉ ካሉ ጨዋታው በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀጥላል::

"ተቀላቀሉ!" ካልክ/ሽ እያንዳንዱ መራመድ ይኖርበታል (መሮጥ አይደለም::) ቦታቸውንምይቀይራሉ:: የጨዋታውን መልዕክት ለሁሉም አድርስ/ሺ—"በዚህ ጨዋታ ስለእያንዳንዳችን አዳዲስ ነገሮችን ተምረናል:: በተጨማሪም ጨዋታዎችን በጋራ መጫዎት ጓደኞችን ለማግኘት ትልቅ መንገድ ነው::

ጨዋታ 3: የሆነ ጥሩ ነገር በል

ግብ: ኳሷ እንዳትወድቅ ለማድረግና ስለሆነ ሰው ጥሩ ነገር ለመናገር በህብረት መስራት.

ጊዜ: 30 ደቂቃ (ተለዋዋጭ)

ቦታ: ህጻናት በአንድ ትልቅ ክብ ለመቆ ምየሚስችል ቦታ

አስፈላጊ: ለስላሳ ኳስ

ዝግጅት: ዝግጅት አስፈላጊ አይደለም

አደረጃጀት: ህፃናት በአንድ ትልቅ ክብ እንዲቆሙ ማድረግ

የጨዋታው አካሄድ

ኳሷ ከመሬት እንዳትወድቅ ለመጠበቅ አጠቃላይ ክፍሉ እንደ ቡድን መስራት እንዳለበት ለህጻናት ገለፃአ ድርግ/ጊ:: በቡድኑ ውስጥ ላለህጻን ኳሱን አቀብል/ሊ:: የመጀመሪያውን ኳስ የተቀበለው/ችው ህጻን ኳሱን ለሌላ ይወረውራል::

በመቀጠል ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ ለሚኖርበት በቡድኑ ውስጥ ላለ ህፃን ኳሱን አስተላልፍ/ፊ:: አጠቃላይ ክፍሉ እንደ ቡድን በመስራት ኳሷን ከመውደቅ መከላከል እንዳለበት ለህፃናት ገለጻ አድርግ/ጊ::

የሆነ ሰው ኳሷን ከጣላት ተሳታፊዎች ኳሷን ወደእነሱ ስለወረወረው ሰው የሆነ ጥሩ ነገር መናገር ይኖርባቸዋል:: በመቀጠል ኳሷን የወረወረው ሰው ኳሷን ስለጣለው ሰው የሆነ ጥሩ ነገር መናገር ይኖርበታል:: ለምሳሌ "በእውነት አንተ ጠቃሚ ሰው ነህ!" በመቀጠል ሁሉም ህጻናት ይቀመጣሉ::

ሞጁል 7: አካቶ ትምህርት

አካቶ ትምህርት

ይህ ሞጁል ጉዳት ያለባቸውን ህፃናት በትምህርት ስለማካተት ያተኩራል:: ጉዳት ስላለባቸው ህጻናት በምንነጋገርበት ጊዜ የአካል፣ የስሜትና የአዕምሮ ጉዳት ስላለባቸው ህፃናት ማለታችን ነው:: እነዚህን ህጻናት በትምህርት ማካተት ያስፈልጋል:: ይህም ትምህርት ቤቶች ሁሉም ተማሪዎች የተሻለና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ከሚያደርጉት ጥረት ጋር ለማያያዝ ነው::

ከዚህም ሌላ ቀጥሎ ስለተዘረዘሩት አካላት ማሰብ የአካቶ ትምህርት ትኩረት ይሆናል::

- የስነ-ባህሪና የስሜት ችግሮች ያሉባቸው ህጻናት፣
- በድንገተኛና በመፈናቀል ምክንት የተከሰተ ጭንቀት ያጋጠማቸው፣
- ጊዜያዊ ወይም ተከታታይ የትምህርት ችግሮች ያጋጠሟቸውና፣
- በአዕምሮ ህመም የተጎዱ

እነዚህ "ችግር ያለባቸው ተማሪዎች" ብዙ ጊዜ ችግር እንዳለባቸው ተደርገው አይቆጠሩም:: ይሁን እንጅ እነዚህ ህጻናት የአካል ጉዳት ካለባቸው የተለዩ አይደሉም::

አካቶ ትምህርት

አካቶ ትምህርት ተግባራዊ የሚሆነው ችግር ያለባቸውና የሌለባቸው ህጻናት በአንድ ክፍል ውስጥ በጋራ ሲማሩና ሲሳተፉ ነው:: ችግር ያለባቸው ህፃናት ችግር ከሌለባቸው ጓደኞቻቸው ጋር በጋራ ሆነው ሲማሩ ውጤቱ ጥሩ እንደሚሆን ጥናቶች ያመለክታሉ::

አካቶ ትምህርት ማለት ሁሉም ህፃናት በትምህርት ሂደት መገኘታቸው፣ መሳተፋቸውና ውጤታማ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው:: በማህበረሰቡ ውስጥ ስላለው የተማሪዎች ልዩነት፣ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ባህላቸውን፣ ፖሊሲዎቻቸውንና ተግባሮቻቸውን እንደገና ማደራጀት ይኖርባቸዋል::

የአካቶ ትምህርት መርሆዎች

- ትምህርት ለሁሉም ህፃናት መሰረታዊ ሰብአዊ መብት ነው::
- አካቶ ትምህርት የህጻናት መብት እንጅ የተለየ ጥቅም አይደለም::
- አካቶ ትምህርት ችግር ያለባቸውንና የሌለባቸውን ህጻናት ባንድ ላይ የሚሳትፍ ነው::
- አካቶ ትምህርት ማንኛውም ህጻንና ቤተሰብ እኩል ዋጋ ያለው በመሆኑ ተመሳሳይ አማራጭና ተሞክሮ ይኖረዋል::
- አካቶ ትምህርት የጉዳት መጠኑ አነስተኛም ይሁን ከፍተኛ፣ ድብቅም ይሁን ግልፅ ጉዳት ያለባቸውን ህጻናት በሙሉ ይመለከታል::
- አካቶ ትምህርት ጓደኝነት ስለመመስረት፣ እንደ ማንኛውም ሰው አባልነትና አማራጮች ስለመኖራቸው ያተኩራል::
- ማካተት ህፃናት ለመማርና ለመሳተፍ እንዲችሉ ትርጉም ባለው መልኩ መደገፍ ነው::

ይህ ሞጁል ትምህርት ቤትን ይበልጥ አካታች ለማድረግ ሁለት ቁልፍ የተግባር ደረጃዎችን ያቀርባል።

1. አካታችነትን በትምህርት ቤት ማስጀመር
2. ተማሪዎችን ለተጨማሪ ድጋፍ መለየትና ለሚመለከተው ማስተላለፍ

ተግባር 1: አካታችነትን በትምህርት ቤት ማስጀመር

በትምህርት ቤትህ/ሽ የአካታችነትን ጥረቶች ለማስጀመር የትምህርት ቤቱን ባልደረባዎች ባንድ ላይ ሰብስብ/ቢ። ስብሰባው ከዚህ በታች የተሰጡትን የአካታችነትን መልዕክቶች ለማስተላለፍ መሆን ይገባዋል። በመሆኑም ሁሉም የትምህርት ቤቱ ባልደረባዎች የአካታችነትን ጠቀሜታዎች ይገነዘባሉ። ከዚህም በመነሳት ሁሉም የትምህርት ቤት ባልደረባዎች የአካታችነትን ጥቅሞች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ያስተላልፋሉ።

ተግባር 1.1: ስለጉዳት አይነቶች አጭር መግለጫ መስጠት



ተግባር 1.2 ለአካቶነት ትኩረት መስጠት

ከቁጥር ካለማስገባት፣ ከማግለልና ከመነጠል (segregation) ይልቅ ትምህርት ቤትህ/ሽ በአካታችነት ላይ ሊያተኩር እንደሚገባ እንመክራለን:: . ለረጅም ጊዜ ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ከትምህርት ተገልለው፣ በተለዩ ክፍሎች ወይም ት/ቤቶች ሲማሩ ቆይተዋል:: አንዳንድ ሰዎች ልዩ ትምህርት ተለይቶ የሚካሄድ ትምህርት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ:: ይሁንና ሁሉም ህፃናት በአንድ ላይ ሲማሩና ትምህርት ቤቶች ሁሉም ተማሪዎች የችሎታ ልዩነት እንዳለ ሆኖ በተለየ ሁኔታ እንደሚማሩ ሲደረግ የሚገኘው አወንታዊ ትምህርታዊና ማህበራዊ ውጤት ለአጠቃላይ ትምህርቱ ጠቃሚ ይሆናል:: በአካቶ ትምህርት ምክንያት ማንኛውም በትምህርት ቤት የሚገኝ ተማሪ ተጠቃሚ ይሆናል:: አካቶ ትምህርት ሁሉም ተማሪዎች በማህበራዊ ግንኙነትና በህይወታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛል::

ከዚህ በታች የቀረበውን ስዕል በማየት የአካቶ ትምህርት ጠቀሜታን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል::



የአካቶ ትምህርት ባህርያት

- ሁሉም ህፃናት መማር እንደሚችሉ እውቅና ይሰጣል::
- በህፃናት መካከል ላለው ልዩነት ዕውቅና ይሰጣል፤ ያከብራል፤ (ዕድሜ፣ ስርአተ-ፆታ፣ ዘር፣ ቋንቋ፣ ጉዳት፣ የኤችአይቪ ኤድስ ጉዳዮችና ሌሎች)
- የትምህርት መዋቅሮች፣ ስልቶችና ሥነ-ዘዴዎች የሁሉንም ህፃናት ፍላጎቶች እንዲያሟሉ ያስችላል::
- አካታች ህብረተሰብን ለማስተዋወቅ የሚያስችል ሰፊ የስልት አካል ነው::
- በቋሚነት ተለዋዋጭ የሆነ ልዩ ሂደት ነው::
- ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም የሚለውን ግብ ለማሳካት ይረዳል::
- በጉዳት ደረጃና አይነት ላይ ተመስርቶ ማንም ህፃን አይገለልም::
- ጉዳት ያለባቸውና የሌለባቸው ተማሪዎች ግላዊ ፍላጎቶች የሚያሟላ ትምህርት እንዲያገኙ ያስችላል::
- ማንኛውም ተማሪ ሙሉና ከፍ ያለ ዋጋ ያለው የክፍሉና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባል እንዲሁም ተቀባይነትና ክብር ያለው መሆኑን ያረጋግጣል::

በጥባጭነት (Bullying) - በጥባጭነት በክፍል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ተማሪዎች የሚጎዳ ስለሆነ ጎጅነቱን ማወቅ ጠቃሚ ነው። የአካል ጉዳት ካለባቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በበጥባጮች ይጠቃሉ። መምህራን በክፍል ውስጥ እንዴት ለተማሪዎቻቸው ምቹ አካባቢ መፍጠር ላይ እንደሚያተኩሩ ገለጻ አድርግ/ጊ። ትምህርት ቤታችሁ በበጥባጭ ተማሪዎችና መምህራን ለሚደርስ ጥቃት ምንም ይቅርታ የማያደርግ ፖሊሲ እንዳለው አረጋግጡ።

አካቶ ትምህርት ሁሉም ተማሪዎች በማስተማር ሂደት እንዲገኙ፣ እንዲሳተፉና ውጤታማ እንዲሆኑ ያስችላል። አካቶ ትምህርት በትምህርት ቤቶች ያለውን ባህል፣ ፖሊሲና አሰራር ለተማሪዎች ልዩነቶች ምላሽ በሚሰጥ አኳኋን ማሻሻልን ይጠይቃል። ትምህርት ቤትህ/ሽ የአካል ጉዳት የአካል ጉዳት ላለባቸውና ለሌለባቸው ተማሪዎች ይበልጥ አካታች መሆን እንዲችል በውይይት ጊዜ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ተቋሙ ሊያከናውናቸው ስለሚችሉ አማራጭ መንገዶች ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ አድርግ/ጊ። መምህራንና ሰራተኞቹ ትምህርት ቤቱ አካታች መሆን እንዲችል ቁርጠኛ እንዲሆኑ በጎ ተጽዕኖ ማሳደር ይኖርብሃል/ሻል።

ፈጣን ማስታወሻ

- ተማሪዎች (ችሎታ ከግንዛቤ ሳይገባ) በተለየ መንገድ ይማራሉ።
- መምህራን ህፃናት በሚገባ መማር ይችሉ ዘንድ የተለያዩ ምቹ አማራጮችን መፍጠር ይኖርባቸዋል።
- ተማሪዎች ስለተማሯቸው ጉዳዮች በተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ።

ተግባር 1.3:- ተግባርና ሃሳፊነቶች

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር /ትና የአስተዳደር አካላት

- ሰራተኞች ልዩነትን በአወንታዊ መልኩ መቀበል ይችሉ ዘንድ ትምርት ቤት አቀፍ ግንዛቤ መፍጠር ትኩረት መስጠት፣
- ከወተመህ፣ ከመምህራን፣ ከቤተሰብና ከተማሪዎች ጋር በመሆን በአካታች ትምህርት ምቹ የሆነ አካባቢን ለመፍጠርና ለማስተዋወቅ በትብብር መስራት፣
- ስለ ማስተማር ሥነ-ዘዴ ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው ርዕሳነ መምህራን፣ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች መምህራን እንዴት በጥሩ ሁኔታ ሊያስተምሩ እንደሚችሉ ድጋፍ ማድረግ፣
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ቅድሚያ የትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቀርበው እንዲመዘገቡና አስፈላጊም ሲሆን እንደገና የመግባ ትዕድል እንዲያገኙ ትኩረት መስጠት፤
- ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚያጋጥሟቸውን የመማር ችግሮች ለመረዳት የትምህርት ቤት አመራሮች ግልጽና ፈጠራ የተላበሰ ህሊና ሊኖራቸው ይገባል። ለምሳሌ ተማሪዎች ራሳቸው ወይም ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ካልተናገሩ ወይም ህመሙን/ችግሩን ለይቶ የማየት አጋጣሚ ካልተፈጠረ በስተቀር አንድ ተማሪ የሚጥል በሽታ ወይም ስር የሰደደ በሽታ እንዳለበት ለማወቅ አይቻልም። እነዚህን ድብቅ መዛባቶች ብዙ ሰው እንደ ጤናማ ሁኔታ ስለሚቆጥራቸው ለተማሪዎችና ለወላጆች ማሳወቅ የሚያስጨንቅ ይሆናሉ። ስለሆነም በልየታ ብቻ ሳይሆን በትምህርት መሳሪያዎች አቅርቦትም የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ቅድሚያ ትኩረት ማድረግ።
- ከትምህርት ቤት ባልደረቦቻቸው ጋር በመወያየት የአካታችነትን መርሆዎች እንዲለዩና የአካታች ትምህርትን ባህሪ ማሳወቅና ማስገንዘብ የሚችል ውጤታማ ቡድን መመስረት የአካቶ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ወሳኝ ተግባር አድርጎ መውሰድ።

መምህራን

- በትምህርት ቤቱ በሚካሄዱ የሰራተኞች ስብሰባ ላይ በመገኘት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ቅድሚያ የትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረጉ በኩል ተግተው እንዲሰሩ ማስረዳትና ማበረታታት
- ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚያጋጥሟቸውን የመማር ችግሮች በመረዳት እገዛ ማድረግ፤ የተማሪዎችን ጉዳይ በሚመለከት በውይይት ላይ ተሳታፊ መሆንና ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ እንዲሁም ክፍለ ትምህርቶች ወደ መማሪያ ክፍሎች መድረሳቸውን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ

ተግባር 2: ተጨማሪ ድጋፍ ለማድረግ ተማሪዎችን መለየትና ማወቅ

አካቶ ትምህርት ማለት ትምርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርጉበት ሂደት ነው:: ህጻናት የችሎታ ልዩነት ቢኖራቸውም ሊማሩ ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ ማዕከል ያደረገ ነው:: ይህም ማለት መምህራን ችሎታን ወይም የትምህርት ችግሮችን ባላገናዘበ መልኩ ተማሪዎችን እንዲማሩ የሚረዱ ስልቶችን በስራ ላይ ሊያውሉት ይችላሉ ማለት ነው::

ተግባር 2.1: ቀድሞ ርምጃ መውሰድ

ተማሪዎች ችግር እንዳጋጠማቸውና ቀድመው ርምጃ መውሰድ እንዳልቻሉ በተገነዘብክ/ሽ ጊዜ ከነሱ ጋር ተባብረህ ስራ/ሪ:: ከዚህም ሌላ ከወላጆችና ከአሳዳጊዎች ጋር ተባብረህ/ሽ በመስራትም ተማሪዎቹ ብቻቸውን እንዳልሆኑ ወላጆች እንዲገነዘቡ አድርግ/ጊ:: የሁሉንም ተማሪ የዕይታና የመስማት ደረጃ የመለየት ተግባርም ማከናወን ያስፈልጋል::

የመስማትና የማየት ልየታ ማካሄድ

- *ሁሉም ህፃናት ለሚያጋጥማቸው ችግር የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ እንዲቻል ዕድሜአቸው ለትምህርት ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ የማየትና የመስማት ደረጃ ልየታ ማድረግ ያስፈልጋል::*
- ህፃናትን ለማስቻል ለመርዳት የማየትና የመስማት ችግሮችን በመለየት ውሳኔ ማድረግ ጠቃሚ የሆነ የመጀመሪያ ርምጃ ነው::
- የልየታው ስራ ቀለል ባሉ ትናንሽ የልየታ መሳሪያዎች በትምህርት ቤቱ አነስተኛ ስልጠና በመስጠት በመምህራን ወይም የጤና አገልግሎት በሚሰጡ አካላት ሊካሄድ ይችላል::
- የልየታ ምዘናው የዕይታና የመስማት ምርመራ ተጠቃሚ የሚሆኑ ተማሪዎችን በህክምና ባለሞያዎች በመለየት የትምህርትና የክፍል ውስጥ ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻል ነው::
- አነስተኛ እይታ ወይም የመስማት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች መርዳት እንዲችሉ በክፍል ውስጥና በአካባቢያዊ ድጋፍ አሰጣጥ ላይ መምህራን ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል::
- የዕይታና የማዳመጥ ልየታ ከተካሄደ በኋላ በተለይም ከፍተኛ ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ወላጆች ስለውጤቱ መረጃ ማግኘት ይኖርባቸዋል::
- ከከፍተኛ ምርመራ በኋላ መምህራን የተማሪዎችን ውጤት በቀጣይነት መከታተል ይኖርባቸዋል:: በእይታና በመስማት ላይ ለውጥ መከሰት አለመከሰቱን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::
- የተማሪዎቻቸው የመማር ውጤት እንዲሻሻል ትምህርት ቤቶች በአቅራቢያ ከሚገኙ የጤና ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጉዳት ልየታና ዘላቂ ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

የማንበብና የመጻፍ ችግሮች የሚታዩባቸውን ህፃናት ጓደኞቻቸውን በመጠቀም መለየት

አጠቃላይ ሰፊ ግምገማ /ምርመራ ማካሄድ

- ከማየት ወይም ከመስማት ጋር የተያያዙ ችግሮች ከተለዩ በኂላ ተማሪዎች በትምህርት ተግባሮቻቸው ዙሪያ ችግሮቻቸው መቀጠል አለመቀጠላቸውን መከታተል ጠቃሚ ነው።
- ይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ግላዊ የትምርት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎቶችና የትምርት ድጋፍ አይነቶች ለመለየት አጠቃላይ ከሆነ ትምህርት ይልቅ የግል ትምህርት ዕቅድን መጠቀም ተመራጭ ነው።
- ተማሪዎች ምን አይነት ጉዳት እንዳለባቸው እና ሊደረግላቸው የሚገባ የትምህርት ወይም የመዝናኛ ድጋፍ ምን እንደሆነ ለመለየት አንድ የምርመራ አማራጭን ብቻመጠቀም የለብንም።

በርካታ ችግሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች መደገፍ

- ከአንድ ጉዳት በላይ የአካል ጉዳት ያጋጠማቸው ተማሪዎች ተደራራቢ ጉዳት ያለበቸው ተብለው ይቆጠራሉ።
- እነዚህ ተማሪዎች ከትምርት ቤቱና ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ ለመስራት ብዙ ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ያለው አገልግሎትና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።
- ለምሳሌ አይነ -ስውር የሆኑ በርካታ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ትኩረት ያልተሰጣቸውና ያልተለየ ተጨማሪ ያካልጉዳት አሉባቸው።

  (የማዳመጥ ችግር፣ የመስማት፣ ችግርና የአዕምሮ ችግር)

የትምህርት ዉጤቶችን ማሻሻል

- የትምህርት ቤቱን አካባቢ ለህጻናት የተመቸና ለአካል ጉዳተኞች ደህንነት የሚረዳ እንዲሆን በማድረግ አደራጅ/ጂ። በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉ የትምርት ዕንቅፋቶችን በሙሉ አስወግድ/ጂ።
- የአካል ጉዳት ያለባቸውን ህጻናት የሚረዱ ውጤታማ የማስተማር ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ስራ/ሪ።
- የአካል ጉዳትና ልዩ ፍላጎት (የማየትና የመስማት ጉድለት፣የአዕምሮ ጉዳት፣ ልዩ የትምህርት ችግሮች ወዘተ) ልዩ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል።

ተግባር 2.2:- የክፍል ውስጥ የትግበራ መሳሪያዎችን በስራ ላይማዋል

የሚከተሉትን ፈጣን የትግበራ መሳሪያዎች (ቸክሊስት) በመጠቀም እነማን መስማት እንዳልቻሉ፣ ዝቅተኛ እይታ እንዳላቸው፣ ዘግይተው እንደሚያነቡና ጭራሹኑ ማንበብ እንዳልቻሉ ተማሪዎችን በየደረጃው መለየት ይቻላል። ቸክሊስቶቹ መምህራን ለተማሪዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ ትምህርት ስልቶችን እንዲያደራጁ ይጠይቃሉ።

ፈጣን የትግበራ መሳሪያ 1

መስማት የማይችሉ ተማሪዎች ባህርያት

መስማት አለመቻል

የንግግርና የቋንቋ አጠቃቀም ምልክቶች	አዎ	የለም	እርግጠኛ አይደለሁም
ተማሪው/ዋ ረጅም አረፍተነገር የመመስረት፣ ያልተገባ ሰዋሰው የመጠቀም እና ዘገምተኛ የንግግር ድምፆችን የማፍለቅ ችግር ይታይበታል::			
ተማሪው/ዋ ጓደኞቻቸው ያለ ምንም ችግር የሚጠቀሟቸውን የንግግር ድምፆች የመመስረት ችግር አለባቸው::			
ክትምህርት ቤት ተግባራት ጋር የተያያዙ ችግሮች			
ተማሪው/ዋ ባንዳድ ሁኔታዎች ጥሩ የሚያዳምጥ/የምታዳምጥ በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ ምላሽ የማይሰጥበት/የማትሰትበት ሁኔታ ይስተዋላል::			
ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት ተግባራት የፍላጎትና የትኩረት ማጣት ያሳያል/ታሳያለች::			
ተማሪው/ዋ በክፍል ውስጥ የሚሰጡ መመሪያዎችንና ማብራሪያዎችን በመከተል ችግር ያጋጥመዋል/ያጋጥማታል::			
ተማሪው/ዋ ማንበብ ያለመቻል ችግሮች ይታይበታል/ባታል::			
ተማሪው/ዋ ለመምህራን ጥያቄዎች የተሳሳተ ምላሽ ይሰጣል/ትሰጣለች::			
የክፍል ውስጥ ባህርያት			
ተማሪው/ዋ አንደኛውን ጆሮ ትቶ/ታ ሌላኛውን የሚጠቀሙ ይመስላሉ:: ወይም የማያዳምጥ የሚመስለውን/ላትን ጆሮ ወደ ሚደመጠው ነገር በማዘንበል ለመጠቀም ይሞክራል/ ትሞክራለች::			
ተማሪው/ዋ ጮክ ብሎ/ላ ይናገራል/ትናገራለች::			
ተማሪው/ዋ በአንዳንድ አጋጣሚዎች የሚያዳምጥ/የምታዳምጥ ሲመስል/ስትመስል በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ ምላሽ የማይሰጡበት ሁኔታ ይስተዋላል::			
ተማሪው/ዋ አንዳንድ ጊዜ ስሙ/ስሟ ሲጠራ/ስትጠራ ምላሽ መስጠት ይሳነዋል/ናታል::			
ተማሪው/ዋ በአካባቢው ለሚሰሙ ድምጾች አዘውትሮ/ራ ምላሽ አይሰጥም/አትሰጥም::			
ተማሪው/ዋ መረጃ እንዲደገምለት/ላት አዘውትሮ/ራ ይጠይቃል/ትጠይቃለች::			
ተማሪው/ዋ የተረበሸ/ች እና ግራ የተጋባ/ች ይመስላል/ ትመስላለች::			
ተማሪው/ዋ በውይይትጊዜ አዘውትሮ/ራ የመምህራንን ፊት በትኩረት ያያል/ታያለች::			

እባክህን/ሽን በክፍል ውስጥ የተገነዘብካቸውን /ሻቸውን የተማሪዎች ቀዳሚ ችግሮች ግለጽ/ጭ:

____

____

በክፍል ውስጥ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመደገፍ የሚረዱ ጥሩ ውጤት ያስገኙ ስልቶችን ተገንዝበሃል/ሻልን?

____

____

ፈጣን የትግበራ መሳሪያ 2

የዝቅተኛ ዕይታ አደጋ ያለባው ተማሪዎች ባህርት

የዝቅተኛ ዕይታ ምልክቶች

የአይን ገጽታ		አዎ	የለም	እርግጠኛ አይደለሁም
1	የተማሪው/ዋ አይኖች በብዛት እንባ ያነባሉ?			
2	የተማሪው/ዋ አይኖች የቀሉና ያበጡ ናቸው?			
3	የተማሪው/ዋ አይኖች የተጨማደዱና ዳመናማ ይመስላሉ?			
4	የተማሪው/ዋ አይኖች ያበጡ ናቸው?			
5	ተማሪው/ዋ አይኖች ግራጫ ወይም ነጭ ይመስላሉን? (አንደኛው ወይም ሁለቱም ብሌኖች)			
6	የተማሪው/ዋ አይኖች ቅንጅት ያንሳቸዋል?			
ከትምህርት ቤት ተግባራት ጋር የተያያዙ ችግሮች				
7	ተተማሪው/ዋ ርቀው የሚገኙ ነገሮች ደብዛዛ ናቸው የሚል ቅሬታ ያሰማል/ታሰማለች?			
8	ተማሪው/ዋ በሚያነብበት/በምታነብበት ጊዜ ደብዛዛ ዕይታ እንዳጋጠመው/ማትይገልጻል/ትገልጻለች?			
9	ተማሪው/ዋ ደቃቅ ህትመቶችን ስለማንበብ ችግር እንዳጋጠመው/ማት ወይም በታተሙ ፊደላትን መካከል ልዩነቶችን ስለ መለየት ቅሬታ ያሰማል/ታሰማለች?			
10	ተማሪው/ዋ በሚያነብበት/ በምታነብበት ጊዜ የራስ ምታት ይሰማዋል/ታል?			
11	ተማሪው/ዋ በሚያነብበት/በምታነብበት ጊዜ ቃላት በወረቀቱ ላይ የሚንከባለሉ ይመስለኛል የሚል ቅሬታ ያሰማል/ታሰማለች?			
12	የተማሪው/ዋ በክፍል ውስጥ የማየት ችሎታ በፊደላት መጠን፣ በቀለም ወይም በብርሃን ድምቀት ተጽንኦ ያድርበታል?			
ባህርይና እንቅስቃሴ				
13	ተማሪው/ዋ ንቃት የጎደለው/ላት ወይም ነገሮችን ለመለየት የሚ/ምቸገር ነው/ናት?			
14	ተማሪው/ዋ ኳስን በእጅ እንደመያዝ ያለ የአይንና የእጅ ቅንጅት ችግር ያሳያል/ታሳያለች?			
15	ተማሪው/ዋ በሚያነብበት/በምታነብበት ጊዜ አንደኛውን አይን ይሸፍናል/ትሸፍናለች?			
16	ተማሪው/ዋ በሚያነብበት/በምታነብበት ጊዜ ራሱን/ራሷን ያዘነብላል/ታዘነብላለች?			
17	ተማሪው/ዋ እቃዎችን ወደ አይኑ/ኗ ጠጋ አድርጎ/ጋ ያያል/ታያለች?			

እባክዎን ተማሪዎች በብዛት በክፍል ውስጥ የሚያሳዩዋቸውን እርስዎ የተገነዘቡዋቸውን ምልክቶችና ችግሮች ይግለፁ? ______________________________

____

በክፍል ውስጥ የዕይታ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት የሚያስችሉ ምን ስልቶችን መለየት ችለዋል?

____

* *መምህራን የተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ፊደላት የያዘ ካርታ ሊኖራቸው ይገባል:: ይህም በተለይ በገጠር አካባቢ ለሚሰሩ መምህራን ከተገቢ ገለጻዎች ጋር እንደ ጠቃሚ የመለያ መሳሪያ ያገለግላቸዋል::*

ፈጣን የትግበራ መሳሪያዎች 3

የማንበብ ችግር (መዘግየት፣ አለመቻል) ያለባቸው ህፃናት ባህርያት

የማንበብ ችግር ያለባቸውን ህፃናት (ከ1ኛ-3ኛ ክፍሎች) መለየት የሚያስችል ቼክ ሊስት

በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ህጻናት ጋር ሲነጻጸር እነዚህ ተማሪዎች የሚከተሉት ችግሮች ይታዩባቸዋል።	
1	በጽሁፍ የሰፈሩ ሃሳቦችን የመገንዘብ ችግር
2	ጽሁፍን ከግራ ወደ ቀኝ ለማንበብ መቸገር
3	የመጻህፍት ርዕስ በሽፋኑ ላይ መሆኑን አለመረዳት
4	በመጻህፍት ውስጥ ያሉ ታሪኮች ከአንድ ገጽ ወደቀጣዩ የሚሄድ መሆኑን አለመረዳት
5	የአንዳንድ ቃላት ድምጾችን እንደሚመሳሰሉ (ኩበት፣ እበት,) ሌሎቹ ደግሞ እንደማመሳሰሉ አለመገንዘብ (እሳት፣ ብቅል)
6	ሌሎች ህፃናት በውጤታማነት ሊማሯቸው የሚችሉ የንግግር ድምጾች ግንዛቤ ተግባራትን በአግባቡ አለመፈጸም
7	የፊደላት ስሞችን ማስታወስ አለመቻል
8	በራስ ስም ውስጥ ያሉ ጥቂት ፊደላትን መለየት አለመረዳት
9	ተመሳሳይነት ያላቸውንና በወረቀት ላይ የሰፈሩ ቃላት እንዴት እንደሚነበቡ አለማወቅ
10	ቃላትን ማንበብ አለመቻል (ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ)
11	በሚጻፍ ጊዜ ፊደላትን መቅረጽና ቃላትን በአግባቡ መደርደር አለመቻል
12	ቃላትን በተገቢው ፍጥነትና ትክክለኛነት ማንበብ አለመቻል
13	ተዘውታሪ ቃላትን ያለግድፈት መጻፍ አለመቻል
14	አቀላጥፎ ማንበብ አለመቻል
ተማሪዎች ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ባህርያት አንደኛውን ያሳያሉ።	
15	ከማንበብና ከመጻፍ ክሂሎች ይልቅ የማዳመጥና መናገር ክሂሎች የተሻሉ ናቸው።
16	አዳምጦ መረዳት እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው ዝቅተኛ ነው።
17	ማንበብና መጻፍን አለመፈለግ (በተለይም ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ)

የማንበብ ችግር ያለባቸውን ህፃናት (ከ4ኛ-8ኛ ክፍሎች) መለየት የሚያስችል ፈጣን የተግባር መሳሪያ

በክፍል ውስጥ ከሌሎች ህጻናት ጋር ሲነጻጸር እነዚህ ህፃናት የሚያጋጥሟቸው ችግሮች	
1	በማንበብ እናመጻፍ የሚሰሩ ተግባራትን በወቅቱ አለመስራት
2	ለማንበብ መቸገር (ተገቢነት፣ ድምጸት፣ ፍጥነት)
3	የተለመዱ ቃላትን ያለግድፈት ለመጻፍ መቸገር
4	ረጅምና ባለብዙ ቀለም ቃላትን ያለግድፈት ለመጻፍ መቸገር
5	የአጻጻፍ ስርአት ችግር (ሥርአተ-ነጥብ)
6	ሀሳቦችን ለማስተላለፍ የንግግር ቋንቋን በግልጽ ማደራጀት አለመቻል
7	የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን መቸገር 1. የቃላት ንባብ ሙከራዎች 2. ቃላትን ድምጽን ከፍ አድርጎ የማንበብ ወቅታዊ ምዘናዎች 3. የፊደላት አጻጻፍ ሙከራዎች 4. የአንብቦ መረዳት ሙከረ
8	ሂሳባዊ ቀመሮችን ማስታወስን የሚጠይቁ የሂሳብ ተግባራትን በተገቢው አለመያዝ
ተማሪዎች ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ባህርያት አንደኛውን ያሳያሉ።	
9	ከማንበብና ከመጻፍ ክሂሎች ጋር ሲነጻጸር አዳምጦ መረዳት ይከብዳቸዋል።
10	የአዳምጦ መረዳት እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው ዝቅተኛ ነው።
11	ድርሰትን በትክክለኛ አጻጻፍ እና ሥርአተ ነጥብ ከማስፈር ይልቅ የድርሰቱን ይዘት መጻፍ ይቀላል። (ፍደላት፣ ስርአተ-ነጥብ)
12	ማንበብና መጻፍን ለማከናወን ፈቃደኛ አለመሆን ይታያል። (በተለይም ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ)
13	ማንበብና መጻፍ ከሚጠይቁ ከአካዳሚያዊ ትምህርቶች ጋር የተያያዘ ችግር

ተግባር 2.3:- ለተጨማሪ ድጋፍ የተለዩ ተማሪዎች

ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ እንዴት እንደሚፈልጉ ለመለየት ፈጣን የትግበራ መሳሪያዎችን መረጃ መጠቀም ትችላላችሁ:: ቸክሊስቶቹ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ህፃናት ለይቶ ማስቀመጥ አይደሉም:: ለመስማት ወይም ለዕይታ ጉድለት ችግር የተጋለጡ ተማሪዎችን ወደሚመለከተው ለማስተላለፍ ከወላጆች ጋር ተባብሮ መስራት ከግንዛቤ መግባት ይኖርበታል:: ለተጨማሪ ድጋፍና አገልግሎት አማራጮች ወዳሉበት ወደ ህብረተሰቡ መድረስ ያስፈልጋል::

ተግባር 3 እንደገና መከለስ (ያለፈውን መገምገም): ተግባሮችና ሃላፊነቶች የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር

ከትምህርት ቤቱ አገልግሎት ውጭ ለሆነ ድጋፍ ከወላጆች ጋር በመተባበር ስራ/ሪ::

ሁሉም ህፃናት መማር ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ ለባለድርሻ አካላት የማስጨበጥ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::

መምህራን

ትኩረት እንዲያገኙ የተፈለጉትን ተማሪዎች ለመለየት ቸክሊስቶችን ተጠቀሙ:: የክፍሉን አቀራረብ የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች ባገናዘበ መልኩ አሻሽላችሁ ተጠቀሙ::

ማስታወሻ

- ቸክሊስቶች ተማሪዎችን ለይቶ ለማስቀመጥ የምንጠቀምባቸው አይደሉም::
- ተማሪዎችን የአካል ጉዳት እንዳለባቸው አድርጎ አለመፈረጅ::
- ሁሉም ህፃናት ሊማሩባቸው የሚችሉባቸውን መልዕክቶች ተደራሽ ማድረግ::



ሞጁል ፰: የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነባቸው ትምህርት ቤቶች

የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነባቸው ትምህርት ቤቶች

ክፍል 1:- የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነበት የትምህርት ቤት አካባቢ መኖሩን ማረጋገጥ

የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነበት የትምህርት ቤት አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው?

ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት የሁሉም ልጃገረዶች እና ሴቶች፣ ህጻናትና አዋቂ ወንዶች መብት ነው፡፡ በዋናነትም የቤተሰብ ጤናን ለማሻሻል፣ የእናቶችና ህጻናት ሞትን እና ድህነትን ለመቀነስ ይጠቅማል፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንድ ህጻናት ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት ችግር ላይ ናቸው፡፡

ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት ችግር ላይ ያሉ ህጻናት በመርሃ ግብር አለመኖር፣ በዕድሉ አለመፈጠር፣ የኢኮኖሚ አጋዥ በማጣት፣ በዘር ወይም በጎሳ ማንነታቸው፣ በመልከዓ-ምድር ምቹ አለመሆን፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በአድሎ፣ በመገለል እና በሌሎች ምክንያቶች ትምህርት አያገኙም፡፡ ይህም ሆኖ ብዙ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ተመዝግበው በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የላይኞቹ ክፍሎች ላይ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቁጥር ትንሽ ልጃገረዶች በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ በገጠር አካባቢዎች የጾታ ምጥጥን ክፍተቱ የበለጠ ይጨምራል፡፡ የጾታ ምጥጥን ክፍተቱ የሚጀምረው ትምህርት ለመጀመር ከሚደረገው ምዝገባ ጀምሮ ነው፡፡

ይህም ሆኖ የልጃገረዶች እና የወንዶች የመድገምና ማቋረጥ ምጣኔ ተቀራራቢ ሲሆን የትምህርት አፈጻጸማቸው ላይ ግን ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር **የጾታ ምጥጥን** በትምህርት ቤቶች እንዲኖር ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ ሌላው ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር በትምህርት ዘርፉ የሴት የትምህርት አመራሮችን ቁጥር መጨመር እና አቅማቸውን ማዳበር ነው፡፡ የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን የሚያበረታቱ ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠሩ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ቅበላቸው ይጨምራል፣ ያቋረጡ ተማሪዎች ይመለሳሉ፣ የተማሪዎች ውጤት ይሻሻላል፣ እንዲሁም የተማሪዎች የማጠናቀቅ ምጣኔ ይጨምራል፡፡ የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን የሚያበረታቱ ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠሩ ትምህርት ቤቶች የሚከተሉት ምቹ ሁኔታዎች አሏቸው፡-

የተማሪዎች፣ የመምህራን እንዲሁም የትምህርት ቤት አመራሮች ስርዓተ-ፆታ የተመጣጠነ ነው፡፡	የትምህርት ግብዓቶች የልጃገረዶችን እና የወንዶችን ፍላጎቶች ያገናዘቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ንጹህ ውሃ፣ለልጃገረዶችና ለወንዶች የተለዩ መጸዳጃ ቤቶች፣ የልጃገረዶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና ማረፊያ ክፍል	የክፍል ውስጥ መማር ማስተማሩ ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ ነው፡፡

ተማሪዎችና መምህራን ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው። እንዲሁም ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ችግሮች የሚፈቱበት ግልጽና አሠራር አለ።	የትምህርት ቤቱ አመራር በጣም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን ለይቶ የሚረዳበትን ስልት ቀይሶ ተግባር ላይ አውሏል።	የወንዶችና የልጃገረዶች የተጓዳኝ ትምህርት ተሳትፎ እኩል ነው።

በእኔ ትምህርት ቤት የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነበት ለማድረግ እንዴት ማድረግ እችላለሁ?

ከመጀመራችን በፊት የሚከተሉትን ጠቃሚ ትርጉሞች እንመልከት፡-

የስርዓተ-ፆታ እኩልነት፡- እኩል መብት፣ ኃላፊነት እና እድል ለሴቶች እና ለወንዶች ያለልዩነት እና መድሎ መስጠት ነው።

የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት፡- የሴቶችን እና የወንዶችን ፍላጎት ያገናዘቡ ተግባራትን ወይም አገልግሎቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መተግበር/መስጠት ነው።

የስርዓተ-ፆታ ምጥጥን፡- የሴቶችን እና የወንዶችን ቁጥር እኩልነት የሚያሳይ ሲሆን የሴቶች ቁጥር ሲካፈል ለወንዶች ቁጥር መጠኑ 1:1 ከሆነ ምጣኔው እኩል ነው ማለት ነው።

ምንም እንኳን የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የመጨረሻ ግብ እንደሆነ ቢታሰብም ግቡን ለማሳካት የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ላይ ያተኮሩ ተግባራት ሥራ ላይ መዋል አለባቸው። ትምህርት ቤት ማህበራዊ መማማር የሚከወንበት ተቋም በመሆኑ አዎንታዊ የሆነ ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት ያስችላል። የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚማሩ ልጃገረድ እና ወንድ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ትምህርታቸው ላይ ትኩረት አድርገው የመማር እድል አላቸው። በተጨማሪም ተማሪ የመቀበል ምጣኔን ይጨምራል፣ አቋርጦ የመመለስ ምጣኔን ይጨምራል እንዲሁም የልጃገረዶችን እና የወንዶችን የመማር ውጤት ለማሻሻል ያግዛል።

ትምህርት ቤትዎን በሚገባ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት የሰፈነበት ለማድረግ የሚያግዙ እርምጃዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

የትምህርት ቤቱን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት መለኪያ የውጤት መሙያ ካርድ እና የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያ በመጠቀም የትምህርት ቤቱን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት መለካት።

የትምህርት ቤቱን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ለማሻሻል የሚያግዙ ተግባራትን የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ማካተት።



የትምህርት ቤት ደህንነትን ማሻሻል፤[ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የጾታ ጥቃቶችን የሚከላከል ኮሚቴ እንዴት ይቋቋማል፤ ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የጾታ ጥቃቶችን መከላከልና ምላሽ እና ለህጻናት ምቹና ማራኪ ትምህርት ቤት ሞጁሎችን ይመልከቱ]

ተግባር 1፡ ለእያንዳንዱ ተግባር የሚያስፈልጉ ቅደም ተከተሎች፣ ተግባር እና ኃላፊነቶች

1. የትምህርት ቤቱን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት መለካት።

አስፈላጊ መሣሪያዎች፡-

- *የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት መለኪያ የውጤት መሙያ ካርድ*
- *የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያ*

ተግባር 1.1፡- የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት ማካሔድ

ርዕሰ መምህራን እና/ወይም የጉድኝት ሱፐርቫይዘር የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት የመለኪያ ውጤት ካርድን በመጠቀም ጥናቱን ማካሔድ እና በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነትን ለማስፈን የሚረዱ መሻሻል የሚገባቸውን ተግባራት መለየት አለባቸው፡፡

እያንዳንዱን ዝርዝር ነጥብ በነጥብ ሳይዘሉ በአግባቡ ውጤት መስጠት ወሳኝ ነው፡፡ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ግለሰቦች ለየብቻ ሳይነጋገሩ ውጤቱን ቢሞሉ የተሻለ ነው፡፡ በመጨረሻም በውጤቱ ላይ በተለይም የተለያየ ውጤት የተሰጠበት ሀሳብ ላይ በጋራ መመካከር አስፈላጊ ነው፡፡ ውጤቱን በማስላት መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች በመለየት መወሰን፡፡ ውጤቱ ከ43-48 ከሆነ በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነትን ከፍተኛ ነው ማለት ነው፡፡ ውጤቱ ከ34-43 ከሆነ በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነትን ለማስፈን መሻሻል የሚገባቸው ተግባራት አሉ ማለት ነው፡፡ ውጤቱ ከ34 በታች ከሆነ በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለሆነ በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል የሚገባቸው ተግባራት አሉ ማለት ነው፡፡

ከዚህ በታች ተግባር 2 በትምህርት ቤት የጾታ ፍትሃዊነትን ለማሻሻል በዝርዝር መሠራት ያለባቸውን ተግባራት ያብራራል፡፡ በተቻለ መጠን ርዕሰ መምህሩ/ሯ በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት የመለኪያ ውጤት ካርድን በመጠቀም መነሻ የዳሰሳ ጥናት ማካሔድ አለበት/አለባት፡፡ የተገኘውን ውጤት ለሱፐርቫይዘር፣ ለመምህራን እና ለወተመህ በማስረዳት ማካፈል አለበት/አለባት፡፡ በዓመቱ የትምህርት መጨረሻ የዳሰሳ ጥናቱን በማድረግ የጾታ ፍትሃዊነቱ መሻሻሉን ወይም መስፈኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

ተግባር 1.2፡- የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያን መጠቀም

ርዕሰ መምህራን እና/ወይም የጉድኝት ሱፐርቫይዘር የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያን በመጠቀም መምህራን በክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት መጠበቃቸውን እና የክፍል ውስጥ መማር ማስተማሩ ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ መሆኑን ማየት አለባቸው፡፡

ምልከታው የሚደረገው ሙሉ ክፍለ ጊዜው ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ነው፡፡ ከክፍል ምልከታ በኋላ ከጥንካሬዎች በመጀመር መሻሻል በሚገባቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ የክፍል መምህሩ/ሯ ጋር መወያየት ያስፈልጋል፡፡

የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያውን በመጠቀም በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ ወቅት ሁሉም መምህራን ክፍል ውስጥ በመግባት መነሻ የዳሰሳ ጥናት ማካሔድ አለበት፡፡ በዓመቱ የትምህርት አጋማሽም አካባቢ ድጋሚ ምልከታ በማድረግ መምህራን በክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት መጠበቃቸውን እና የክፍል ውስጥ መማር ማስተማሩ ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ ሆኖ መሻሻሉን ማረጋገጥ፡፡ ሁሉም መምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮች ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ ሥነ ትምህርት ላይ ስልጠና መውሰድ አለባቸው፡፡

ተግባር 1 ማጠቃለያ፡- ተግባርና ሀላፊነቶች

ርዕሰ መምህራን እና የጉድኝት ማዕከል ሱፐርቫይዘሮች

- *በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ እና መጨረሻ የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት የመለኪያ ውጤት ካርድን በመጠቀም የዳሰሳ ጥናት ማካሔድ፤*
- *የተገኘውን ወጤት ለሱፐርቫይዘር፣ ለመምህራን እና ለወተመህ በማስረዳት ማካፈል፤*
- *የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያውን በመጠቀም በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ እና አጋማሽ ወቅት አካባቢ ሁሉም መምህራን ክፍል ውስጥ በመግባት የዳሰሳ ጥናት መካሔድ አለበት። የምልከታውን ውጤት ለመምህራን ማስረዳት ተገቢ ነው።*

ጠቃሚ መልዕክት፡-

የዳሰሳ ጥናት መሳሪያዎችን ለሁሉም ግልጽ በማድረግ ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። ሁሉም የትምህርት ቤቱ አካላት የዳሰሳ ጥናቱን ተግባራዊ ሂደት እና ጥናቱ የሚደረግበትን ምክንያት መረዳት አለባቸው።

2. መሻሻል ይገባቸዋል ተብለው ተለዩ ተግባራትን የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ማካተት

የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትን በትምህርት ቤት ለማሻሻል ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተለዩ ዝርዝር ተግባራትን የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ማካተት አለባቸው። የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት የመለኪያ ውጤት ካርድን በመጠቀም በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ላይ በተገኙት ዋና ዋና ወጤቶች ዙሪያ ከሱፐርቫይዘር፣ ከመምህራን እና ከወተመህ ጋር በመነጋገር በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነትን ለማስፈን የሚረዱ ዝርዝር ተግባራትን መለየት፤ ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው በዝርዝር ቀርበዋል።

ህዝብ ነክ ጥናቶች (Demographics)



በትምህርት ቤት ውስጥ በሚተገበሩ ሁሉም ተግባራት ላይ ሁለቱም ጾታዎች የእኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ስሜታቸው እየጨመረ ከመጣ የጾታ ምጥጥን ትምህርት ቤቱ ላይ ጨምሯል ማለት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ዜሮ ውጤት ካለ የጾታ ምጥጥን በትምህርት ቤቱ ችግር ላይ ነው ማለት ነው። በቁጥር አነስተኛ ሴት መምህራን፣ የትምህርት ቤት አመራሮች ወይም የወተመህ አባላት ካሉ የልጃገረዶችን እና የሴቶችን ችግሮች በአግባቡ የመረዳት ችግር አለ በመሆኑም በአግባቡ ለችግሮቻቸው መፍትሔ አያገኙም ተብሎ ይታሰባል። በተጨማሪም ልጃገረዶች በትምህርት ቤቱ ውክልና እንዳላቸው አይሰማቸውም፤ ልጃገረዶች የትምህርት አመራርነት ቦታ ላይ ሴቶችን የማያዩ ከሆነ ወደፊት ለዚህ ዓይነት ኃላፊነት የሚበቁ አይመስላቸውም። በክፍል ውስጥ ያሉት የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንድ ተማሪዎች ቁጥር ያነሰ ከሆነ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምቾት ስለማይሰማቸው በትምህርታቸው ውጤታማ ለመሆን ይቸገራሉ። በተቃራኒውም የሴት ተማሪዎች ቁጥር ሲበዛ ወንድ ተማሪዎች ላይም ችግሩ ይከሰታል።

በትምህርት ቤት የዚህ ዓይነት ችግር በሚከሰትበት ጊዜ መፍትሔዎችን ማፈላለግ ወሳኝ ነው። በትምህርት ቤት የተማሪዎች ስብጥር በሚገመገምበት ወቅት ከዚህ በታች የቀረቡትን መነሻ ሀሳቦች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

የጾታ ልዩነትን መሠረት የሚያደርጉ ምዝገባዎችን፣ ከትምህርት ቤት ማቋረጥን፣ ልዩ ልዩ ተግባራት በምክንያት መለየት፤ እነዚህን ክፍተቶች ለመፍታት የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራትን ለይቶ ለሥራ ማዘጋጀት። ለወላጆች

ግንዛቤ መፍጠር አንዱ እርምጃ ሲሆን ከወላጆችና ከተማሪዎች በኩል ያሉትን ችግሮች መረዳት ያስፈልጋል። ከዚያም ከባለድርሻ አከላት ጋር በመተባበር የጾታ ምጥጥን ክፍተትን ማሻሻል።

ወተመህ የአባላቱን የጾታ ምጥጥን የሚያረጋግጥ አደረጃጀትን በመከተል የአመራር ተዋጽኦውን እና የኃላፊነት ድርሻውን ማስተካከል ይችላል። ለምሳሌ የወተመህ ሊቀመንበር በየምርጫው እየተፈራረቀ ወንድ ወይም ሴት እንዲሆን ማድረግ፤ የመምህራን ቅጥር እና የትምህርት አመራሮች ምደባ ላይ ወንዶች እና ሴቶች እኩል እድል እንዲያገኙ ከወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ጋር መመካከር፤ ከሴት መምህራን እና የትምህርት አመራሮች ጋር የአመራርነት ሚና ለመጫወት በሚጥሩበት ጊዜ በሥራ ላይ እና በሥራ አካባቢ ስለሚያጋጥሟቸው መሠናክሎች እና ችግሮች ማወያየት፤ በሥራ ላይ እና በሥራ አካባቢ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል የሚያስችሉ ስልቶች ላይ መወያየት እና እኩል እድል ለሴቶችና ለወንዶች መስጠት፤

የትምህርት ቤት ግብዓቶች

የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት ላይ ዜሮ ነጥቦች አሉ ማለት በትምህርት ቤት ግብዓቶች አለመሟላት ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ በትምህርት ቤቱ ምቹነት ላይ ጫና ይፈጥራል። ይህም የተማሪዎች ቅበላ ላይ፣ ማቋረጥ ላይ እና የትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። የትምህርት ቤት ግብዓቶች መሟላት አለመሟላታቸውን በምናረጋግጥበት ወቅት የሚከተሉትን ጉዳዮች ልብ ማለት ያስፈልጋል።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ንጹህ ውሃ፣ ለልጃገረዶችና ለወንዶች የተለዩ በርና መቆለፊያ ያላቸው ንጹህ መጸዳጃ ቤቶች፣ የልጃገረዶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና ማረፊያ ክፍል መኖር አስገዳጅ የህጻናት መብት ነው።

መጸዳጃ ቤቶች በየቀኑ በተደጋጋሚ በጽዳት ሠራተኞች አማካኝነት መጸዳት አለባቸው። (ተማሪዎች መጸዳጃ ቤቶችን ማጽዳት የለባቸውም።)

ከእያንዳንዱ መጸዳጃ ክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የንጽህና መጠበቂያዎች የሚጠራቀሙበት የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቅርጫት መኖር አለበት።

ከእያንዳንዱ መጸዳጃ ቤት ውጭ በቅርብ ርቀት ላይ የእጅ መታጠቢያ ከሳሙና ጋር መኖር አለበት።

ትምህርት ሚኒስቴር ለ50 ተማሪዎች አንድ የመጸዳጃ ክፍል (መቀመጫ) እንደሚያስፈልግ ይመክራል። ትምህርት ቤቶች ለሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ማቅረብ አለባቸው። (የወር አበባ ሥነ-ጽዳት እና መሰረታዊ ሥነ-ተዋልዶ ጤና፤ ተደጋግሞ ጥቅም ላይ የሚውል የልጃገረዶች የንጽህና መጠበቂያ እንዴት ይዘጋጃል? የሚለውን ሞጁል ይመልከቱ)። ትምህርት ቤቶች ይህን ዝቅተኛ ስታንዳርድ ማሟላት ካልቻሉ ለማሟላት የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራትን በትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ማካተት አለባቸው። ድጋፍ ማፈላለግ የመጀመሪያው ተግባር ሊሆን ይችላል።

ደህንነት

የደህንነት ጉዳይ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ትኩረት ተሰጥቶት መረጋገጥ ስላለበት ራሱን ችሎ ስለደህንነት "በትምህርት ቤት የሚደርሱ የጾታ ጥቃቶችን የሚከላከል ኮሚቴ እንዴት ይቋቋማል፤ በትምህርት ቤት የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ" በሚለው ክፍል ውስጥ ቀርቧል።

መምህራን እና መማር ማስተማር

የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት ላይ ዜሮ ነጥቦች አሉ ማለት የመማር ማስተማሩ ሂደት መሻሻል አለበት ማለት ሊሆን ይችላል። የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያን በመጠቀም የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ በመመካከር መምህራን ችግሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ የተግባር ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ያስፈለፈጋል።

የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትን በትምህርት ቤት ለማረጋገጥ የሚረዱ ዝርዝር ነጥቦች በትምህርት ቤቱ የተግባር ዕቅድ ዝግጅት ወቅት ማካተት ያስፈልጋል። የተወሰኑ ምሳሌዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

- ወንዶችና ልጃገረዶች እኩል ጥያቄ የመመለስ ዕድል እንዳላቸው እንዴት ማረጋገጥ ትችላለህ/ትችያለሽ?
- ወንዶችና ልጃገረዶች እኩል የክፍል ውስጥ ተግባራትን እየመሩ መሆናቸውን እንዴት ማረጋገጥ ትችላለህ/ትችያለሽ?
- በመማር ማስተማሩ ሂደት የተለያዩ የመማር ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎችን ማርካት መቻሉን እንዴት ማረጋገጥ ትችላለህ/ትችያለሽ?
- ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በተጫወቱትን ሚና እና በሳይንስ፣ በሒሳብና በሥነ- ጽሁፍ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እንዴት ማረጋገጥ ትችላለህ/ትችያለሽ?

ሁሉም መምህራን በትምህርት ቤት የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶች መከላከል ላይ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ መሰልጠን አለባቸው። በሁሉም የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች ይህን ስልጠና የሚሠጡ ባለሙያዎች መኖር አለባቸው።

ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍ

የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት ላይ ዜሮ ነጥቦች አሉ ማለት ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍ መሻሻል አለበት ማለት ሊሆን ይችላል። ብዙ ጊዜ እነዚህ ተማሪዎች ሴቶች ናቸው። ትምህርት ቤቱ ወይም ማህበረሰቡ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን በመርዳት የህጻናቱን ምዝገባ፣ አቋርጦ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እና የትምህርት ውጤታማነትን በጣም እንዲጨምር ማድረግ ይችላሉ።

የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር ኮሚቴ ለትምህርት ቤታቸው በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት አለባቸው። አንዱ ስልት ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች ድጋፍ የሚሆን የገቢ ማስገኛ ተግባራትን መፍጠር ሊሆን ይችላል። የገቢ ማስገኛ ተግባራቱ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ይለያያሉ። ልትተገብሯቸው ከምትችሏቸው ፕሮጀክቶች መካከል፡-

- ከትምህርት ቤቱ መሬት ውስጥ ለእርሻ የሚሆን መሬት ቀንሶ መስጠት፤
- የደንብ ልብሶችን (ዩኒፎርሞችን) ወይም ተደጋግሞ ሥራ ላይ የሚውል የልጃገረዶች ንጽህና መጠበቂያ መስፋት፤
- በትምህርት ቤት ካፌቴሪያ ከፍቶ መሥራት፤ ወይም
- የትምህርት ቤት ሱቅ መክፈት፤

የተንዳኝ ትምህርት ተግባራት

የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት ላይ ዜሮ ነጥቦች አሉ ማለት የተማሪዎች ተሳትፎ ፍትሃዊ አይደለም ማለት ሊሆን ይችላል። ወንዶች እና ልጃገረዶች የመጫዎቻ ሜዳዎችን መጠቀማቸውና

ሁሉም በስፖርት ተሳታፊ መሆናቸው በጣም ጥሩ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ተግባራት ለአካላዊና አዕምሯዊ ጤናቸው ጠቃሚ ናቸው። ወንዶች ብቻ በስፖርት መሳተፍ አለባቸው የሚለው የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። ልጃገረዶችም ቢሆን በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ስለሚያምኑ በስፖርት መሳተፍ አንፈልግም ሊሉ ይችላሉ።

ሁሉንም ወንዶች እና ልጃገረዶች የስፖርት መጫዎቻ ሜዳዎችን በንቃትና በእኩል እንዲጠቀሙ ማበረታታት አለብህ/አለብሽ። ትምህርት ቤቱ የስፖርት መጫዎቻ ሜዳዎች አገልግሎት እንዴት እየሰጡ እንደሆነ መገምገም እና ወንዶች ብቻቸውን በበላይነት እንዳይጠቀሙበት አቅዶ መሥራት ያስፈልጋል። የልጃገረዶችን የስፖርት ክበብ እና ሌሎች የልጃገረዶች አካላዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚሰሩ ሥራዎችን ማበረታታት አለብህ/አለብሽ።

ልጃገረዶች እና ወንዶች ክበቦች ላይ እና ሌሎች የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ላይ እኩል መሳተፍ አለባቸው። የትምህርት ምዝገባ ላይ በልጃገረድ እና በወንድ ተማሪዎች መካከል ያለው ቁጥር እኩል ቢሆንም እንኳን በሌሎች ተግባራት ያላቸው ተሳትፎ እኩል አለመሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው። አንዱ የልጃገረዶች ተሳትፎ መጨመሪያ ስልት ልጃገረዶችን የክበብ መሪዎች በማድረግ ነው።

የሥርዓተ-ጾታ ክበብ የትምህርት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ፣ የጾታ እኩልነት ላይ ያለውን ዕውቀት ለማዳበር እና የጾታ እኩልነት ያለበትን ደረጃ ለማሻሻል ጉልህ ሚና ይጫዎታል።

የጾታ እኩልነት ወንዶችን እና ልጃገረዶችን አሳታፊና ሁሉንም ጠቃሚ በመሆኑ የወንዶችን፣ የልጃገረዶችን እና የሴቶችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ይፈልጋል። በዚህም ምክንያት ወንድ መምህራን የሥርዓተ-ጾታ ክበብ አባል ሆነው መሳተፋቸው ወንድ ተማሪዎች በንቃት ክበቡ ውስጥ እንዲሳተፉ ያስችላል። የሥርዓተ-ጾታ ክበብ በአግባቡ ሥራውን እንዲሰራ አዘውትረው መሰብሰብ የሚችሉበት ቦታ እና የሥራ ማስኬጃ በጀት ሊኖረው ይገባል።

ተግባር 2 ማጠቃለያ:- ተግባርና ሳፊነቶች

ወላጅ፣ ተማሪና መምህር ህብረት

የወላጅ፣ ተማሪና መምህር ህብረት አባላት ስብጥር እና ኃላፊነት ላይ የጾታ ምጥጥንን ማረጋገጥ፤

ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራን እና የጉድኝት ማዕከል ሱፐርቫይዘሮች

> **ጠቃሚ መልዕክት:-**
> የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ አካል የሚሆኑ ተግባራት ትምህርት ቤቱን በጾታ ፍትሃዊነት የተሻለ እንዲሆን የሚያስችሉ ዝርዝር እና ሊሳኩ የሚችሉ ግቦች መሆን አለባቸው። የባህርይ ለውጥ ማምጣት ጊዜ እና ቁርጠኛ ሆኖ መሥራትን ይጠይቃል።

ከወላጅ፣ ተማሪና መምህር ህብረት እና መምህራን ጋር የትምህርት ቤትን የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት የመለኪያ ውጤት ካርድን እና የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያ ውጤትን የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ አካል ማድረግ። ትምህርት ቤቱ በጾታ ፍትሃዊነት የተሻለ እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራትን ዕቅዱ ውስጥ ማካተት።

ክለሳና ማጠቃለያ

ይህ ሞጁል የትምህርት ቤት የጾታ ፍትሃዊነት እንዴት እንደሚለካ ቁልፍ ሃሳቦችን በማሳየት እና መምህራን የጾታ ፍትሃዊነትን መሠረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የማስተማር ተግባራት እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ምሳሌ ተካቶበታል። እነዚህ መሣሪያዎች የጾታ ፍትሃዊነትን ለማስፈን ትኩረት በመስጠት መስተካከል

ያለባቸውን ጉዳዮች እንድትረዳ/እንድትረፎ እና የጾታ ፍትሃዊነት የሰፈነበት ትምህርት ቤት ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ያመላክታል፡፡ ዝርዝር እና ሊሳኩ የሚችሉ ተግባራት የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡ የመስኪያ(የጥናት) መሣሪያዎችመሻሻሎችን እና ለውጦችን ለማየት በየጊዜው ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡ የጾታ ፍትሃዊነት የሰፈነበት ትምህርት ቤት የወንድ እና የሴት ተማሪዎችን ምዝገባ፣ አቋርጦ መመለስ፣ የትምህርት ውጤታማነት እና ትምህርት የማጠናቀቅ ምጣኔ ይጨምራል፡፡

ሪድ II የትምህርት ቤት የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ የዳሰሳ ጥናት መስኪያ የውጤት ካርድ

ክልል	ትምህርት ቤት	ቀን
ወረዳ	ምልክታዉን ያደረገው ሰው ሥም/ ማዕረግ	

ህዝብ ነክ ጥናቶች (Demographics)

ተ.ቁ.	አመልካች	ድርሻ (Ratio)	ውጤት አሰጣጥ	ውጤት
1	ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች ለወንድ ተማሪዎች ያላቸው ድርሻ (የሴት ተማሪዎችን ቁጥር ለወንድ ተማሪዎች ቁጥር ማካፈል፤ ሴቶች/ ወንዶች)		ድርሻው ከ0.98 - 1.02 ከሆነ, ውጤት = 2 ድርሻው ከ0.94 - 0.97 ወይም 1.03 - 1.06 ከሆነ, ውጤት = 1 ሌሎች = 0	
2	ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች ለወንድ ተማሪዎች ያላቸው ድርሻ			
3	በሥርዓተ ጾታ ክበብ የሚሳተፉ ሴት ተማሪዎች ለወንድ ተማሪዎች ያላቸው ድርሻ			
4	በሁሉም ክበቦች የሚሳተፉ ሴት ተማሪዎች ለወንድ ተማሪዎች ያላቸው ድርሻ			
5	ሴት መምህራን ለወንድ መምህራን ያላቸው ድርሻ			
6	ሴት የወተመህ አባላት ለወንድ የወተመህ አባላት ያላቸው ድርሻ (ሁሉም ዋና እና ንዑስ ኮሚቴዎች)			
7	ሴት የትምህርት አመራሮች ለወንድ የትምህርት አመራሮች ያላቸው ድርሻ (ሁሉም ርዕሰ መምህር እና ምክትል ርዕሳነ መምህራን ተደምረው)			

የትምህርት ቤት ግብዓቶች					
ተ.ቁ.	አመልካች	አዎ	አይደለም	ውጤት አሰጣጥ	ውጤት
1	ትምህርት ቤቱ ለልጃገረድ እና ለወንድ ተማሪዎች የተለያዩ መጸዳጃ ቤቶች አሉት፤ በር አላቸው?			የተለያየ መጸዳጃ ቤት + በር = 2፣ መጸዳጃ ቤት = 1፣ በአንድ ላይ = 0	
2	መጸዳጃ ቤቱ አጠገብ ሳሙና እና ውሃ አለ?			ሁልጊዜ ሁለቱም አሉ = 2 ውሃ ብቻ አለ፤ ሳሙና የለም = 1 ሁለቱም የሉም = 0	
3	ቢያንስ ለ50 ተማሪዎች አንድ የመጸዳጃ ክፍል (መቀመጫ) አለ?			አለ = 1፤የለም = 0	
4	መጸዳጃ ቤቱ በየቀኑ ለምን ያህል ጊዜ ይጸዳል?			ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ = 1 በየቀኑ አይጸዳም = 0	
5	የወር አበባ ላይ ለሆኑ ልጃገረዶች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ራሱን የቻለ ማረፊያና መጸዳጃ ክፍል አለ?			አለ = 1፤ የለም = 0	
6	በትምህርት ቤቱ ለሁሉም ሴት ተማሪዎች የሚሆን ተደጋግሞ አገልግሎት ላይ የሚውል ወይም ዘመናዊ የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት አለ?			ሁለቱም አለ = 2 ከሁለቱ አንዱ አለ = 1 ምንም የለም = 0	
7	ሴት ተማሪዎች የተጠቀሙበትን የንጽህና መጠበቂያ እንዴት ማስወገድ እንዳለባቸው ዕውቀቱ አላቸው?			አለ = 1፤ የለም = 0	
ደህንነት					
ተ.ቁ.	አመልካች	አዎ	አይደለም	ውጤት አሰጣጥ	ውጤት
1	ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ላይ ቅሬታ የሚያቀርቡ ተማሪዎችን የሚያስተናግድ ኮሚቴ ወይም የተወከለ ሰው አለ?			አለ = 2፤ የለም=0	
2	ሁሉም ተማሪዎች ስለኮሚቴው ወይም ስለተወከለው ሰው ያውቃሉ?			አዎ = 2፤ የለም=0	
3	በትምህርት ቤቱ ወይም በክፍል ውስጥ በተማሪዎች ላይ ግርፋት ይፈጸምባቸዋል?			በፍጹም የለም = 1 አልፎ አልፎ አለ = 0	
4	ትምህርት ቤቱ ዙሪያው የታጠረ ነው?			አዎ ሁሉም ታጥሯል = 1 የለም፣በከፊል ታጥሯል=0	
5	መጸዳጃ ቤቶች በትምህርት ቤቱ አመራሮችና መምህራን በማንኛውም ሰዓት ክትትል ይደረግላቸዋል?			አዎ = 1 የለም=0	

6	በግቢው ውስጥ ያሉ ሁሉም ቦታዎች በትምህርት ቤቱ አመራሮችና መምህራን በየቀኑ ክትትል ይደረግላቸዋል?(በመጸዳጃ ቤቶች ጀርባ፣ በመማሪያ ክፍሎች ጀርባ፣ በመዝናኛ አካባቢዎች ወዘተ)			አዎ፣ ሁሉም ቦታዎች ላይ በየቀኑ ክትትል ይደረጋል=1; በየቀኑ ክትትል አይደረግም=0	
7	ትምህርት ቤቱ ለጥቃት የተጋለጡ ተማሪዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል (ለምሳሌ ለፖሊስ፣ ለሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽህፈት ቤት፣ ለህጻናት እንክብካቤ ክፍል፣ ለጤና ተቋማት ወዘተ)?			አዎ = 1፤ የለም=0	
8	ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን ከጥቃት ለመከላከልና ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ከማህበረሰቡ አካላት ጋር በትብብር ይሠራል?			አለ = 1፤ የለም = 0	
9	ትምህርት ቤቱ ደህንነታቸው ስለተጠበቁ እና አደገኛ ስለሆኑ ቦታዎች ለተማሪዎች መረጃ ይሰጣል?			አዎ = 1፤ የለም = 0	
10	ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡባቸውን መንገዶችክትትል የሚያደርግ ቡድን ከማህበረሰቡ አካላት ተመድቧል? ለሁሉም መንገዶች?			ለሁሉም መንገዶች አለ =2 ለተወሰኑት መንገዶች አለ=1 ምንም የለም = 0	

መምህራን እና መማር ማስተማር

ተ.ቁ.	አመልካች	አዎ	አይደለም	ውጤት አሰጣጥ	ውጤት
1	ሁሉም መምህራን በየቀኑ ከትምህርት ቤት የቀሩ ተማሪዎችን ቁጥር ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጽፋሉ?			አዎ = 1፤ የለም=0	
2	ሁሉም መምህራን ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ጾታዊ ጥቃቶች መከላከያ መመሪያ ስልጠና ወስደዋል ወይም በቂ ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል?			ለሁሉም መምህራን = 2 ለርዕሰ መምህር እና ለተወሰኑት መምህራን = 1 -ምንም የለም =0	
3	መምህራን ባለፉት 3 ወራት የሪድ ‖የክፍል ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ምልከታ መሳሪያን በመጠቀም ምልከታ አድርገው ግብረ መልስ ሰጥተዋል?			ሁሉም መምህራን = 3 75% መምህራን = 2 50% መምህራን = 1 ከ50% በታች መምህራን = 0	

ለችግር ተጋላጭ ተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍ

ተ.ቁ.	አመልካች	አዎ	አይደለም	ውጤት አሰጣጥ	ውጤት
1	በትምህርት ቤቱ ወይም በማህበረሰቡ የትምህርት ቁሳቁስ በማጣት ምክንያት ለሚቸገሩ ተማሪዎች መርጃየሚሆን ገቢ ማስገኛ ልዩ ልዩ ተግባራት አሉ?			አለ = 1፤ የለም = 0	
2	ትምህርት ቤቱ ከሚዘገዩ ወይም ከአቋረጡ ተማሪ ወላጆች ጋር፣ አቋርጠው መመለስ ካለባቸው ተማሪ ወላጆች ጋር እና ከችግረኛ ተማሪዎች ውጤት መሻሻል ጋር በተያያዘ ከወላጆች ጋር በአካል በመገናኘት ይመካከራል (ትምህርት ቤት እና ወደ ቤታቸው በመሄድ)			አዎ ለሁሉም= 1 የለም=0	
3	የማጠናከሪያ ትምህርት ለወንዶችና ለልጃገረዶች እኩልይሰጣል?			አዎ = 1፤ የለም=0	
4	ለሁሉም ከ5-8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሥነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት ከኤች አይቪ/ኤድስ፣ ከተላላፊ የአባላዘር በሽታዎች እና ካልተፈለገ እርግዝና ራሳቸውን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው ትምህርት ይሰጣል?			አዎ = 1፤ የለም=0	

የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት

ተ.ቁ.	አመልካች	አዎ	አይደለም	ውጤት አሰጣጥ	ውጤት
1	ወንዶችና ልጃገረዶች የመጫዎቻ ሜዳዎችን ለእኩል ሰዓት እና በሁሉም ሜዳዎች እኩል ይጠቀማሉ (በጾታ ተለይቶ የተሰጠ ሜዳ የለም)?			አዎ ሁለቱም = 2 አዎ አንዳቸው = 1 የለም = 0	
2	ወንዶችና ልጃገረዶች የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራትእኩል ይሳተፋሉ?(ማስታዎሻ:- ምዝገባ ≠ተሳትፎ)			አዎ = 1፤ የለም = 0	
3	የሥርዓተ ጾታ ክበብ የመሥሪያ ቦታ እና የሥራ ማስኬጃ በጀት አለው?			አዎ ሁለቱም = 2 አዎ አንዳቸው = 1 ሁለቱም የለም = 0	

4	ልጃገረዶችና ወንዶች በተመሳሳይ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራትእኩል ይሳተፋሉ? እንዲሁም ለተግባራቱ የሚያውሉት ጊዜ እኩል ነው?			አዎ ሁለቱም = 1; የለም = 0	
5	ልጃገረዶች ከወንዶች በእኩል መጠን የክፍል አለቃ ሆነው ይመራሉ(ምክትል የክፍል አለቃን ሳይጨምር)?			አዎ = 1፤ የለም = 0	
የሁሉም ውጤቶች ጠቅላላ ድምር					
ውጤቱ ከ45-54 ከሆነ በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነት ከፍተኛ ነው::	ውጤቱ ከ34-44 ከሆነ በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነትን ለማስፈን መሻሻል የሚገባቸው ተግባራት አሉ ማለት ነው::		ውጤቱ ከ34 በታች ከሆነ በትምህርት ቤቱ የጾታ ፍትሃዊነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለሆነ በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል የሚገባቸው ተግባራት አሉ ማለት ነው::		

ሪድ II - የክፍል ውስጥ ምልከታ መሳሪያ አጠቃቀም መመሪያ

የክፍል ውስጥ ምልከታ መሳሪያ መምህራን በክፍል ውስጥ ከሴትና ወንድ ተማሪዎች ጋር በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት የሚያደርጉት መስተጋብር ብዛትና ጥራት ምን ያህል እንደሆነ ለማየት ጠቀሜታ አለው:: ይህን የክፍል ውስጥ ምልከታ መሳሪያ ርዕሰ መምህራን፣ የጉድኝት ማዕከል ሱፐርቫዘሮች፣ የመምህራን አማካሪዎች ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሊጠቀሙበት ይችላሉ::

ምልከታውን በሚፈለገው መንገድ እና ዓላማ ለመሙላት ምልከታ የሚያደርገው አካል በክፍል ውስጥ መሳሪያውን ይዞ/ዛ በመግባት መምህራን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያደርጉትን መስተጋብር ብዛትና ጥራት መሙላት አለበት/አለባት::

የምልከታመሳሪያው በውስጡ ሦስት ክፍሎች አሉት፡-

በክፍል 1:- በመማር ማስተማሩ ትግበራ ወቅት የጾታ እኩልነት ላይ የሚደረግ ምልከታ፤ በመማር ማስተማሩ ትግበራ ወቅት በሚደረጉ ጾታዊ መድሎዎች ላይ ያተኩሩ ጥያቄዎችን የያዘ ነው::

በክፍል 2:- የሠንጠረዥ አሞላል መመሪያዎች (Matrix Instructions) ፤ መምህራን በክፍል ውስጥ ከሴትና ወንድ ተማሪዎች ጋር በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት የሚያደርጉትን መስተጋብር ይገመግማል:: እንዲሁም

በክፍል 3:- የክፍል 1 እና የክፍል 2 ትንተናን ያጠቃልላል::

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የሠንጠረዥ አሞላል ላይ ያተኩራሉ:: የክፍል ውስጥ ምልከታው ቢያንስ አርባ ደቂቃ መውሰድ አለበት:: ነገር ግን ከዚያ በላይ መቆየት ይቻላል::

ከምልከታ በኋላ ለመምህሩ/ሯ እና/ወይም ለርዕሰ መምህሩ/ሯ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል:: ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ እንዴት እንደሚሰጥ የሚያብራራ መመሪያ አለ::

ክፍል 1:- በመማር ማስተማሩ ትግበራ ወቅት የጾታ እኩልነት ላይ የሚደረግ ምልከታ፤

ለጥያቄ ቁጥር 1-11 የሚሰጠው ምላሽ ተገቢ ከሆነ “አዎ”፣ “የለም”፣ “ልጃገረድ”፣ “ወንድ”፣ “ሁለቱም”፣ ወይም “ሁለቱም አይደለም” ነው። አንዳንድ ባህርይዎች በምልከታ የማይታወቁ መሆናቸውን ማስታዎስ ጠቃሚ ነው። በዚህ ጊዜ“ሁለቱም አይደለም” ወይም “መልስ የለም” ማለት ተገቢ ነው።

ክፍል 2:- የሠንጠረዡ አሞላል መመሪያዎች

የመስተጋብር ቁጥር

በዚህ አምድ ውስጥ ያሉ ቁጥሮች ከእያንዳንዱ የመማር ማስተማር መስተጋብር ጋር ይሄዳሉ፤ መምህሩ/ሯ ከሚጠይቁት ጥያቄ ይጀምራል። ለምሳሌ፤ መምህሩ/ሯ ተማሪዎችን ጥያቄ ጠየቀ አንድ ልጃገረድ ተማሪ መለሰች፣ እንደገና መምህሩ/ሯ ተማሪዎችን ተከታይ ጥያቄ ሲጠይቁ የተለየ መስተጋብር ነው ማለት ነው። በተጨማሪ ሌላ ሰው አዲስ ጥያቄ ሲጠይቅ ይህ ሌላ መስተጋብር ይሆናል። ይህም ተማሪዎችን ለመጠየቅ ሊያነሳሳቸው ይችላል። በዚህ ጊዜ ይህ ድርጊት ለብቻ ይመዘገባል። ነገር ግን ተመሳሳይ የምዘና ስልቶችን መጠቀም አለብን (ለምሳሌ፡- የመምህር ግብረ መልስ፣ የጥያቄ ደረጃ)።

የጥያቄ ደረጃ

የመምህሩ/ሯ ጥያቄ ከፍተኛ ደረጃ የሚለካ፣ ዝቅተኛ ደረጃ የሚለካ ወይም ከሥነ- ትምህርት ውጭ ሊሆን ይችላል። ከታች ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡-

ከፍተኛ ደረጃን የሚለካ ጥያቄ:- ጥያቄው ለከፍተኛ ማብራሪያ እና ተሳትፎ የሚዳርግ ነው። ሁለት ዓይነት ከፍተኛ ደረጃ የሚለኩ ጥያቄዎች አሉ። መተንተን (analysis) እና መገምገም (evaluation)።

የመተንተን ጥያቄዎች

ሀሳቦችን ማያያዝ፣ ጥቅሞችና ጉዳቶችን ማወዳደር፣ ተገቢ አስተሳሰቦች ማራመድ እና ምክንያታዊ መሆን ነው። የመተንተን ጥያቄ ቁልፍ ቃላት፡- “አወዳድር/አወዳድሪ”፣ “በየምድባቸው አስቀምጥ/ጭ”፣ “ማጠቃለያ ስጥ/ጭ”

ምሳሌ:- በአጥቢዎች እና በገበሎ አስተኔዎች መካከል ያለውን ልዩነት እና አንድነት አወዳድር/አወዳድሪ።

የመገምገም ጥያቄዎች

ተማሪዎች ከእውነታውን ከማወቅ በዘለለ የራሳቸውን አመዛዝኖ የመወሰን አቅም በትምህርታቸው እንዲያጎለብቱ ያስፈልጋል፣ ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ እና በእውነታ ላይ የተመሠረቱ የመከላከያ ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ስሜታቸውን ብቻ መሆን የለበትም።

ቁልፍ ሀረጎች ወይም ቃላት:- “ምን የመፍትሔ ሀሳቦችን ትጠቁመኛለህ/ ትጠቁሚኛለሽ?”
“በሃሳቡ ትስማማለህ/ትስማሚያለሽ?”
“ስለ... ምን ታስባለህ/ታስቢያለሽ?”
“የትኛው የበለጠ ጠቃሚ ነው ብለህ ታስባለህ/ታስቢያለሽ?”

ምሳሌ:- በኢትዮጵያ የቤተሰብ ደንብ ውስጥ ባሉ ሀሳቦች ትስማማለህ/ትስማሚያለሽ?

ዝቅተኛ ደረጃ የሚለካ ጥያቄ:- የዕውቀት ጥያቄዎች ወይም ትክክል ወይም ስህተት ተብለው የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው። ተማሪዎች እውነታዎችን ብቻ ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል።

ቁልፍ ቃላት:- ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ እና እንዴት? ወይም "አብራራ/አብራሪ ..."

ምሳሌዎች:- የ5 እና የ7 ድምር ስንት ነው? በዚህ ታሪክ ውስጥ መሪ ቀስቃሽ ማን ነበር?

ስነ-ትምህርታዊ ያልሆኑ ጥያቄዎች:- ተማሪዎች ከተማሩት ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች ናቸው። ለምሳሌ:- የተማሪዎች ንጽህና አጠባበቅ ወይም ባህርይ።

ማን ምላሽ ሰጠ?

ማን ምላሽ እንደሰጠ ማስታዎሻ መያዝ:- የጾታ ስብጥር ያለው የተማሪዎች ቡድን (2 ወይም ከ2 በላይ, በአንድ ላይ)፣ ልጃገረድ ወይም ወንድ።

አንድ ተማሪ ጥያቄ ከጠየቀ፤ ልክ እንደቁጥር ነክ ያልሆኑ መረጃዎች ይህን በማስታዎሻ ጀርባ መመዝገብ (ለምሳሌ የመምህር ግብረ መልስ፣ የጥያቄ ደረጃ)

ተማሪ እጅ ሲያወጣ/ስታወጣ

መምህር እጅ ያወጣውን ተማሪ ወይስ የማይሳተፈውን/ የማትሳተፈውን ፈልገው ይመርጣሉ?

ተማሪ ከመምረጣቸው በፊት የሚሠጡት የማሰቢያ ጊዜ

ይህ በተጠየቀው ጥያቄ እና መልስ የሚመልስ/ የምትመልስ ተማሪ እስከሚመረጥ/ እስከምትመረጥ ድረስ ያለው የጊዜ ርዝማኔ ነው። ተማሪዎች የተመረጡት "ምንም የለም" (የማሰቢያ ጊዜ የለም)፣ "ከ2-5 ሰከንዶች" ወይም "ከ5 ሰከንዶች በላይ" ነው የሚለውን ማስታዎሻ መያዝ ተገቢ ነው።

የሥም አጠቃቀም

መምህር ተማሪን በሚመርጡበት ወይም ለተማሪ ግብረ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የተማሪዎችን ሥም መጥራት አለመጥራታቸውን ማስታዎሻ መያዝ ተገቢ ነው።

እንዲመልስ/እንድትመልስ ለተመረጠው/ለተመረጠችው ተማሪ የተሠጠ የማሰቢያ ጊዜ

አንዳንድ ጊዜ በተለይ ዓይነአፋር ተማሪዎች(በአብዛኛው በልጃገረዶች ያመዝናል) ሀሳባቸውን ለማሰባሰብ እና ምላሻቸውን ለመናገር የተወሰነ ሰከንዶችን ዘግይተው ሊናገሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ "ምንም የለም"(የማሰቢያ ጊዜ የለም)፣ "ከ2-10 ሰከንዶች" ወይም "በቂ ጊዜ" (ከ10 ሰከንዶች በላይ) የሚለውን ማስታዎሻ መያዝ ተገቢ ነው።

ተማሪ ወደ ሰሌዳ ሲሄድ/ስትሄድ

ተመሪው/ተማሪዋ ወደሰሌዳ ሥራውን/ሥራዋን ለማሳየት ሂዷል/ሂዳለች? (አዎ ወይም የለም)

የመምህር ግብረ - መልስ

ተማሪዎች መልስ በሚሰጡበት ወቅት መምህር እንዴት አስተያየት/ግብረ-መልስ እንደሚሰጡ ማስታዎሻ መያዝ፤ የክፍል ውስጥ መረጃ ሰብሳቢው/ዋ የሚከተሉትን መተግበር አለመተግበራቸውን ማረጋገጥ ይችላል/ትችላለች:: ወይም የመምህሩ/ሯ ግብረ - መልስ ከነዚህ የማይመደብ መሆኑን ከመረጃ መሰብሰቢያ ወረቀቱ ጀርባ መግለጽ አለበት/ባት::

ግብረ - መልስ የለም:- መምህር ምንም የቃል ወይም ከቃል ውጭ የሆነ አስተያየት አልሰጡም::

አቀባበል:- በመምህሩ/ሯ ይህ ነው የማይባል አስተያየት ከሆነ የተሰጠው፤ ለአብነት "እ…እህ" ወይም እሺ"::

የአመላለስ ስልቱን መሰረት አድርጎ የማበረታቻ አስተያየት ሲሰጥ:- መምህሩ/ሯ የአመላለስ ስልቱን መሰረት አድርገው የማበረታቻ አስተያት የሚሰጡበት መንገድ ማለት ነው:: ይህ ሰዋስው ላይ ሊሆን ይችላል (ጥያቄው ሰዋስው ላይ ያተኮረ ካልሆነ)፣ የእጅ ጽሁፍ (ሰሌዳ ላይ የተጻፈ ከሆነ) ወይም እንዴት እንደተባለ/እንደተመለሰ:: ምሳሌ:- "በጣም ጥሩ:: ግሱን በግልጽ እና በትክክል ተናግረኸዋል/ተናግረሽዋል:: " (ግስ የተጠየቀው ጥያቄ ትኩረትና ዓላማ አለመሆኑን መገመት)

የመልሱን ይዘት መሠረት አድርጎ የማበረታቻ አስተያት ሲሰጥ:- መምህሩ/ሯ የመልስ ይዘቱን መሠረት አድርገው የማበረታቻ አስተያየት የሚሰጡበት መንገድ ነው:: መምህሩ/ሯ በተማሪ የተሰጠው ምላሽ ትክክል መሆኑን ወይም ከፍተኛ ደረጃን የሚለካ ጥያቄ ከሆነ ተማሪው/ዋ ለመመለስ ያደረገውን/ጥረት እና አስተሳሰብ ማበረታታት:: ምሳሌ:- "በጣም ጥሩ:: ማህበረሰቡ አካባቢውን እንዴት መጠበቅና መንከባከብ እንዳለበት የሰጠኸውን/የሰጠሽውን አስተያየት ወድጀዋለሁ:: "

ከፍተኛ ደረጃ የሚለካጥያቄን መመርመር:- መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በተጨማሪነት ስለትምህርቱ ጠለቅ አድርገው እንዲመረምሩ ወይም ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ሲያደርጉ ነው::

ለምሳሌ:- "በትክክል:: ነጭ አውራሪስ በቅርቡ በመጥፋት ላይ ያለ እንስሳ ነው:: ሰዎች እንዴት መጠበቅና መንከባከብ እንዳለባቸው ምን ታስባለህ?"

አሉታዊ አስተያየት:- መምህሩ/ሯ ተማሪዎችን የሚያሸማቅቅ አስተያየት የሚሰጡ ከሆነ አስተያየቱ አሉታዊ አስተያየት ነው::

ለምሳሌ:- "የቤት ሥራህን በአግባቡ አልሰራህም፤ የበለጠ ማወቅ አለብህ:: " ወይም

ለምሳሌ:-"ደደብ ነህ/ሽ! ሥራህን በትክክል መሥራት አለብህ/ሽ"

የክፍል ተማሪዎችን አስተያየት እንዲሰጡ መጠየቅ:- በተማሪው/ዋ ስለተሰጠው መልስ ትክክል መሆን አለመሆን የክፍል ተማሪዎችን አስተያየት እንዲሰጡ መጠየቅ ነው::

በተማሪው/ዋ የተሰጠው ምላሽ ላይ ያለውን ስህተት ራሳቸው እንዲያፈላልጉ ማድረግ ተማሪዎች የበለጠ እንዲነሳሱ ማድረግ የሚያስችል የማስተማር ስልት ነው::

ለምሳሌ:- "የራስህን/ሽን የመጀመሪያ አንቀጽ በትኩረት ተመልከት እና ያልተሟላውን ዓረፍተ ነገር ፈልግ/ጊ:: "

ይህ ሰንጠረዡ ውስጥ አልተካተተም ነገር ግን ይህ ስልት ሲተገበር የጾታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማስታዎሻ መያዝ አለበት::

ከተማሪዎች ያለው ርቀት

ተማሪው/ዋ መልስ በሚመልስበት/ በምትመልስበት ጊዜ መምህሩ/ሯ ከተማሪ ያለው/ያላት ርቀት 1 ሜትር ወይም ከ1 ሜትር ያነሰ ወይም ከ1 ሜትር በላይ ሊሆን ይችላል። መምህሩ/ሯ ወደ ተማሪው/ዋ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት ከሆነ አይቆጠርም።

የመምህሩ/ሯ የሰውነት ቋንቋ/ እንቅስቃሴ

መምህሩ/ሯ ከተማሪዎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር ወቅት የሚያሳዩት የሰውነት ቋንቋ/ እንቅስቃሴ ሲሆን የተወሰኑ ምሳሌዎች ቀጥሎ ቀርበዋል።

አዎንታዊ፡-

- ፈገግታ፣
- መስማማትን/ አለመስማማትን ራስን በማንቀስቀስ መግለጽ፣
- በዓይን መከታተል፣
- መምህሩ/ሯ በሚናገሩበት ወቅት የተማሪዎች በጎ አቀባበል፣
- ሌሎች አዎንታዊ አካላዊ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ የእጅ አውራጣትን ለአድናቆት ወደላይ ማንሳት)

አሉታዊ፡-

ግንባርን መቋጠር ወይም አሉታዊ የፊት ገጽታ አገላለጽ፣ ፊትን መዞር ወይም ከተማሪው/ዋ መራቅ፣ በተማሪው ላይ እጅን ማወዛወዝ።

ገለልተኛ፡- ምንም አካላዊ እንቅስቃሴ በመምህሩ/ሯ ካልታየ፤

ክፍል 3:- የትንተና መመሪያዎች

ትንተና ክፍል I

ለእያንዳንዱ የመልስ ዓይነት የተለያየ ተራ ቁጥር መጻፍ (ማለትም “የለም” እና “አዎ”የሚል መልስ ያላቸው ጥያቄዎች ወዘተ)

ቁልፍ ማብራሪያዎች መካከለኛው የሠንጠረዥ አምድ ላይ ተካቷል።

መምህሩ/ሯ የጾታ እኩልነትን በትክክል በመማር ማስተማሩ ወቅት ከተገበሩ የመልሶቹ አቀማመጥ እንደሚከተለው ይሆናል። በተራ ቁጥሮቹ እና በምላሾቹ መካከል መለያየት ካለ መምህሩ/ሯ ማስተካከል ያለባቸው ተግባራት አሉ ማለት ነው።

በክፍል ውስጥ የጾታ እኩልነትን በሚከተሉት ነጥቦች አማካኝነት መመልከት ያስፈልጋል፦		ምልከታዎች
ምላሽ	**ተራ ቁጥር**	**ተራ ቁጥሮች**
የለም	1, 6, 7, 11	
አዎ	4, 5, 8	
ሁለቱም	2, 3, 9, 10	
ከሁለቱም ውጭ	3	

ትንተና ክፍል II

የመለኪያ መሣሪያው ውስጥ ያለውን ሠንጠረዥ መጠቀም። ለእያንዳንዱ 10 የምልከታ ምድቦች(10 አምዶች)፣ ለእያንዳንዱ ጾታ የተሰጡ መልሶችን በዓይነት በዓይነት በመለየት መቁጠር፤ የጾታ እኩልነትን በትክክል በመማር ማስተማሩ ወቅት ከተተገበረ የመልሶች ቁጥር በየምልከታ ምድቦች ለልጃገረዶች እና ለወንዶች እኩል መሆን አለበት (በክፍል ውስጥ የልጃገረዶች እና የወንዶች ቁጥር እኩል ነው እንበል)። በልጃገረዶች እና በወንዶች መካከል ልዩነት ካለ መምህሩ/ሯ የማስተካከያ ሥራዎችን ለይቶ መተግበር ያስፈልጋል።

የመምህር ግብረ-መልስ መመሪያዎች.

ምልከታው ከተጠናቀቀ በኋላ መረጃ ሰብሳቢው/ዋ መምህሩን/ሯን ከክፍል ወዲያው እንደወጡ ለማነጋገር መጠየቅ አለበት/ባት። የክፍል ውስጥ ምልከታው ዓላማ የመምህራንን ባህርይ እና የማስተማር ክህሎት በተለይም ወንድ እና ልጃገረድ ተማሪዎችን በእኩል ለመያዝና ለመርዳት የሚያደርጉትን ጥረት ለማሻሻልና ለመርዳት መሆኑን መግለጽ ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም ይህ የአጭር ጊዜ ምልከታ በመሆኑ ሙሉ የማስተማሩን ገጽታ የማያሳይ አለመሆኑን ማስረዳት ጠቃሚ ነው። በሌላ በኩል ውይይቱ አዎንታዊ እንዲሆን፦

በመጀመሪያ መረጃ ሰብሳቢው/ዋ በአዎንታዊ አስተያየቶች መጀመር አለበት። በመቀጠል መረጃ ሰብሳቢው/ዋ ሠንጠረዡ ላይ በተሞላው እያንዳንዱ የልጃገረዶች እና የወንዶች መገምገሚያ ነጥብ ላይ መወያየት አለባቸው። ከዚያም በመማር ማስተማሩ ወቅት ወደፊት መስተካከል ስለአለባቸው ጉዳዮች መዘርዘር ያስፈልጋል። መረጃ ሰብሳቢው/ዋ የመረጃ ውጤቱን መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥየጾታ እኩልነት በመማር ማስተማር ሂደቱ እንዴት መተግበር እንዳለበት አስተያየት መስጠት አለበት/ባት። መረጃ ሰብሳቢው/ዋ የተሰጠው ግብረ-መልስ ላይ መምህሩ/ሯ አስተያየት ካለው እንዲሰጥ/እንድትሰጥ መጠየቅ አለበት። መረጃ ሰብሳቢው/ዋ እና መምህሩ/ሯ በጋራ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል የማሻሻያ ዕቅድ በማቀድ ሁለታቸውም ተፈራርመው ያቀዱበትን ቀን ያስቀምጣሉ።

ሪድ II - በክፍል ውስጥ የጾታ እኩልነት ምልከታ መሣሪያ

ክልል	**ትምህርት ቤት**	**ቀን**
ወረዳ	**የተመልካቹ ሥም**	
መምህር	**ክፍል**	**ጾታ (ወንድ/ሴት)**

መመሪያዎች፡- ክፍል I እና II በአግባቡ ያንብቡ። በመጀመሪያ የክፍል II ሠንጠረዥ (ክፍል II: የመምህር ተማሪ መስተጋብሮች ሠንጠረዥ) መሞላት አለበት። እንዲሁም በክፍል I ያለውን ምልከታ ቅጽ ጎን ለጎን ጊዜ በፈቀደ መጠን መሙላት። (በመማር ማስተማሩ ትግበራ ወቅት የጾታ እኩልነት ምልከታ) ክፍል II ተሞልቶ ሲጠናቀቅ በክፍል I የቀረውን ሞልተው ያጠናቁ።

ማስታዎሻ፡- በክፍል I ያሉ ሁሉም የመማር ማስተማር ተግባሮች ምልከታ ላይደረግባቸው ይችላል። ምልከታ ካልተካሔደ "መልስ የለም" የሚል ምላሽ ያስቀምጡ።

ተ.ቁ	ክፍል I፡- በመማር ማስተማሩ ትግበራ ወቅት የጾታ እኩልነት ምልከታ	መልስ (አዎ/የለም) (ልጃገረዶች/ወንዶች/ ሁለቱም/ከሁለቱም ውጭ/መልስ የለም)	እባክዎ ዝርዝር ማብራሪያ ይጻፉ
1	በክፍል ውስጥ ለልጃገረዶች እና ለወንዶች የተለየ መቀመጫ ወይም ቡድን አለ ወይ? (በመምህሩ/ሯ ወይም በራሳቸው በተማሪዎች የተሰየመ) (አዎ/የለም)		
2	የሚሰሩ ተግባሮችን ለመምራት የሚጠየቀው ማን ነው ልጃገረዶች፣ ወንዶች፣ ሁለቱም፣ ከሁለቱም ውጭ(ለምሳሌ፡ - የክፍል አለቃ፣ የቡድን ሥራ)? መልሱ "ከሁለቱም ውጭ" ከሆነ፣ ተማሪዎች በራሳቸው የሚመራቸውን ከሰየሙ በመጨረሻው አምድ ላይ ማስታዎሻ ይጻፉ።		
3	መምህሩ/ሯ ከማን ጋር የበለጠ ግንኙነት አላቸው ከልጃገረዶች ጋር፣ ከወንዶች ጋር፣ ከሁለቱም ጋር ወይም ከሁለቱም ውጭ (ለምሳሌ፡- በመቀለድ፣ በግል በመነጋገር፣ በቤተሰባዊነት)?		
4	መምህሩ/ሯ በመማር ማስተማሩ ወቅት የወንድ እና የሴት ምሳሌዎችን ይጠቀማሉ (ለምሳሌ፡- ሴት/ወንድ ዶክተር፣ ሴት/ ወንድ ተማሪ ወዘተ)? (አዎ/የለም/መልስ የለም)		
5	መምህሩ/ሯ በመማር ማስተማሩ ወቅት የወንድ እና የሴት ተውላጠሥሞችን እኩል ይጠቀማሉ? (አዎ/የለም/መልስ የለም)		

6	መምህሩ/ሯ በመማር ማስተማሩ ወቅት ልጃገረዶችን እና ወንዶችን ለመግለጽ በእኩል ድርሻ በመስጠት ይጠቀማሉ(ለምሳሌ፡- የቤት ሠራተኛነት፣ ሩህሩህ፣ ታዛዥ፣ ዝምተኛነት፣ ዓይን አፋርነት ወዘተ…)? (አዎ/የለም)		
7	መምህሩ/ሯ በመማር ማስተማሩ ወቅት ህጻናት እና አዋቂ ወንዶችን ለመግለጽ በእኩል ድርሻ በመስጠት ይጠቀማሉ (ለምሳሌ፡- አስተዳዳሪ፣ ጠንካራ፣ ተቆጣጠሪ፣ ዝምተኛነት፣ ዓይን አፋርነት ወዘተ…)? (አዎ/የለም)		
8	መምህሩ/ሯ በመማር ማስተማሩ ወቅት ከሁለቱ አንዱን ጾታ ልማዳዊ ባልሆነ መንገድ ይገልጻሉ (ለምሳሌ፡- ልጃገረዶች ጠንካራ፣ ባለሙያዎች ወዘተ… ናቸው፤ ወንዶች ተሸካሚ፣ የተገኙ ተራ ሥራዎችን የሚሰሩ ወዘተ… ናቸው)? (አዎ/የለም)		
9	መምህሩ/ሯ በክፍል ውስጥ ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ በብዛት የሚያበረታቱት ልጃገረዶችን ነው ወይስ ወንዶችን? (አዎ/የለም)		
10	መምህሩ/ሯ በክፍል ውስጥ ባህርያቸውን መሠረት በማድረግ በብዛት የሚያበረታቱት ልጃገረዶችን ነው ወይስ ወንዶችን? (አዎ/የለም)		
11	መምህሩ/ሯ በክፍል ውስጥ አካላዊ ጥቃት ይጠቀማሉ (መግጨት፣ በጥፊ መምታት)፣ በቃል ይሳደባሉ (መስደብ፣ መቀለድ) ወይም አካላዊ ቅጣት ይፈጽማሉ (ተማሪዎችን ማንበርከክ፣ ማቆም)? (አዎ/የለም)		
12	በተማሪዎች መካከል መጠቃቃት፣ መቀላለድ፣ መበሻሸቅ አለ (ከነበር ወንዶች ወይም ሴቶች መሆናቸውን ማሳታዎሻ ይይዙ)? (አዎ/የለም)		
13	ከነበር መምህሩ/ሯ በምን መንገድ ምላሽ ሰጡ?		
14	በመማር ማስተማሩ ወቅት ሌሎች የተለዩ ተግባሮች ካሉ ማስታዎሻ ይያዙ (ለምሳሌ፡- የዘወትር ሥራ፣ ከክፍል እንዲወጡ መፍቀድ፣ አካላዊ ወይም ሌላ ቅጣት፣ ወዘተ…)		

ክፍል II: የመምህር ተማሪ የመማር ማስተማር መስተጋብር መመዝገቢያ ሠንጠረዥ (የአጠቃቀም መመሪያውን ይመልከቱ)

የመስተጋብር ቁጥር	1. የጥያቄ ደረጃ			2. ማን ምላሽ ሰጠ?			3. እጅ ያወጣ ተማሪ አለ?		4. ተማሪ ከመመረጡ በፊት የተሠጠ የማሰቢያ ጊዜ			5. በሥም ተማሪዎች ይጠራሉ?		6. ለመልስ ለተመረጠ ተማሪ የተሠጠ የማሰቢያ ጊዜ			7. ወደ ሰሌዳ የሄደ ተማሪ አለ?		8. የመምህር ግብረ-መልስ (ሁሉም የሚተገበሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ)							9. ከተማሪዎች ያለው ርቀት		10. የመምህሩ/ሯ የሰውነት ቋንቋ/ እንቅስቃሴ		
	ከፍተኛ	ዝቅተኛ	ሥነ - ትምህርታዊ ያለሆኑ ጥያቄዎች	በጋራ ሁለቱም ጾታዎች	ልጃገረድ	ወንድ	አዎ	የለም	የለም	ከ2-5 ሰከንዶች	በቂ (> 5 ሰከንድ)	አዎ	የለም	የለም	ከ2-10 ሰከንዶች	በቂ (> 10 ሰከንድ)	አዎ	የለም	ግብረመልስ የለም	አቀባበል	በአመላለስ ስልቱ የማበረታቻ አስተያየት ሲሰጥ	የመልሱን ይዘት መሠረት አድርጎ የማበረታቻ አስተያየት ሲሰጥ	ከፍተኛ ደረጃ የሚለካ ጥያቄን መመርመር	አሉታዊ አስተያየት	የክፍል ተማሪዎችን አስተያየት እንዲሰጡ መጠየቅ	1 ሜትር ወይም በታች	ከ1 ሜትር በላይ	አዎንታዊ	አሉታዊ	ገለልተኛ
1																														
2																														
3																														
4																														
5																														
6																														
7																														
8																														
9																														
10																														
11																														
12																														
13																														
14																														

15																														
16																														
17																														
18																														
19																														
20																														
21																														
22																														
23																														
24																														
25																														
26																														
27																														
28																														
29																														
30																														
31																														
32																														
33																														
34																														
35																														
36																														
37																														
38																														
39																														
40																														
ድምር																														

ትንተና ክፍል I

በክፍል ውስጥ የጾታ እኩልነትን በሚከተሉት ነጥቦች አማካኝነት መመልከት ያስፈልጋል፡-		ምልከታዎች
ምላሽ	**ተራ ቁጥር**	**ተራ ቁጥሮች**
የለም	1, 6, 7, 11, 12	
አዎ	4, 5, 8	
ሁለቱም	2, 3, 9, 10	
ከሁለቱም ውጭ	3	

ትንተና ክፍል II

ተ.ቁ	የመገምገሚያ መስፈርት	ምድብ	ልጃገረዶች	ወንዶች
1	የጥያቄ ደረጃ	ከፍተኛ		
		ዝቅተኛ		
		ሥነ - ትምህርታዊ ያልሆኑ ጥያቄዎች		
2	ምላሽ የሰጡ ወንዶች/ልጃገረዶች ጠቅላላ ብዛት፡-			
3	መልስ የሚሰጥ ተማሪ ሲመረጥ እጅ ያወጡ ወንዶች/ልጃገረዶች ጠቅላላ ብዛት፡-			
4	ተማሪ ከመመረጡ በፊት የተሠጠ የማሰቢያ ጊዜ	የለም		
		2-5 ሰከንዶች		
		በቂ (> 5 ሰከንድ)		
5	መልስ የሚሰጥ ተማሪ ሲመረጥ በሥም የተጠሩ ተማሪዎች ወንዶች/ልጃገረዶች ጠቅላላ ብዛት፡-			
6	ለመልስ ለተመረጠ ተማሪ የተሠጠ የማሰቢያ ጊዜ	የለም		
		ከ2-10 ሰከንዶች		
		በቂ (> 10 ሰከንድ)		
7	ወደሰሌዳ የሄዱ ወንዶች/ልጃገረዶች ጠቅላላ ብዛት፡-			
8	የመምህር ግብረ-መልስዓይነት በጾታ	ግብረመልስ የለም		
		አቀባበል		
		በአመላለስ ስልቱ የማበረታቻ አስተያየት ሲሰጥ		
		የመልሱን ይዘት መሠረት አድርጎ የማበረታቻ አስተያየት ሲሰጥ		
		ከፍተኛ ደረጃ የሚለካ ጥያቄን መመርመር		
		አሉታዊ አስተያየት		
		የክፍል ተማሪዎችን አስተያየት እንዲሰጡ መጠየቅ		
9	መምህሩ/ሯ መልስ ከሚሰጠው/ ከምትሰጠው ተማሪ ያለው ርቀት	1 ሜትር ወይም በታች		
		ከ 1 ሜትር በላይ		
10	የመምህሩ/ሯ የሰውነት ቋንቋ/ እንቅስቃሴ	አዎንታዊ		
		አሉታዊ		
		ገለልተኛ		
የመምህር ግብረመልስ ላይ የአጠቃቀም መመሪያውን ይመልከቱ።				

ክፍል 2፡- ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የጾታ ጥቃቶችን የሚከላከል ኮሚቴ እንዴት ይቋቋማል፤ ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ

በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ጾታ ዳይሬክቶሬት መመሪያ መሠረት ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የጾታ ጥቃቶችን የሚከላከል ኮሚቴ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ (የትምህርት ሚኒስቴር ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የጾታ ጥቃቶችን መከላከል መመሪያን ይመልከቱ)፡፡ ኮሚቴው 7 አባላትን ያካትታል፡፡ ተማሪዎችን፣ የትምህርት አመራሮች፣ መምህራን፣ የመምህራን ማህበር ተወካዮች እና ወተመህን ያጠቃልላል፡፡

የኮሚቴው ሚና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ከትምህርት ቤት ጋር ስለተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶች ግንዛቤ መፍጠር እና ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ መከላከል እንዲሁም ለጥቃቶች ምላሽ መስጠት ነው፡፡ በብዙ ትምህርት ቤቶች ጾታዊ ጥቃቶች ሪፖርት አይደረጉም፡፡ ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው ለማመልከት አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም ለደረሰባቸው ጥቃት ተገቢ የሆነ ምላሽ እናገኛለን ብለው አያምኑም፤ ጥቃቱን ቢያሳውቁ አጥቂያችን ይበቀለናል ብለው ይጨነቃሉ፡፡ ኮሚቴው በትምህርት ቤት መኖሩ በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጭ ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል እና ለጥቃቶች ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡

ኮሚቴው እንዴት ይዋቀራል? ከተዋቀረ በኋላ ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ የመከላከል እና ለጥቃቶች ምላሽ በአግባቡ እንዴት መስጠት ይችላል?

ኮሚቴውን ለማዋቀር ሁለት ተግባሮችን ማከናወን ያስፈልጋል፡-

1. የኮሚቴውን አባላት በትምህርት ቤት ማስመረጥ
2. ጾታዊ ጥቃት እና የከፋ አካላዊ ጥቃት ለደረሰባቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለይቶ መዘርዘር

ሁለቱን ተግባሮች ለመፈጸም መከተል ስላለብን ቅደም ተከተሎች፣ የኮሚቴ አባላት ሚናዎች እና ተግባርና ኃላፊነቶች ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

1. የኮሚቴውን አባላት በትምህርት ቤት ማስመረጥ

ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ ሰጭ ኮሚቴ መቋቋም ያለበት በተማሪ ተወካዮች እገዛ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ተማሪዎች በኮሚቴዎች ላይ ሙሉ እምነት ያድርባቸዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ኮሚቴው ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ይቸገራል፡፡ ስለምርጫው የትምህርት ቤትጠቅላላ ስብሰባ ላይ መነገር አለበት፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በክፍላቸው ውስጥ በምርጫው ላይ የራሳቸወስን ድምጽ መስጠት አለባቸው፡፡

ኮሚቴው ውስጥ የሚመረጡ አባላት ጾታ የተመጣጠነ ወይም የሴቶች ቁጥር ከወንዶቹ የበለጠ መሆን አለበት፡፡ ሁሉም የኮሚቴ አባላት ጾታዊ ጥቃቱን በአግባቡ መከላከል እና የመፍትሄ አካል መሆን የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ በአብዛኛው ህጻናት ወሳኝ እና ወቅታዊ መረጃዎችን ከእነሱ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ላላቸው ጎልማሶች ወይም ለሴቶች መስጠትን ይመርጣሉ፡፡

ከኮሚቴው አባላት ውስጥ ከተማሪዎች ጋር እየተገኛኙ መረጃ የሚሰበስቡ/ የሚቀበሉ አንድ ወንድ አባል እና አንድ ሴት አባል ይመረጣሉ፡፡ ሁለቱ ተመራጮች ሁልጊዜ በትምህርት ሰዓት ትምህርት ቤት መሆን አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ መምህራን ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ሁለቱ አባላት ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ አሰጣጥ ላይ የሰለጠኑ ቢሆኑ የተሻለ ነው፡፡

የተመረጡ አባላት ኃላፊነታቸውን በሚረከቡበት ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንዋና ዋና ባህርያት እና ተግባሮች እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

- ተማሪዎች ስለተመረጡ የኮሚቴ አባላት እና አባላት በጥቆማ ስለሚቀበሏቸው የጥቃት ዓይነቶች በቂ ግንዛቤ እንዳላቸው ማረጋገጥ።
- ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስተማማኝ የጾታዊ ጥቃቶች ሪፖርት አቀባበል ስልት መዘርጋት ወሳኝ ነው። ጥቃት ለደረሰባቸው እና ለምስክሮቹ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ይጠበቃል።

የጾታዊ ጥቃቶች ላይ ጥቆማዎችን በምንቀበልበት ጊዜ ሦስቱን “C”ዎች ማስታዎስ አለብን፡-

ርህራሄ (Compassion)

- ብዙ ከማውራት ሁልጊዜ ማዳመጥ፣
- ወቀሳን በመተው ጥያቄዎችን ብቻ ይጠይቁ (ተጠቂዋ/ው ምን ለብሳ/ሶ እንደነበር ወይም ጥቃቱን እንዲፈጽም በምን እንዳነሳሳችው/ እንዳነሳሳት በፍጹም አይጠይቁ)
- ተጠቂዋ/ው ላይ በደረሰው ጥቃት ማዘንዎን እና የእሷ/የእሱ ስህተት እንዳልሆነ ይንገሯት/ይንገሩት።

ብቃት (Competency)

- ሪፖርት ለማድረግ የሚያስፈልጉ እያንዳንዱን ሂደቶች ለተጠቂዋ/ው ይንገሩ እና ወደ ዝርዝር ሪፖርቱ ከመግባታችሁ በፊት ፈቃደኛነቷን/ፈቃደኛነቱን ያረጋግጡ፣
- ጥቃቶች ላይ የተደነገጉ የኢትዮጵያ ህጎችን ይወቁ፣
- በቅርብ ያሉ ብቃት ያላቸውን የህክምና እና የምክር አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማትን ይወቁ፣
- የተፈጸመውን ጥቃት ለፖሊስ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንዳለብዎት ይወቁ።

ምስጢራዊነት (Confidentiality)

- እርስዎ እና ተጠቂዋ/ው ብቻ ራሱን በቻለ ክፍል ውስጥ የምትወያዩ መሆናችሁን እርግጠኛ ይሁኑ። ሌላ የሚሰማችሁ ሰው ከውስጥም ከውጭም መኖር የለበትም።
- ከራሷ/ሱ ፍቃድ ውጭ ስለጥቃቱ ለማንም እንደማይናገሩ ለተጠቂዋ/ው ያረጋግጡላት/ለት (ለርዕሰ መምህር ወይም ለኮሚቴው መረጃውን ማቅረብ የግድ አስፈላጊ ከሆነ የተጠቂውን ሥም ከራሷ/ሱ ፍቃድ ውጭ እንደማይገልጹ ያስረዱ)።

ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ለደረሱ ጾታዊ ጥቃቶች ምላሽ አሰጣጥ፡-

ለደረሱ ጾታዊ ጥቃቶች ምላሽ የሚሰጥበት መንገድ እንደጥቃቱ ደረጃ እና እንደ ጥቃት ፈጻሚው ማንነት ይወሰናል። የተፈጸሙ ሁሉም ጾታዊ ጥቃቶች ለፖሊስ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። እንዲሁም ተጠቂዋ/ው በአስቸኳይ የህክምና እና የምክር አገልግሎት ማግኘት አለባቸው። የተፈጸሙ ከባድ አካላዊ ጥቃቶችም በሙሉ ለፖሊስ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። ከተጠቂዋ/ው ጋር በመተባበር ወላጆች እንዲነገራቸው በማድረግ በጉዳዩ ላይ አብሮ ማሳተፍ። ከኮሚቴው ጋር በጉዳዩ ላይ በመመካከር በተሻለ መንገድ መወሰን (ሁል ጊዜ ምስጢር መጠበቅ አለበት)።

የህጻናትን ደህንነት ሁልጊዜ ልብ ማለትና ማስታወስ እንዲሁም ህጻናቱን እና ወላጆችን በውሳኔዎች ላይ ማሳተፍ ያስፈልጋል።

በተደጋጋሚ ጥቃት በመፈጸም የሚታወቁ ግለሰቦች ወይም የትምህርት ቤቱ አመራሮች የተፈጸሙ ጥቃቶች አያያዝ ላይ በፍጹም አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን የለባቸውም።

እጅግ አሰቃቂ የጥቃት ገጠመኞች በትምህርት ቤቱ የሥራ ውጤታማነት ላይ ጫና ስለሚፈጥር ኮሚቴው እና የተመረጡ አባላት ተጠቂዎችን መዳናቸውን በተከታታይ በመጠየቅ ማረጋገጥ አለብን።

በተጨማሪም የጥቃት ጥቆማዎችን ከመቀበል ባሻገር ኮሚቴው ተገዶ የመደፈር ጥቃት ለደረሰባቸው ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለይቶ በመዘርዘር ማስቀመጥ (ተግባር 2) እና ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ስለሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶች የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ (ተግባር 3) ያስፈልጋል።

አዕምሯዊ ጥቃት

(መበጥበጥ፣ መሳደብ፣ ማስፈራራት፣ ቸል ማለት፣ በተቀፅላ ሥም መጥራት) የአዕምሮ ጥቃት አካል ናቸው። በመሆኑም በንቃት ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት አዕምሯዊ ጥቃት ከጾታዊ ወይም አካላዊ ጥቃቶች የበለጠ በሰው ልጆች ላይ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አካላዊ እና ስሜታዊ የጤና ችግር ይፈጥራል። ያለዕድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት የአዕምሯዊ ጥቃት አካል ናቸው።

ተግባር 1 ማጠቃለያ:- የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነቶች

ርዕሰ መምህር

- ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ ሰጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ግልጽ፣ ከመድሎ ነጻ የሆነ እና ተማሪዎች በምርጫው ላይ ተገቢ ድምጽ የሰጡበት መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የኮሚቴውን ሥራ ሙሉ ትኩረት ሰጥቶ መደገፍ እና የሥራቸውን እውነተኛነት ማረጋገጥ፣
- ከተቻለ እንደኮሚቴ አባል ሆኖ ማገልገል፤ ነገር ግን ተመራጭ አባል አይደሉም፣
- የትምህርት ቤቱ መምህራን እና ሠራተኞች ጥቃት የሚያስከትለውን ጫና ተረድተው ተግባሩን በመከላከል እያገዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

መምህራን

- ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶች መለየትና መከላከል ላይ በንቃት መሳተፍ፣
- ስለኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት ግንዛቤ መፍጠር፣
- ኮሚቴውን በልዩ ልዩ ሥራዎች ማገዝ፣
- ተማሪዎች ጥቃቶችን እንዲያሳውቁ ማበረታታት፣
- ጥቃቶችን መለየት እና ለኮሚቴው ስለጉዳዩ ሪፖርት ማድረግ።

ወመተህ

- ወላጆች ስለኮሚቴው ሥራ እና ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶች መከላከል ላይ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን መምራት እና መምህራን ጥቃቶች እንዲቆሙ የሚሠሩትን ሥራ ማገዝ።

2. ጾታዊ ጥቃት ስደረሰባቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለይቶ መዘርዘር

ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ ሰጭ ኮሚቴ አባል ለመሆን ተጠቂዎችን ወደ ተገቢ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እንዴት መላክ እንዳለባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው:: እባክዎ ከዚህ ሞጁል ጀርባ ያለውን በጾታዊ ጥቃት ለተጋለጡ ግለሰቦች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መለያ መሣሪያ የሚለውን ይመልከቱ::

ይህ ቀላል የመለያ መሣሪያ ጾታዊ ጥቃት ላይ የሚሰሩ የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን (የህክምና ሆስፒታሎችንና ክሊኒኮችን፣ የምክር አገልግሎት መስጫዎችን፣ የህግ ድጋፍ ሰጭዎችን፣ የህግ አስከባሪዎችን ማለትም የህጻናት ጥበቃ ክፍል፣ የሴቶች እና/ወይም የህጻናት መጠለያዎች እና ማህበራትን ወይም ጾታዊ ጥቃት መከላከል ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያካትታል) ለመለየት ይጠቅማል::

አንዳንድ አገልግሎት ሰጭዎች በቅርብ ርቀት የማይገኙ ይሆናሉ፤ ይሁን እንጅ በአካባቢያችን የሚገኙ አገልግሎት ሰጭዎችን ለይቶ ማወቅ ጠቃሚ ነው፤ አገልግሎታቸውን የምንፈልግበት ወቅት ሊኖር ይችላል:: የመለያ መሣሪያው በተለያዩ የኮሚቴው አባላት አማካኝነት ሥራ ላይ መዋል አለበት:: ከተቻለ እያንዳንዱን አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለሁለት ምክንያቶች መጎብኘት ያስፈልጋል፡-

1. ለህጻናቱ ተገቢ አገልግሎት የሚሠጡ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ እና
2. አገልግሎት ሰጭዎች ጋር በመተዋወቅ ተገልጋይ ተማሪዎችን ለመላክ::

በመለያ መሣሪያው አማካኝነት የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ልየታ እንደተጠናቀቀ ለህዝብ ግልጽ የሆነ ቦታ ላይ ሁሉም ተማሪዎች እንዲያዩት መረጃው ይለጠፉል::

ተግባር 2 ማጠቃለያ፡- ተግባርና ኃላፊነቶች

ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ ሰጭ ኮሚቴ አባላት

አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን መጎብኘት እና በመለያ መሣሪያው አማካኝነት የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ልየታ ማጠናቀቀ::

ርዕሰ መምህራን

የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ልየታ እንደተጠናቀቀ ለህዝብ ግልጽ የሆነ ቦታ ላይ ሁሉም ተማሪዎች እንዲያዩት መረጃውን መለጠፍ::

ጠቃሚ መልዕክት፡- አንዳንድ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለሚሰጡት አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላሉ፤ ስለዚህ ለክፍያ የሚሆን ገቢ ማፈላለግ ጠቃሚ ነው:: ተጠቂዎች ለአገልግሎቱ መክፈል የለባቸውም::

ክለሳና ማጠቃለያ

ተጠቂዎች ርህራሄ በተሞላ መንገድ፣ ብቃት ያለው እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው:: ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ጥቃት በሚፈጸምባቸው ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም:: እንዲሁም ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ጥቃት በሚደርስባቸው ወቅት በመኖሪያ አካባቢያቸው የሚገኙ ጎልማሶች እገዛ አያደርጉላቸውም:: በዚህም ምክንያት ጉዳተኞቹ የደረሰባቸውን ጥቃት አያሳውቁም:: በመሆኑም ብዙ ጎልማሶች ስለጥቃቱ አስከፊነት እና የድግግሞሽ መጠን ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ መሆኑን ተማሪዎች ያረጋግጣሉ ወይም ይመሰክራሉ:: ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና ምላሽ ሰጭ ኮሚቴ ማቋቋም እና አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን መለየት ችግሩን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ወሳኝ ተግባር ነው::

ጥቃት ለደረሰባቸው ግለሰቦች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት መለያ መሣሪያ

ተ.ቁ	አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ሥም ዝርዝር	የሚሰጡትን አገልግሎት ዓይነት ይምረጡ፡- • ህክምና/ ሆስፒታል • ህክምና/ ክሊኒክ • የምክር አገልግሎት መስጫ • የህግ ድጋፍ ሰጭ(ፖሊስ፣ የህጻናት ጥበቃ) • የሴቶች እና/ወይም የህጻናት መጠለያዎች • ጾታዊ ጥቃት መከላከል ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች (ማህበራት፣ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑድርጅቶች)	ተጠቂዎችን ለማገዝ የሰለጠኑ መምህራንና ሠራተኞች (አለ/የለም)	ድርጅቱ መገኛ አድራሻ እና ከትምህርት ቤቱ ያለው ርቀት (ለትራንስፖርት ገንዘብ ያስፈልጋል?)	አድራሻ (የሚመለከተው አካል/አካላት ሥም እና ስልክ ቁጥር/ሮች)	የአገልግሎት ክፍያ አለ? ምን ያህል ነው?

ክፍል 3:- ሴት አመራሮችን ማበረታታት

በኢትዮጵያ የሴት አመራር ላይ ያሉ እውነታዎች

- *መረጃዎች እንደሚያሳዩት ወንዶች ለአመራርነት የበለጠ ይበረታታሉ፤ ለከባድ ኃላፊነቶች እና ለከፍተኛ የአመራርነት ቦታዎች ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች እድሎች ይመቻቻሉ::*
- *እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ* 2013 *በተደረገ የሠራተኞች ቆጠራ* 30% *የሚሆኑት ሴቶች ብቻ ናቸው ከፍተኛ ባለሙያዎች፤ ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶች ናቸው ከፍተኛ የአመራርነት ቦታ ላይ ያሉት::*
- *በትምህርት ቤቶች የሴት መምህራን እና ምሳሌ የሚሆኑ ሴቶች ቁጥር አነስተኛ ነው፤ ይህ ሴቶችን የማስተማር ክፍተት ሲሆን በተለይ ገጠራማ አካባቢዎች ላይ ችግሩ ይበዛል::*
- *በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ካሉ መምህራን ውስጥ በአማካይ* 63% *ወንዶች እና* 37% *ሴቶች ናቸው:: ከወንዶች ውስጥ* 68% *እና ከሴቶቹ ውስጥ* 73% *ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት አላቸው::*
- *ልጃገረዶች በአካባቢያቸው ውጤታማ የሆኑ ሴቶች ስለሌሉ ወይም በጣም ትንሽ ስለሆኑ ተምረን ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለን ብለው ለማሰብ ይቸገራሉ::*
- *ሴቶችና ልጃገረዶች ድጋፍና ምክር ይፈልጋሉ:: የሴት አመራሮች ቢኖሩም እንኳን በከፍተኛ ደረጃ የወንዶችን አመለካከት መቀየር፣ የቤት ውስጥ እኩል የሥራ ክፍፍልና ኃላፊነት እንዲኖር ተጨማሪ ሥራ መሥራትን ይጠይቃል::*

በትምህርት ቤታችሁ በትክክል ሴት አመራሮችን ማበረታታት እንዴት ይቻላል?

በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሥርዓተ ጾታ ክበቦች ቢኖሩ እንዲሁም በሁሉም ክፍሎች ወንድ እና ሴት አለቆች ቢኖሩ እንኳን በትምህርት ቤቱ የጾታ እኩልነት እና የሴቶች አመራርነት እየተበረታታ ነው ማለት አያስችልም:: ምክንያቱም አመራርነት በአመለካከት ለወንዶች የተተወ ተግባር በመሆኑ ነው:: ይህን አመለካከት ለመቀየር ድርጊቶች ታቅደው በጥንቃቄ ውጤትን መሠረት ባደረገ መንገድ መተግበር አለባቸው:: በመጀመሪያ ደረጃ እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት ውስጣዊ ዝግጁነት የግድ ይላል::

ትምህርት ቤቶች ሊተገብሯቸው የሚገቡ ትክክለኛ እና እውነተኛ ሴት አመራሮችን የማበረታቻ ሦስት ዋና ተግባሮች አሉ::



ቀጥሎ ያሉትን እያንዳንዱን ተግባሮች ለመፈጸም መከተል ያለብን ቅደም ተከተሎች፣ ተግባርና ኃላፊነቶች በዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

1. ምሳሌ የሆኑ ሴት አመራሮችን እና ሴት የትምህርት አመራሮችን ቁጥር በትምህርት ቤት ማሳደግ

የሴቶች የአመራርነት ሚና ያለውን ጠቀሜታ ከማስተዋወቅ እና መሪዎች እንዲሆኑ በማማከር የኃላፊነት ቦታዎችን እንዲይዙ ከማነሳሳት በላይ ሴት አመራሮችን ብቁና ምሳሌ ማድረግ ቀላል ነው።

ትምህርት ቤቶች ሴቶች በአስተዳደራዊ ቦታዎች እና በወተመህ ከፍተኛ የአመራርነት ሚና እንዲጫዎቱ ማድረግ አለባቸው። የአመራርነት ቦታዎች 50% በሴቶች እና 50% በወንዶች እንዲያዝ ግብ በማስቀመጥ ጾታዊ ምጥጥኑን መጠበቅ፤ ሴት መምህራን የአመራር ቦታዎችን በመያዝ ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ለምሳሌ የኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ከውጭ በሚሰሩ ልዩ ልዩ ሥራዎች ቃል አቀባይ፣ የክበብ መሪዎች።

> **ጠቃሚ መልዕክት:-**
>
> በትምህርት ቤቱ ያሉ ሴቶች ቁጥር አነስተኛ ከሆነ ለወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት የሴት መምህራን እና አመራሮች ቁጥሩ እንዲጨምር ይናገሩ።

ጎልማሶች ለሴት አመራሮች ክብርና ዋጋ ሲሰጡ የተመለከቱ ተማሪዎች ለልጃገረድ አመራሮች ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ። ከተማሪዎች መካከል ሴት አመራሮችን ምሳሌ ማድረግ ይከተላል። ለምሳሌ:- ሴት የክፍል አለቆች ለስሙ ያልሆነ እውነተኛ የአመራርነት ሚና እንዳላቸው እርግጠኛ መሆን፤ ወንድ የክፍል አለቆች የበላይ ለመሆን የሚሞክሩ ከሆነ መምህራን ይህን ችግር ማስተካከል አለባቸው።

ልጃገረዶች የሴቶች አመራር ላይ ያለውን የተሳሳተ ልማዳዊ አስተሳሰብ ወደ ጎን መተው ካልቻሉ ጠንካራ የአመራርነት ሚና ይጫዎታሉ ተብሎ አይጠበቅም።

የአመራርነት ችሎታን ለመገንባት የሚያስችሉ ክህሎቶች:-

ጥልቅ የሥራ ስሜት (Passion):- ለምትሰራው/ለምትሰሪው ሥራ ጥልቅ ስሜት ሲኖርህ/ሽ ሌሎች ይህን ጥልቅ ስሜት በመውሰድ እና ጠንክረው በመሥራት ግቦችን ያሳካሉ።

አካታችነት (Inclusivity):- ሁሉም ሠራተኞች በሥራ እንዲሳተፉ በማመቻቸት የየራሳቸውን ሙያዊ አስተዋጽኦ እንዲዎጡ ያበረታቷቸው።

ጥሩ አድማጭነት (Good Listening):- ሌሎች ምን እንደሚፈልጉ ለማወቅ እና አብሮ በተሻለ መንገድ ለመሥራት ጥሩ አድማጭ ይሁኑ።

አዎንታዊ አመለካከት (Positive attitude):- ከባድ ችግሮች ቢኖሩ እንኳንከሌሎች ጋር በመሆን መፍትሔ ይፈልጉ።

ለሌሎች እውቅና መስጠት (Reconnizing others):- አንድ ሰው ጥሩ ሥራ ሲሰራ ሌሎች በሙሉ እንዲያውቁ ያድርጉ። ሰዎች ለሥራው ዋጋ በሚሰጡበት ጊዜ ሌሎችም ጠንክረው ለመሥራት ይነሳሳሉ።

የተሻለ የትምህርት ቤት አካባቢ ለመፍጠር እነዚህ የአመራርነት ክህሎቶች ክፍል ውስጥ እና ውጭ፣ በክበቦች ውስጥ እና በወተመህ ሥራዎች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው። የሴቶች የአመራርነት ሚና ያለውን ጠቀሜታ በተከታታይ እና በንቃት ማስተዋወቅ አለብን።

ተግባር 1 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

ርዕሰ መምህራን እና ምክትል ርዕሰ መምህራን

- ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በተከታታይ የአመራርነት ሚናቸውን እየተወጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- አዎንታዊ የአመራር ክህሎትን በምሳሌነት መተግበር፣

ሴት አመራሮች

- አዎንታዊ የአመራር ክህሎትን በምሳሌነት መተግበር፣
- ሌሎች ሴቶች የአመራርነት ሚናን ተረክበው እንዲወጡ ማበረታታት እና ማማከር፣

የሥርዓተ ጾታ/የልጃገረዶች ክበብ

- ከሁሉም ተማሪዎች እና መምህራን ጋር በሴት አመራርነት እና የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ መመካከር እና ማበረታታት፣

2. ሴት አመራሮችን ማማከር

የአመራርነት ባለሙያዎች ሁሉም አመራሮች የጋራ የሚያደርጓቸው ችሎታዎች እንዳሏቸው ያምናሉ። ነገር ግን ከግለሰብ ግለሰብ የሚለያዩ ችሎታዎች አሉ። ሴቶች እና ልጃገረዶች የተሻሉ አመራሮች እንዲሆኑ መደገፍ እና ማማከር አለብን። ነገር ግን እነዚህ ሀሳቦች የወንዶችንም የአመራርነት ብቃት ለማሻሻል ያግዛሉ። በመጀመሪያ አመራርነት ምን ማለት እንደሆነ እናብራራ።

አመራርነት:- ለአንድ ሥራ የተሰባሰቡ ሰዎችን በማነሳሳት የሥራው ግብ እንዲሳካ የማድረግ ጥበብ ነው።

አመራርነት 'ትዕዛዞችን መስጠት'፣ 'የተለመዱ ነገሮችን መናገር'፣ 'ጥሩ ጥሩ ሀሳቦች ያሉት'ወይም "ሁሉንም ውሳኔዎች

መወሰን" ማለት አይደለም:: አመራርነት ሌሎች የቻሉትን ሁሉ እንዲሰሩ ማነሳሳት እና በሥራ አካባቢዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው::

ብዙ ጊዜ ሴቶች ተጽዕኖ ፈጣሪ እና ቁመኛ የወንድ አመራሮችን ባህርይ በመኮረጅ ያስመስላሉ:: ሰዎች ፈርተው እንዲሰሩ ማድረግ ጥሩ የአመራር ስልት አይደለም:: ከዚህ ቀጥሎ ልጃገረዶች መሪዎች እንዲሆኑ የምናበረታታባቸው ዝርዝር ስልቶች ቀርበዋል[1]:-

ልጃገረዶች በልበ ሙሉነት እንዲናገሩ ማማከር

ህጻናት ወንዶች ከልጃገረዶች የበለጠ እንደሚያወሩ እና ልጃገረዶች ደግሞ እንደሚያዳምጡ ተምረዋል:: ልጃገረዶች በራሳቸው የማይተማመኑ ከሆነ የራሳቸውን ሀሳብ አውጥተው ለመናገር አይነሳሱም:: ስህተቶችን በማረም ወይም ይቅርታ በመጠየቅ ልጃገረዶች ከወንዶች የበለጠ የተሻሉ ናቸው:: ተመሳሳይ ባህርይ ውስጥ የገባች ልጃገረድ ከተመለከቱ ያቀረበችውን ሀሳብ ለምን ዝቅ አድርጋ እንዳየችው በመጠየቅ ይህን ማድረግ እንደሌለባት ያስገንዝቧት::

ልጃገረዶች ችግሮችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ማስተማር

ወንዶች ችግሮችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው የሚያስችል ባህርይ ተላብሰዋል:: ልጃገረዶች ደግሞ መፍትሔዎች መስጠት ላይ ያተኩራሉ:: ልጃገረዶች ችግሮችን በራሳቸው መፍታት እንዲችሉ ያበረታቷቸው:: በራሳቸው የሚተማመኑ ልጃገረዶች ችግሮችን መፍታት ይችላሉ!

ልጃገረዶችን (እና ወንዶችን) ግጭት የማይቀር መሆኑን እና ከግጭት መደንበር እንደማያስፈልግ ማስተማር

ልጃገረዶች ጥሩ ያልሆኑ የግጭት ስሜቶችን በውስጣቸው በመያዝ ከሌሎች ጋር ሳይጋጩ አብረው መኖር እንዳለባቸው እየተመከሩ ነው ያደጉት፤ በመሆኑም እውነተኛ አስተያየት ከመስጠት ይቆጠባሉ:: ምክንያቱም እውነተኛ አስተያየት በመስጠት አለመግባባት እንዲፈጠር አይፈልጉም:: ልጃገረዶች የራሳቸውን ሀሳብ ሳይደብቁ እንዲያራምዱ ያበረታቷቸው:: ልጃገረዶች በጋራ በመሆን የተለያዩ ሚናዎችን ተከፋፍለው እንዲጫወቱ በማድረግ ምን ላይ እንደሰሩ እና ያልሰሩት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ:: ግጭት የማይቀር አብሮ የመኖር አንድ አካል እንደሆነ በመግለጽ የምንፈታበት መንገድ እንደሚወስነው ማስረዳት ይገባል::

ልጃገረዶች የራሳቸው ስኬት ባለቤት እንዲሆኑ ማበረታታት

ብዙ ጊዜ ልጃገረዶች በሌሎች ከሚገመተው በታች እንደሆኑ ተደርገው ይታሰባሉ:: እንዲሁም አንዳንድ ልጃገረዶች ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ይገምታሉ:: ይህ በራስ መተማመናቸውን ይሸረሽራል:: ሴቶች በስኬታቸው የማይበረታቱ ከሆነ ውጤታማነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ይሔዳል:: ልጃገረዶች ሲመከሩ "አመሰግናለሁ" ማለትን እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው:: ልጃገረዶች የራሳቸውን ስኬት በሚያዩበት ጊዜ እነሱ ይህን በመሥራታቸው ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸዋል::

ልጃገረዶች ችግሮችን እና ውድቀትን እንዳይፈሩ ማበረታታት

ልጃገረዶች በልበሙሉነት ችግሮችን ስለሚታገሉ ስህተቶችን ይፈራሉ፤ ችግሮችን ለመቀበል ብዙም አይደሉም:: አንዳንድ ልጃገረዶች የጥያቄውን ትክክለኛ መልስ 100% ማወቃቸውን እርግጠኛ ካልሆኑ ክፍል ውስጥ አይናገሩም:: ሌሎች ደግሞ አዲስ ትምህርት ወይም ተግባር ከሆነ ለመሞከር ይፈራሉ:: ልጃገረዶች በሚጠየቁበት ጊዜ "አልተዘጋጀሁም" ወይም "ይህን መሥራት አልችልም" ሲሉ ከሰሟቸው ሞክሮ መሳሳት ለመማር እና ለማደግ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ወዲያው ያሳስቧቸው::

1 Adapted from Lean In. Retrieved from *https://leanin.org/tips/role-model*

የሴት አመራርነትን ክብረ በዓል በማዘጋጀት ማክበር

ልጃገረዶች እና ወንዶች ስለአመራርነት የሚነገራቸው መልዕክት በጣም ይለያያል። ወንዶች መሪ እንዲሆኑ ስለምንጠብቅ አመራር ሆነው በሚሰሩበት ወቅት እናደንቃቸዋለን። በሌላ በኩል ግን ልጃገረዶች ምስጉን እና ከሁሉም ጋር ተግባቢ እንዲሆኑ እንጠብቃለን። አንድ ልጃገረድ የአመራርነት ክህሎት ለማዳበር በምታደርገው ጥረት የ"አዛዥነት" ወይም የ"ጠባጫሪ" ባህርይ ተላብሰሻል ተብላ ስትወቀስ ከሰሙ የአመራርነት ክህሎት የሚዳብረው በዚህ መንገድ መሆኑን በማስረዳት ክህሎቷን የበለጠ እንድታዳብር ያበረታቷት።

ተግባር 2 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

ሴት መምህራን፣ አመራሮች ወዘተ

- የራስዎትን ሀሳብ በመናገር እና በራስዎ የሥራ አካባቢ አመራር በመሆን ለልጃገረዶች ምሳሌ ይሁኑ።
- ተጽዕኖ ፈጣሪ ንግግሮችን በማድረግ እና የአመራር ክህሎቶች በመላበስ ለልጃገረዶች ምሳሌ ይሁኑ።
- ደፍረው ለሚናገሩ፣ ዕውቀታቸውን እና እምነታቸውን ለሚያጋሩ ልጃገረዶች ያስጨብጭቡላቸው።

ርዕሰ መምህራን እና ምክትል ርዕሰ መምህራን

- ልጃገረዶች የአመራርነትን ክህሎት እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው እንዲሁም ያመኑበትን ሀሳብ ደፍረው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።
- የሴቶችን በአመራርነት መሥራት እንዲያበረታቱ ወንዶችን ያበረታቱ።

የሥርዓተ ጾታ ክበብ

- ልጃገረዶች አመራር እንዲሆኑ ያማክሯቸው እንዲሁም የአመራርነት ክህሎት እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።
- የሴቶችን በአመራርነት መሥራት እንዲያበረታቱ ወንዶችን ያበረታቱ።

ጠቃሚ መልዕክት:-

አመራርነት ለወንዶች ብቻ የተሰጠ ብቃት አለመሆኑን ልብ ይበሉ። ሴት አመራሮችን "ልክ እንደ ወንዶች አመራር ሁነው" በማለት መሳሳት የለብንም። ሴቶችና ልጃገረዶች አመራርም እናትም መሆን ይችላሉ።

ክለሳና ማጠቃለያ

በተለምዶ ልጃገረዶች እና ሴቶች የአመራርነት ሚና እንዲወጡ አይፈቀድላቸውም። የወንዶች አመራር መሆን በማህበረሰቡ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ሲሆን የሴቶች አመራር መሆን ግን ተቀባይነቱ ዝቅተኛ ነው። አንዳንድ ጊዜ ልጃገረዶች እና ሴቶች በንቃት የአመራርነት ሚና እንዳይጫወቱ ይከለከላሉ ወይም የራሳቸውን አስተሳሰብ እንዲያራምዱ አይበረታቱም። የትምህርት ቤት አመራሮች እና መምህራን የአመራርነት ክህሎትን በመላበስ የሴቶችን የመምራት ብቃት ማሳየት፣ የሴቶች የአመራርነት ሚና ያለውን ጠቀሜታ ማስተዋወቅ እና ልጃገረዶችን መሪዎች እንዲሆኑ በማማከር የኃላፊነት ቦታዎችን እንዲይዙ ማነሳሳት አለባቸው።

ክፍል 4: ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ትንኮሳን፣ የህፃናትን ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለመከላከልና የሥርዓተ ፆታን እኩልነት ለማበረታታት የወተመህ እና የማህበረሰብ ድጋፍ

የሥርዓተ ፆታ ኢ-ፍትሀዊነት፣ ፆታ ተኮር ጥቃት እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህጻናትን በተለይም ሴቶችን ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዳይከታተሉና እንዲያቋርጡ ያደርጓቸዋል፡፡ ወተመህ በትምህርት ቤቱና በማህበረሰቡ መካከል ትስስር የሚፈጥር የአደረጃጀት አካላት ነው፡፡ የወተመህ አባላት ዘርፈ ብዙ የሆኑ ሥርዓተ ፆታ ተኮር ጥቃቶችን ለመከላከል የህብረተሰብ ድጋፍን ለማምጣት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ወተመህ በእነዚህ አስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር የተግባቦት ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡፡ ህብረተሰቡ በእነዚህ ርዕሠ ጉዳዮች ላይ ገለፃ ከተደረገለት የመከላከል ብሎም ችግሩ እንዲቆም የመፍትሄ አካል ይሆናል፡፡ በመከባበር ላይ የተመሠረተና ባህልን መሠረት ያደረገ የህብረተሰብ ተሳትፎና ውይይት ዘለቂታ ያለው የህብረተሰብ ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ህብረተሰቡ በዚህ ሂደት ላይ ሙሉ ተሳታፊ መሆን ራሱን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ እና ኃላፊነት ወስዶ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማህበራዊ እና የባህሪይ ለውጥ በማምጣት ሂደት ተሳትፎውን ማጎልበት ይኖርበታል፡፡

ውጤታማ የህብረተሰብ ተሳትፎ በመፍጠር ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ትንኮሳን፣ የህፃናትን ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛትን ህብረተሰቡ እንዲከላከል ወተመህ እንዴት ታግዙታላችሁ?

ወተመህና የሥርዓተ ፆታ/የሴቶች ክበባት በእነዚህ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ የህብረተሰብ ስብሰባዎች ለማካሄድና ወደ ተግባር ለመግባት የሚያስችሉ የሚከተሉት ሁለት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በታች በቀረቡት ተግባራት አስፈላጊ ደረጃዎችን፣ የሥራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶችን ለመዳሰስ እንሞክራን፡፡

1. ውጤታማ የህብረተሰብ ደጋፊ ክስተቶችን ለመፍጠር የተለያዩ ባህሉን መሠረት ያደረጉ ስልቶችን (ስትራቴጂዎችን) መጠቀም፣
2. የህፃናት ጋብቻና፣ የሴት ልጅ ግርዛትን፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ትንኮሳን እና ኢፍትሀዊ የሆነ ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ የተለያዩ የውይይት ጥያቄዎችን መጠቀም፣

1. ባህሉን መሠረት ያደረጉ ስልቶችን (ስትራቴጂዎችን) በመጠቀም ውጤታማ የህብረተሰብ ድጋፍ መፍጠር

ሰዎች መከባበር በተሞላበት ሁኔታ ሀሳባቸውን እንዲያንጸባርቁና በእነዚህ እምነቶች ላይ ምክንያቶችን እንዲሰጡ ከተደረጉ በጉዳዩ ላይ ድጋፍ የማግኘት ሥራው ውጤታማ ይሆናል፡፡ ሁሉም ሰዎች ለተመሳሳይ ምክንያት ተመሳሳይ እምነት ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

ሀ. በቅድሚያ የወተመህ አባላት የህብረሰቡን እምነቶች በአግባቡ ሊረዱ‌ይገባል፡፡ ከተለያዩ የጎሳ አባላት፣ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ካላቸውና በተለያየ የዕድሜ ክልል የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በአካታችነት ሀሳባቸውንና እምነታቸውን በነፃነት እንዲገልጹ በማድረግ ማወያየት ተመራጭና የተሻለ መንገድ ነው፡፡

ለ. በመቀጠል ለባህላዊ ልማዶች ትኩረት መስጠት ልብ ሊባል የሚገባ ሲሆን ባህላዊ ልማዶችን በእኩል ዓይን ማየት ተገቢ ነው፡፡ በውይይት ወቅት በዕድሜ ለገፉ ታላላቅ ሰዎች ብዙ ዕድል መስጠት ሊለመድ ይገባል፡፡ ሌሎች የማህበረሰብ አባላትን በማያገል ሁኔታ ለባህላዊ ልማዶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ክብር መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

ውይይቱ ለሚካሄድበት ቦታ፣ ጊዜ እና ለሚተላለፈው መልዕክት ትኩረት መስጠት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ሦስቱን ጉዳዮች እንደሚከተለው በተናጥል እንመለከታልን፡፡

ውይይቱ የሚካሄድበት ቦታ

የህብረተሰብ የተለያዩ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ የወተመህ አባላት የተለያዩ ቦታዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ለአብነት፡-

የማህበረሰብ ስብሰባዎች

አብያተ ክርስቲያን፣ መስጊዶች እና ሀይማኖታዊ ስብሰባዎች

የገበያ ቦታዎች

ትምህርት ቤቶች

የቤት ለቤት የአባ/የእማ ወራዎች ጉብኝት

የወረዳና ቀበሌ ስብስባዎች

ውይይቱ የሚካሄድበት ጊዜ

ለታዳሚዎች አመቺ የሆነ ጊዜ በቅድሚያ መወሰን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በትምህርት ጊዜ የማህበረሰቡን አባላት ለስብሰባ መጥራት አብዛኛዎቹ ጊዜውን በጣም ስለሚፈልጉት በተባለው ጊዜ ሊገኙ አይችሉም፡፡ የወተመህ አባላት የማህበረሰብ ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚረዱ የስብስባ ጊዜዎችን ለመወሰን (ለአብነት ቅዳሜና እሁድን) ከትምህርት ቤቱ ርዕሠ መምህራንና ከማህበረሰቡ መሪዎች ጋር በቅንጅት የተለያዩ ሥራዎችን ሊሰሩ ይገባል፡፡ እነዚህም፡-

1. የወላጆች ዕለታዊ ጉዳዮች
2. የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ማሳደጊያ ዘመቻዎች
3. የማህበረሰቡ አባላት የሚሳተፉበት ሌሎች ዘመቻዎች
4. መደበኛ ያልሆኑ የገጠር ስብሰባዎች
5. የቤተ ክርስቲያን/መስጊድ ሀይማኖታዊ ክስተቶች
6. የቀበሌ ሁነቶች
7. የተለያዩ በዓላት ለአብነት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን፣ ዓለም አቀፍ የማንበብና መፃፍ ቀን እና ዓለም አቀፍ የሴት ህፃናት ቀን

የሚተላለፈው መልዕክት

የማህበረሰብ አባላት የራሳቸውን ሀሳቦች መግለፃቸውና በውይይት/በክርክር መሳተፋቸው በጣም አስፈላጊ ነው:: ከባድ ርዕሠ ጉዳዮች በሚነሱበት ወቅት የማህበረሰብ አባላት ለሚያሳዩት የምልክትና የአካል አንቅስቃሴ ቋንቋዎች የወተመህ አባላት የላቀ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል::

በስብሰባዎች ወቅት ውጤታማ ተግባቦት እንዲኖር የተወሰኑ ምክሮች ቀጥሎ ቀርበዋል:

ገለፃ ከማድረግ/ከማብዛት ይልቅ ጥያቄዎችን መጠየቅ	በተለይም በገጠር ደረጃ መደበኛ ባልሆኑ ስብሰባዎች መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ከማህበረሰቡ መሪዎች/ታላላቅ ሰዎች ጋር በጋራ መስራት	ለባህላዊ አስተሳሰቦች ጠቃሚነት እውቅና መስጠት:: ነገር ግን የመወያያ ጥያቄዎችን በመጠቀም አንዳንድ የተሳሳቱ ልምዶችን ማረም
ከወንድና ከሴት የማህበረሰብ መሪዎች ጋር በመሆን ውይይቶችን መምራት	መልዕክቶችን ለማሰራጨት ከሀይማኖት መሪዎች ጋር መስራት	የተለያዩ ልምዶች/ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ማመዛዘን እንዲችሉ የማህበረሰብ አባላትን ጥቄዎችን መጠየቅ

ተግባር 1 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

የትምህርት ቤት ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

1. ትምህርት ቤትን መሠረት ባደረገ ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ትንኮሳን፣ የህፃናትን ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛትን እና ኢፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር በሚያስችሉ መድረኮች ሁልጊዜ ወተመህን መጋበዝ፤
2. የህፃናትን ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን በማስቀረት እና በፆታዊ እኩልነት ላይ መልካም ተሞክሮ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎችና ቤተሰቦች ተሞክሯቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ማድረግ፤
3. ትምህርት ቤትን መሠረት ባደረገ ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ትንኮሳን፣ የህፃናት ጋብቻን፣ የሴት ልጅ ግርዛትን እና ሌሎች ከጤና ጋር ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ከጤና ተቋማት ሠራኞች ጋር በቅንጅት መስራት፤
4. በእነዚህ ጉዳዮች የግንዛቤ ማዳበሪያ ተግባራትን ለመስራት የጎሳ፣ የሀይማኖት መሪዎችንና የሀገር ሽማግሌዎችን ማሳተፍ፣

የሥርዓተ ፆታ ክበባት

- የሴት ልጅ ግርዛት ባህላዊ ምንነትና አደጋ ላይ ተወያዩ:: የሴት ህፃናት ጤናና ትምህርት ሳይጎዳ አዎንታዊ የባህል እሴቶችን እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል ተወያዩ::

ተገቢ ምክሮች

የባህሪይ ለውጥ ቀስ በቀስ የሚያድግ (አዝጋሚ) ሂደት ነው። የማህበረሰብ አባላት በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ችግሮች ላይ እንዲወያዩ ዕድል መስጠት እና የራሳቸውን እምነት/ሀሳብ እንያወጡ/ እንዲያዘባርቁ ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው። ገለፃ ማድረግ ወይም ማብዛት ወይም ሰዎች በሰጡት ሀሳብ ላይ በመነሳት የራስን ውሳኔ መስጠት ሊገኝ የታሰበውን ውጤት ሊቀለብሰው ይችላል።

2. የህፃናት ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ትንኮሳንና ኢ-ፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ

የተለያዩ የውይይት ጥያቄዎችን መጠቀም

ከላይ የተገለፀውን የማህበረሰብ ድጋፍ መመሪያን ተጠቀሙ። እዚህ ላይ በህፃናትን ጋብቻ፣ በሴት ልጅ ግርዛት፣ በሥርዓተ ፆታ ተኮር ትንኮሳና ኢፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታ ላይ የማህበረሰቡን አባላት እንዴት ማሳተፍ እንደሚቻል ተጨማሪ ምክሮችን አካቷል።

የህፃናት ጋብቻ

የህፃናት ጋብቻ መሠረታዊ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሲሆን ሴት ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው የሚያስቀር ተግባር ነው። የህፃናት ጋብቻ ወደ ድህነት የሚመራና አስተማማኝ ኢኮኖሚ እንዳይረጋገጥ ያደርጋል። ከዚህም በተጨማሪ የህፃናት ጋብቻ በሴቶች ጤናና የውሳኔ አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

የህፃናት ጋብቻ ዋና ዋና ምክንያቶች



የህፃናት ጋብቻ በሴቶች ትምህርት ላይ የሚያስከትለው መዘዝ

1. ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው ያገቡ ሴቶች ከትምህርት ገበታ እንዲወጡና ተጨማሪ የትምህርት ዕድል እንዳያገኙ ይሆናሉ፡፡
2. ሴቶች በቤት ውስጥ ሥራዎችና ህፃናትን በማሳደግ ስለሚጠመዱ ወደ ትምህርት ቤት አይመለሱም፡፡
3. ሴቶች ካገቡ በኋላ ከባለቤቶቻቸው ጋር ከቦታ ወደ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በሌላ አዲስ ትምህርት ቤት ገብተው የመማር ዕድላቸው ጠባብ ይሆናል፡፡
4. የሴቶች ከትምህርት ቤት ውጪ መሆን ስለ መብቶቻቸውና ስለጤናና ሥነ ተዋልዶ የመማር ዕድላቸው በጣም ውስን ይሆናል፡፡
5. ሴቶች ባለመማራቸው የሥራ ቅጥር የማግኘት ዕድላቸው በጣም ውስን ነው፡፡
6. ውስን የትምህርት ዕድል ያገኙ ወይም ምንም የትምህርት ዕድል ያላገኙ ሴቶች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት የመላክ ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡
7. በህፃንነታቸው ያገቡ ሴቶች የሚወልዷቸው ልጆች ያለመማር ወይም ማሀይም የመሆን ዕድላቸው ሠፊ ነው፡፡

የማህበረሰብ የቅስቀሳ መድረክ በሚካሄድበት ወቅት ስለ ህፃናት ጋብቻ ገለፃ ከማድረግ/ከማብዛት ይልቅ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተመራጭ ነው፡፡ ቀጥሎ የተወሰኑ ለመወያያ የሚሆኑ ጥያቄዎች የቀረቡ ስለሆነ ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ፡፡

1. ሴት ተማሪዎች ከ18 ዓመት በፊት ወይም ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ጋብቻ ቢመሰርቱ በቤተሰባቸው ሊኖሩ የሚችሉ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምን ምን ናቸው?
2. ሴት ተማሪዎች ከ18 ዓመት በፊት ወይም ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ጋብቻ ቢመሰርቱ ለሴት ተማሪዎች ሊኖሩ የሚችሉ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምን ምን ናቸው?
3. ከምታውቋቸው ሴቶች ውስጥ የተማሩ ወይስ ያልተማሩ ሴቶች ልጆች ናቸው የተሻሉ ወይም ውጤታማ የሆኑት?
4. ከሥራ ማግኘት ባሻገር ትምህርት ዕድል የማግኘት ጥቅም ምንድን ነው? እነዚህ ጥቅሞች በዕለት ተዕለት ኑሮ ልንማራቸው እንችላለን?
5. ወንዶች ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸውን ሴቶች ማግባት ይፈልጋሉን? ለምን?
6. ሁሉም ወንዶችና ሴቶች ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ጋብቻ ቢመሰርቱ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን የምትመስል ይመስላችኋል?

የህፃናት ጋብቻን ለመከላከል እና ለህፃናት ጋብቻ ምላሽ ለመስጠት የሚረዱ ምክረ ሀሳቦች

የማህበረሰብ/የሀይማኖት መሪዎች የህፃናት ጋብቻን ህብረተሰቡ እንዲተው በህግ ላይ የተመሰረተ ክልከላ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

1. ከዕድሜ በታች በሚካሄድ የህፃናት ጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ላለመሳተፍ ህብረተሰቡ እምቢተኝነቱን ማሳየት አለበት፡፡
2. በሚስጢር ሊካሄዱ የታሰቡ የህፃናት ጋብቻዎችን የተማሪዎች የተለያዩ አደረጃጀቶች ለማህበረሰብ መሪዎች፣ ለፖሊስ፣ ለትምህርት ቤት ርዕሠ መምህራን ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በሚስጢር እንዲያጋልጡ በማድረግ አይንና ጆሮ በመሆን እንዲያገለግሉ ማደረግ፡፡

3. የታሰቡ የህፃናት ጋብቻዎችን በተመለከተ ከህብረተሰቡ ጥቆማ/ሪፖርት ለመቀበል የሚያስችል ዝግ የሀሳብ መስጫ ሳጥን ማዘጋጀት፡፡

የሴት ልጅ ግርዛት

የሴት ልጅ ግርዛት ያለምንም ህክምና የሴቶች ብልት/ሀፍረተ ሥጋ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው፡፡ ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ ሰብአዊ መብት ጥሰት እውቅና የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት የተቀናጀና ሥልታዊ ጥረቶችን ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍና በሰብዓዊ መብቶችና ኢ-ፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታ ላይ ማተኮር ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሴቶችና በልጃገረዶች የጤና ጠንቅ ከሚሆነው የወሲባዊና የማራቢያ አካላት ጤንነት ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ይጠበቃል፡፡

ለሴት ልጅ ግርዛት ዋና ዋና ምክንያቶች

የሴት ልጅ ግርዛት በሴቶች ትምህርት ላይ የሚያስከትለው መዘዝ

1. ግርዛት የተፈፀመባቸው ሴቶች ለረዥም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ ለመሆን ይገደዳሉ። ይህም የአጭር ወይም የረዥም ጊዜ ትምህርታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይፈጥርባቸዋል።
2. የሴት ልጅ ግርዛት በሚካሄድበት ወቅት በጤና ላይ ከፍተኛ አደጋ ስለሚያስከትል ሴቶች ከትምህርት ገበታቸው ለረዥም ጊዜ እንዲቀሩ ወይም በቋሚነት በትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል።
3. ሴቶች ለጋብቻ ከመሰጠታቸው በፊት ግርዛት የሚፈፀምባቸው ጊዜያቶች አሉ። አንድ ጊዜ ካገቡ በኋላ ተጨማሪ ትምህርት የማግኘታቸው ዕድል በጣም አነስተኛ ነው።

ለህፃናት ጋብቻ እንደተደረገው ሁሉ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት መጥፎነት ላይ ገለፃ ከማድረግ ወይም ገለፃ ከማብዛት ይልቅ ተያያዥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት በጣም ተመራጭ ነው። ቀጥሎ የተወሰኑ ለመወያያ የሚሆኑ ጥያቄዎች የቀረቡ ስለሆነ ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ። ጉዳዩ በጣም አሳሳቢ ስለሆነ ወንዶችንና ሴቶችን በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈል ማወያየት ይቻላል። ይሁን እንጂ በጉዳዩ ላይ የሌላውን ፆታ ሀሳብ ቢሰሙ የተሻለ ነው ተብሎ ከታሰበ በጋራ እንዲወያዩ ማድረግ ይቻላል።

የማህበረሰብ የቅስቀሳ መድረክ በሚካሄድበት ወቅት ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ሊጠየቁ የሚችሉ የመወያያ ጥያቄዎች:

1. በሴቶች ላይ ግርዛት ቢፈፀም በቤተሰባቸው ሊኖሩ የሚችሉ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምን ምን ናቸው?
2. በሴቶች ላይ ግርዛት ቢፈፀም በሴት ተማሪዎች ሊኖሩ የሚችሉ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምን ምን ናቸው?
3. የሴት ልጅ ግርዛት ሊያስክትሉት የሚችሉት አደጋዎችና በረዥም ጊዜ ሊያስከትሉ የሚችሉ ተጽእኖዎች ምን ምን ናቸው?
4. የሴት ልጅ ግርዛት ሳይፈፀም ቢቀር ሊኖሩ የሚችሉ አደጋዎች ምን ምን ናቸው?ባለመገረዛቸው ምክንያት የሚሰቃዩ ያልተገረዙ የምታውቋቸው ሰዎች አሉ?
5. የሴትን ልጅ ግርዛት ለማስቀረት የሚረዳና ሴትነትን በአግባቡ የሚገልጽ የባህል ገጽታ አለ ወይ?

ለሴት ልጅ ግርዛት ምላሽ ለመስጠት የሚረዱ ምክረ ሀሳቦች

1. የማህበረሰብ/የሀይማኖት መሪዎች የሴት ልጅ ግርዛት ህብረተሰቡ እንዲተው በህግ ላይ የተመሰረተ ክልከላ ሊያደርጉ ይገባል።
2. የሴት ልጅ የግርዛት ሥነ ሥርዓት ላይ ላለመሳተፍ ህብረተሰቡ እምቢተኝነቱን ማሳየት አለበት።
3. የተማሪዎች የተለያዩ አደረጃጀቶች የሴት ልጅ ግርዛትን ለማህበረሰብ መሪዎች፣ ለፖሊስ፣ ለትምህርት ቤት ርዕሠ መምህራን ሪፖርት እንዲያደርጉ አይንና ጆሮ በመሆን እንዲያገለግሉ ማድረግ።
4. የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ከህብረተሰቡ ጥቆማ/ሪፖርት ለመቀበል የሚያስችል ዝግ የሀሳብ መስጫ ሳጥን ማዘጋጀት።

ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት/ትንኮሳ

ብዙ ተማሪዎች በተለይም ልጃገረዶች ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት/ትንኮሳ እንደሚደርስባቸው ሪድ II ያካሄደው የጥናት ግኝት ያሳያል። ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት እንደ ደካማን ማጥቃት፣ ስድብ፣ ዛቻ/ማስፈራራት፣ ግላዊ ስብእናን መንካት እና ፆታዊ ጥቃት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። ከዚህ በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ህግ እና ከትምህርት ሚኒስቴር ፖሊሲ በሚፃረር ሁኔታ አንዳንድ

መምህራን አካላዊ ቅጣት (መማታት፣ ተማሪዎችን ማንበርከክ ወይም ምቾት በሌለው ሁኔታ ለረዥም ጊዜ ማቆየት ወይም አስገድዶ የጉልበት ሥራ ማሰራት) እንደሚያደርሱባቸው ብዙ ተማሪዎች ይናገራሉ። ጥቃት በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲኬድ ወይም ከትምህርት ቤት መልስ እና በቤት ውስጥ ይከሰታል።

ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ተማሪዎች ምቾት እንዳይሰማቸው፣ በትምህርት ውስጥ ውጤታማ እንዳይሆኑ ከማድረጉ በተጨማሪ ትምህርት እንዲያቋርጡ ያደርጋል። አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ወሲባዊ ጥቃት በሰዎች ላይ የዕድሜ ልክ ተጽእኖ ያሳድራሉ።

ህብረተሰቡ በችግሩ አሳሳቢነት ያለው ግንዛቤ ሊዳብር ይገባል። እንዲሁም ማህበረሰቡ ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ላይ ምላሽ በመስጠትና በመከላከል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል። ወተመሀ ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ላይ የመወያያ ጥያቄዎችን በማንሳት ውይይት ማካሄድ ይጠበቅበታል። በአካባቢው ችግሩ ያለበትን ደረጃ መረዳት ውይይቱ ውጤታማ እንዲሆን ይረዳል። በማህበረሰቡ ውስጥ ችግሩ ያለበትን ደረጃና ዓይነት መገምገም የተሻለ ሊሆን ይችላል። ተማሪዎች ለታላላቅ ሰዎች ማንኛውንም ዓይነት የትንኮሳ/የጥቃት ችግሮች ለማጋለጥ/ሚስጥር ለማውጣት ሊፈሩ ስለሚችሉ ቃለ መጠይቅ የሚያደርጉ አካላት ላይ ተማሪዎች እምነት የሚያሳድሩባቸው ሊሆኑ ይገባል።

ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ውይይት ማካሄድ በማህበረሰቡ ውስጥ የተከሰተውን ችግር ጭብጥ ለመረዳት እና ለለውጥ ቅስቀሳ ለማድረግ በጣም ወሳኝ ነው። ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ገለፃ ከማድረግ/ከማብዛት ይልቅ የመወያያ ጥያቄዎች በመጠየቅ ውይይት ማካሄድ ርዕሠ ጉዳዩን በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ/ሀሳብ ለማስተላለፍ የተሻለና ተመራጭ የተግባቦት መንገድ ነው።

ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ላይ ሊጠየቁ የሚችሉ የመወያያ ጥያቄዎች

1. በትምህርት ቤት ውስጥ ምን ዓይነት የተለመደ ችግር አለ?ከትምህርት ቤት ውጪስ? በቤት ውስጥስ?
2. ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥነት ያለው ፆታዊና የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ምን ዓይነት አደጋ እና የረዥም ጊዜ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል?
3. ታላላቆች ለምን ህፃናትን ይመታሉ?ይደበድባሉ?
4. አካላዊ ቅጣት ሳይኖር ህፃናትን ለማስተማር የሚረዳ ሌላ ዘዴ ሊኖር ይችላልን?
5. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ከትምህርት ቤት ውጪና በቤት ውስጥ በሚደረሱ በሥርዓተ ፆታ ላይ ያተኮሩ ጥቃቶች በተመለከተ ምላሽ ለመስጠት ማህበረሰቡ ምን ማድረግ አለበት?

ኢ-ፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታ

ብዙውን ጊዜ ወላጆችና መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች የተለያየ ግምት አላቸው። ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ወንድ ተማሪዎች

- ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ይበረታታሉ፣
- ከቤት ውጪ የተሻለ ማህበራዊ ግንኙነት አላቸው፣
- አዳዲስ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ጊዜ ያገኛሉ፣

ከዚህ በተቃራኒ ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳይከታተሉ እና ሌሎች ተግባራትን እንዳያከናውኑ የሚያግዷቸው የቤት ውስጥ ሥራ የመስራት ኃላፊነቶች አሉባቸው። ሴት ተማሪዎች ያላቸው ነፃነት አነስተኛ እና ከቤት ውጪ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ውስን ከሆነ በራሳቸው የመተማመን ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ ይሆናል። ወተመህ ኢፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታን ማስቀረት የሚያስችል የውይይት መድረክ በመፍጠር የሚከተሉትን የመወያያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይችላሉ።

የማህበረሰብ የቅስቀሳ መድረክ በሚካሄድበት ወቅት ኢፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ ሊጠየቁ የሚችሉ የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ሴት ልጃችሁ ምን እንድትሆን ትፈልጋላችሁ? ወንድ ልጃችሁስ?
2. እንዲሆኑ የምትፈልጉት የተለያየ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? እንዲሆኑ የምትፈልጉት ተመሳሳይ ከሆነ ህልማቸውን ለማሳካት ምን ዓይነት ድጋፍ ታደርጉላቸዋላችሁ?
3. ኢፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታን ለማስቀረት ምን የተሻለ ስራ ልትሰሩ ትችላላችሁ?
4. ወንዶች እህቶቻቸውን በተዘውታሪ የቤት ውስጥ ሥራ በመስራት ያግዟቸዋል? የማያግዟቸው ከሆነ ለምን አያግዟቸውም?
5. በወንዶችና በሴቶች እኩልነት እንዲኖር ሁለቱም ኑሯቸው የተሳካ እንዲሆን ምን ታደርጋላችሁ?

ተገቢ ምክሮች

በተለያዩ ባህሎች ስለ ወንድ ልጆች በአጠቃላይ ስለወንዶች ተዘውታሪ የቤት ውስጥ ስራዎች በማንሳት መነጋገር በጣም አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ ሰዎች "ወንዶች ተዘውታሪ የቤት ውስጥ ስራዎች መሳተፍ አለባቸው" የሚለውን ሲሰሙ እንግዳ ጉዳይ ሊሆንባቸው ይችላል። ይሁን እንጂ እየለመዱት ሲሄዱ አስፈላጊና ጠቃሚ ጉዳይ መሆኑን መረዳት ይችላሉ።

ተግባር 2 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

ወተመህ

1. በሴት ልጆች ግርዛት፣ ከትምህርት ቤት ጋር ተያያዥ ያላቸው ሥርዓተ ፆታ ተኮር ጥቃቶችና ኢፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታ ላይ በትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ውይይት ስብሰባዎች መጠቀም፣
2. ሥርዓተ ፆታ ተኮር ጥቃቶችንና ጎጅ ባህላዊ ልምዶች (Harmful Traditional Practices) ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ከማህበረሰቡ አባላት ጋር መዘርጋትና ማካናወን፣
3. የተለያዩ የህብረተሰብ አደረጃጀቶችንናአጋርነት (ለአብነት የሥርዓተ ፆታ ክበባት፣ መምህራን፣ ተሰሚነት ያላቸው ታላላቅ ሰዎች፣ የአካባቢው መንግስታዊ ባለሥልጣናት፣ የሴቶችና የወጣቶች ማህበራት፣ የማህበረሰብና የሀይማኖት መሪዎች፣ ወዘተ) ማጠናከርና መመስረት። የህፃናትን ልምድንና የስኬት ዕድሎች ለማሻሻል ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል።

ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

1. ከወተመህ፣ ከሥርዓተ ፆታ ክበባት እና ከማህበረሰብና ከሀይማኖት መሪዎች ጋር በእነዚህ ርዕሠ ጉዳዮች ላይ ግልጽ ውይይት ለማካሄድ በቅርበትና በትብብር መስራት፣
2. ልጃገረዶች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት። ቤተሰቦቻቸው የትምህርት መሳሪያ ሊያሟሉላቸው የማይችሉ ሴት ተማሪዎች የትምህርት መሳሪዎች መስጠትና መምህራን ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

የልጃገረዶች/የሥርዓተ - ፆታ ክበባት አስተባባሪዎች

1. ልጃገረዶች የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጆች ግርዛትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ውይይት እንዲደርጉና ተግባሩ እንዳይፈፀም እንዲከላከሉ ኃላፊነት/ሥልጣን መስጠት፣
2. ልጃገረዶች የሴት ልጆች ግርዛትን በተመለከተ ጥቆማ/ሪፖርት እንያደርጉ ኃላፊነት/ሥልጣን መስጠት፣
3. የህፃናትን ልምድንና የስኬት ዕድሎች ለማሻሻል ከወተመህ ጋር በቅንጅት መስራት፣

ተገቢ ምክሮች

ለጋራ ዓላማና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለውይይት በስብሰባ ላይ የመገኘት ልምድ እንዲያድግ ሁሉም ያገባኛል የሚሉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መስራት ይኖርባቸዋል።

ክለሳና ማጠቃለያ

አዎንታዊ ማህበረሰብ ለውጥ ለማምጣት ማህበረሰቡ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በማህበረሰቡ አባላት መካከል መደማመጥ፣ መከባባር፣ ሀሳብንና ልምድን በአግባቡ መለዋወጥ የሚኖር ከሆነ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ደጋፊ እንዲሆኑ ለማድረግና የለውጥ መልዕክቶችን በቀላሉ ማስተላለፍ ይቻላል። የውይይት ርዕሠ ጉዳዩ ምንም ይሁን ምን (የህፃናት ጋብቻ ይሁን የሴቶች ግርዛት፣ ከትምህርት ቤት ተያያዥነት ያላቸው የሥርዓተ ፆታ ጥቃቶች ወይም ኢ-ፍትሀዊ ሥርዓተ ፆታ) ማህበረሰቡ አጋር እንጂ እንቅፋት ሊሆን አይችልም። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የለውጥ አራማጆች የማህበረሰቡን አባላትን ለማዳመጥ ጊዜ መስጠትና በእርጋታ እምነታቸውን ማረም ይጠበቅባቸዋል።

ክፍል 5: የወር አበባ ንጽህና እና መሠረታዊ የመራቢያ አካላት ጤና አጠባበቅ

በኢትዮጵያ በርካታ ልጃገረዶች በወር አበባ ምክንያት በየወሩ ለተወሰኑ ቀናት ከትምህርት ቤት ይቀራሉ፡፡ ብዙ ትምህርት ቤቶች የግል ንጽህና መጠበቂያ እና ንጹህ የመፀዳጃ ቤት የላቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ልጃገረዶች የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ ወይም ሞዴስ የላቸውም፡፡

በትምህርት ቤታችን ልጃገረዶች በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዳይቀሩ እንዴት መከላከል እንችላለን?

ልጃገረዶች በወር አበባ ወቅት በትምህርት ቤት ውስጥ ምቾት እንዲሰማቸው ለማድረግ ትምህርት ቤቶች ሊያካናውኗቸው የሚገቡ አምስት ተግባራት አሉ፡፡ ልጃገረዶች በወር አበባ ወቅት ምቾት ከተሰማቸው ከትምህርት ቤት የመቅረት ዕድላቸው በጣም አነስተኛ ይሆናል፡፡

1. ርዕሠ መምህራን እንደ "ተጠሪ ሴቶች (Focal Women)" ሊገለግሉ የሚችሉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መምህራንን እና የሥርዓተ ፆታ አስተባባሪዎችን መመደብ አለባቸው፡፡
2. ርዕሠ መምህራን የወር አበባ ክፍል ወይም ለልጃገረዶች ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ራሱን የቻለ መፀዳጃ ቤት መኖሩን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. "ተጠሪ ሴቶች (Focal Women)" በወር አበባ ንጽህና እና መሠረታዊ የመራቢያ አካላት ጤና አጠባበቅ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍሎች ለሚማሩለሁሉም ልጃገረዶች የውይይት ጊዜያትን ማደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በነዚህ የውይይት መድረኮች ወንድ ተማሪዎች ቢሳተፉ በብዙ ነገሮች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ልጃገረዶች ጥሩ ስሜት ወይም ምቾት ላይሰማቸው ስለሚችል ለየብቻቸው የውይይት ጊዜ ማደራጀት ተመራጭ ነው፡፡
4. ርዕሠ መምህራንና "ተጠሪ ሴቶች (Focal Women)" ተጠቅሞ የሚጣል ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ በትምህርት ቤቱ ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. የወር አበባን በተመለከተ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ መፍጠር

ተገቢ ምክሮች

ተጠሪ ሴቶች ተግባርና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ ትምህርት ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

ለእያዳንዱ ተገባራት ደረጃዎች፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ቀጥሎ ቀርበዋል።

ለወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ "ተጠሪ ሴቶችን" መመደብ

ርዕሠ መምህራን ከሴት መምህራን መካከል በጎ ፈቃደኛ የሆኑትን በመመደብ ንጽህና አጠባባቅ ላይ ክትትል እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡ እነዚህ ተጠሪ ሴት መምህራን ልጃገረዶችን እንዲረዱ ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሴት ተማሪዎች በእነዚህ ሴት መምህራን ላይ እምነት ሊጥሉባቸውና ሊወዷቸው ይገባል፡፡ የተጠሪ ሴት መምህራን ብዛት በአጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት ይወሰናል፡፡

ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍሎች ለሚማሩ 50 ሴት ተማሪዎች አንድ ተጠሪ ሴት መምህር ይመደባል፡፡ ሴት ተማሪዎች በፈለጉበት ጊዜ ሊያገኟቸው እንዲችሉ እና ሊኖር የሚችለውን የስራ ጫና ለመቀነስ በርካታ ተጠሪ ሴቶች በትምህርት ቤቱ ሊኖሩ ይገባል፡፡ አንድ ጊዜ ተጠሪ ሴቶች ከተለዩ በኂላ እነሱን በተመለከተ ለሴት ተማሪዎች መረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የተመደቡት ተጠሪ ሴቶችን በየክፍሉ በማዞር ለሁሉም ተማሪዎች ማስተዋወቅ

ተገቢ ነው። የተመደቡት ተጠሪ ሴቶች ስም ዝርዝር በማስተወቂያ ሠሌዳ ላይ በመለጠፍ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መረጃው እንዲደርሳቸው ማድረግ ተገቢ ነው።

ተግባር 1 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

1. ተጠሪ ሴቶች (Focal Women)
   1. ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በየሩብ ዓመቱ የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ውይይት ማካሄድ፣
   2. ለአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት የሚውል የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ በትምህርት ቤቱ ውስጥ መኖራቸው፣ ንጽህናቸው የተጠበቀ እና በአግባቡ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤
   3. ልጃገረዶች የምክር አገልግሎትና የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ ሲፈልጉ በቀላሉ ሊያገኟቸው ይገባል፣

ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

1. የተጠሪ ሴቶች ሚናና ኃላፊነት መስጠት
2. ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍሎች የሚማሩ ሁሉም ሴት ተማሪዎች ትክተታዊ ሴቶችን በተመለከተ በማስታወቂያና በተለያዩ መንገዶች ግንዛቤ የተፈጠረላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

መምህራን

1. በየሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ትክተታዊ ሴቶችን ማስተዋወቅ፣
2. በመማሪያ ክፍሎች የትክተታዊ ሴቶችን ስም ዝርዝር መለጠፍ፣

2. ለልጃገረዶች ብቻ የሚሆን ደህነነቱ የተጠበቀ ክፍል ወይም የመፀዳጃ ቤት መኖሩን ማረጋገጥ

ልጃገረዶች ብቻ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ የንጽህና መጠበቂያ ክፍሎችንና ለልጃገረዶች ብቻ የተለየ መፀዳጃ ቤት መኖሩን ማረጋገጥ የወር አበባን ንጽህና ለመጠበቅ የሚረዱ ሁለት መንገዶች ናቸው።

ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍል

ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍል ራሱን ችሎ የተዘጋጀ ክፍል ሲሆን ልጃገረዶች በወር አበባ ወቅት የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ የሚያገኙበት፣ የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ የሚቀየሩበትና ሲደክማቸው ወይም ህመም ሲሰማቸው የሚያርፉበት ነው። የትምህርት ቤቱ ተጠሪ ሴቶችክፍሉ ውስጥ በወር አበባ መጠበቂያ ያለው፣ ንጹህ እና ለውጪ ከሚመጡ ጥቃቶች የተጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ደህንነታቸው የተጠበቁ ክፍሎች የሚከተሉት ሊያሟሉ ይገባል።

ለብቸኝነት አመቺ የሆነ: ሊቆለፍ የሚችል ሆኖ ከሴቶች ውጪ ማንም ሰው ወደ ውስጥ ማየትም ሆነ መግባት የማማያስችል ክፍል	ከተጠቀሙበት በኋላ የሚጣል ወይም እንደገና ሊጠቀሙበት የሚችል ወይም ሁለቱንም ዓይነት የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ	የመፀዳጃ ቤት ቁሳቁሶችና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት

የእጅ መታጠቢያ ገንዳ ከንጹህ ውሀና ከሳሙና ጋር	ለመቀመጥ ወይም ለመጋደም የሚያችል ቦታ (ወንበር፣ አግዳሚ ወንበር ወይም ፍራሽ)	ለመቀየሪያ የሚሆኑ ልብሶች

ለልጃገረዶች ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ መፀዳጃ ቤት

ደህንነታቸው የተጠበቀ ክፍሎች የማይኖሩ ከሆነ ቢያንስ ለልጃገረዶች እና ለወንዶች ለየብቻ አገልግሎት የሚሰጡ መፀዳጃ ቤቶች የግድ ሊኖሩ ይገባል:: የመፀዳጃ ቤቶችም ለግል አገልግሎት አመቺ የሆነና ሊቆለፍ የሚችሉ ሆነው ማንም ሰው ወደ ውስጥ ሊያይበት ወይም ወደ ውስጥ ሊገባበት የማይችል መሆን አለባቸው:: የመፀዳጃ ቤቶችም፣

1. የመፀዳጃ ቤት ቁሳቁሶች፣
2. የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት
3. የእጅ መታጠቢያ ገንዳ ከንጹህ ውሀና ከሳሙና ጋር
4. ሴት ተማሪዎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መጠቀም እንዲችሉ ተጠሪ ሴቶችእንደ ዋና ተግባራቸው በመውሰድ የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ እና መቀየሪያ ልብሶችን ማዘጋጀት አለባቸው::

ተግባር 2 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

ትክተታዊ ሴቶች

1. ከርዕሰ መምህራን ጋር በመሆን ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍል ወይም ለሁሉም ልጃገረዶች ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ መፀዳጃ ቤት ማደራጀት፣
2. የወር አበባ መጠበቂያ ፓድ፣ ለመቀያየሪያ የሚሆን ልብሶች፣ ሳሙናና ውሀ የመሳሰሉትን ያካተተ የመፀዳጃ ቤት እና የንጽህና ቁሳቁሶች ያሟላሉ፣

ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

1. ከተጠሪ ሴቶችጋር በመሆን ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍል ወይም ለሁሉም ልጃገረዶች ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ መፀዳጃ ቤት ማደራጀት፣
2. ተጠሪ ሴቶች አስፈላጊ የንጽህና ቁሳቁሶችን ማሟላት እንዲችሉ የበጀት ድጋፍ ማድረግ፣
3. በየዕለቱ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ንጽህና መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፣
4. በአጠቃላይ ስብሰባ ወቅት ስለ ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ለወላጆችና ለወተመሀ መረጃ መስጠት፣

3. የወርአበባ ንጽህና አጠባበቅና መሠረታዊ የመራቢያ አካላት ጤና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት

ተጠሪ ሴቶች ሁሉም ልጃገረዶች እስከሚሳተፉ ድረስ በወር አንድ ጊዜ የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅና መሠረታዊ የመራቢያ አካላት ጤና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል:: የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኩ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ቢካሄድ ብዙ ልጃገረዶች እንዲሳተፉ ይረዳል:: ለአንድ ሠዓት

ያህል ሊካሄዱ የሚችሉ አራት ክፍለ ጊዜያትና የእያንዳንዱ ክፍለ ጊዚያት ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ተገቢ ምክሮች

- በመፀዳጃ ቤቶች አካባቢ በልጃገረዶች ላይ ያታዊ ጥቃት መድረስ የተለመደ ነው:: የወር አበባ መጠበቂያ ክፍሎችና የመፀዳጃ ቤቶች ደህንነታቸው አስተማማኝ ካልሆኑ ልጃገረዶች ሊጠቀሙባቸው አይችሉም:: መምህራን በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የተጠቃሚ ተማሪዎች ደህንነት መጠበቁን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::
- አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለማሟላት ከወተመህ አባላት ጋር መመካከር ይገባል:: የወተመህ አባላት በጀት በመስጠት በኩል እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ::
- የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያዎችን ለማቅረብ በጀት መመደብና አቅርቦቱ ሳይቆራረጥ መቅረብ አለበት::

ክፍለ ጊዜ 1: የወር አበባ ምንነትና ስለ ወር አበባ አባባሎች

ስለ የወር አበባ አጠቃላይ እውነታዎች

1. ልጃገረዷ/ሴቷ ካላረገዘች በስተቀር በወር አንድ ጊዜ የደምና የቲሹ ማጥላት ወይም መፍሰስ ነው::
2. የወር አበባ ማየት ተፈጥሯዊ ሂደት ሲሆን ያለምንም መከላከያ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተፈፀመ በኂላ የወር አበባ ካልመጣ የእርግዝና ምልክትም ይሆናል::
3. የወር አበባ የሁሉም ሴቶች የጋራ ተፈጥሯዊ ክስተት ነው::
4. ትክክለኛ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የወር አበባን በቀላሉ መያዝ/መቆጣጠር ይችላል::
5. የወር አበባ ብዙውን ጊዜ ዘወትር ከ21-35 ቀናት ይከሰታል::

ብዙ ባህሎች ከወር አበባ ጋር በተያያዘ የተለያየ እምነት፣ የተለመደ አባባልና እርም/አይነኬ ጉዳዮች አሏቸው። በኢትዮጵያ የወር አበባን በተመለከተ ማህበራዊ ልማዶች ወይም ያልተፃፉ ህጎች እና ተግባራት አሉ። እስኪ ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ ይመልከቱ።

ተግባር: የተለመዱ አባባሎች እና እውነታዎች

ልጃገረዶችን ስለ ወር አበባ የሰሙትን እንዲናገሩ በማድረግ መጀመርና ከእያንዳንዱ ልጃገረድ ጋር መወያየት:: ልጃገረዶች ሀሳባቸውን ያለምንም መሸማቀቅ በግልጽ እንዲያቀርቡ ማበረታታት:: በወር አበባ ላይ የተለመዱ አበባሎችና እውነታዎች ከዚህ በታች እንደ ሚከተለው ቀርበዋል:: እያንዳንዱ የተለመደ አባባል ከተነበበላቸው በኂላ እውነት ወይም ሀሰት መሆኑን እንዲናገሩ ጥያቄችን መጠየቅ:: ምላሻቸው ሀሰት ከሆነ እውነቱ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ በተጨማሪ መጠየቅ::

አፈ-ታሪኮች ወይም እምነቶች	እውነታዎች
የወር አበባ እያየች ያለች ሴት ነፍሠ ጡር (እርጉዝ) ልትሆን አትችልም	**ሀሰት**:- የወር አበባ በማየት ላይ ያለች ነፍሠ ጡር ሴት ልትሆን ትችላለች
በወር አበባ ወቅት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ተገቢ አይደለም	**ሀሰት**:- ልጃገረዶች በወር አበባ ወቅት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ የለባቸውም ለማለት በቂ ምክንያት ሊኖር አይቻልም። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ የወር አበባ ወቅት የሚኖር የሰውነት መሸማቀቅን ይቀንሳል።
የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ ወይም ሞዴስ ወይም የወር አበባ መቀበያ/መምጠጫ ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ/ፓድ ብትጠቀሙ ክብረ ንጽህና አይኖራችሁም።	**ሀሰት**:- የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ ወይም ሞዴስ ወይም ደም እንደ ስፖንጅ መያዝ የሚችል ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ መጠቀም ከክብረ ንጽህና ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ክብረ ንጽህና ከወሲባዊ ግንኙነት ተግባር ጋር የተያያዘ ሲሆን ፓድ መጠቀም ግን በወር አበባ ወቅት የግል ንጽህናን ከመጠበቅ ጋር የተያያዘ ተግባር ነው።
የወር አበባ ማየት ጀመረች ማለት ልጃገረዷ የግብረ ስጋ ግንኙነት ጀምራለች ማለት ነው።	**ሀሰት**:- የወር አበባ በልጃገረዶች የኮረዳነትን ወቅት ከሚያሳዩ ምልክቶች አንዱ ነው።
በወር አበባ ወቅት ልጃገረዶች/ሴቶች ሻይ መጠጣት የለባቸውም	**ሀሰት**:- ትኩስ መጠጦችን መጠጣት በወር አበባ ወቅት የሚኖር የሆድ ቁርጠትን ይቀንሳል። ነገር ግን በብዛት ሻይና ቡና መጠጣት የወር አበባ ሲፈስ ህመም እንዲኖር ያደረጋል። ከዚህ ውጪ ሻይ መጠጣት ምንም ጉዳት አያስከትልም።
የወር አበባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በተለይም ለወንዶች ሚስጢር መሆን አለባቸው	**ሀሰት**:- ሁሉም ልጃገረዶችና ሴቶች ሊጋጥማቸው የሚችል የተፈጥሮ ክስተት ስለሆነ ለማንኛውም ሰው ሚስጢር መሆን የለበትም
እንደገና ታጥበው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ጨርቆች ወይም ፓዶች ደረቅና በድብቅ ቦታ የሚቀመጡ መሆን አለባቸው	**ሀሰት**:- እንደገና ታጥበው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ጨርቆች ወይም ፓዶች በሳሙና ታጥበው በፀሀይ ብርሀን መድረቅ አለባቸው። ይህን ማድረግ የጎንዮሽ ችግር (ኢንፌክሽን) እና የመቆጥቆጥ ስሜት የሚፈጥሩ ባክቴሪያዎችን ለመግደል ይረዳል።

የወር አበባ የተፈጥሮ ሂደት እንጂ የሚያሳፍር ነገር አይደለም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ክፍለ ጊዜ 2: የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅና አወጋገድ

የወር አበባን በተመለከተ ልጃገረዶች የማፈር ስሜት ይሰማቸዋል። ምክንያቱም አዋቂዎች ወይም ትልቅ ሰዎች በአጠቃላይ ቤተሰቦች በወር አበባ ወቅት ምን እንደሚያጋጥማቸውና ምን ማድረግ እንዳለባቸው የመወያያ ጊዜ ሰጥተው ስለማያወያዩአቸው ነው። አዋቂዎች በነዚህ ጉዳዮች መወያየት አሳፋሪ ጉዳይ አድርጎ የማየት ስሜት ይሰማቸዋል። ይሁን እንጂ ተጠሪ ሴቶች ስለ ወር አበባ ግልጽ፣ ሀቀኛ መሆን፣ የወር አበባ ተፈጥሯዊና ምንም የሚያሳፍር ጉዳይ አለመሆኑን ልጃገረዶችን ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል።

የተለያዩ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ መንገዶች አሉ። ይሁን እንጂ ቁርጥራጭ ወይም የተቀደዱ ጨርቆችን ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፓዶችን መጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የተለመደ ነው። ቀጥሎ ልጃገረዶች ማወቅ ያለባቸው ጉዳዮች ቀርበዋል።

ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች	ማወቅ ያለባችሁ
ጨርቅ፣ አሮጌ ጨርቅ፣ ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ እንደገና አገልግሎት የሚሰጡ ፓዶች	ጨርቆች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ ንጹህ እንዲሆኑ በአግባቡ በሣሙና ከታጠቡ በኋላ በፀሀይ እንዲደርቁ መደረግ አለበት። ጨርቆቹ ንጹህ ካልሆኑ የጎንዮሽ የጤና ጠንቅ (ኢንፌክሽን) ሊፈጥሩ ይችላሉ። ልጃገረዶች በትምህርት ቤት ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ መቀያየር እንዲችሉ ተጨማሪ ጨርቆች ወይም ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ እንደገና አገልግሎት የሚሰጡ ፓዶች መያዝ አለባቸው። በትምህርት ቤት ውስጥ ጨርቆችን ማጠብ የማይቻል ከሆነ የተጠቀሙበትን ጨርቅ በፕላስቲክ (በፌስታል) በማጠራቀም ወደ ቤት ወስደው ማጠብ ይኖርባቸዋል።
የሚወገድ የንጽህና መጠበቂያ ፓዶች	አመቺ ቢሆንም አካባቢን ለመጠበቅ ጥሩ አይደለም። ውድ ስለሆነ ብዙዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በየወሩ የመግዛት አቅም አይኖራቸውም። በመሆኑም ለረዥም ጊዜ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። በመፀዳጃ ቤት ከውሀ ጋር ሊለቀቅና ሊቃጥል አይችልም ፓዶች ሲሰሩ ጥቅም ላይ የዋሉት ኬሚካሎች ለገላ/ሰውነት መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ
የወር አበባ መቀበያ/ መምጠጫ ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ/ፓድ	አንዳንድ ባህሎች የወር አበባ መቀበያ/መምጠጫ ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ/ፓድ የሚጠቀሙ ልጃገረዶች ክብረ ንጽህና የላቸውም የሚል የተሳሳተ እምነት አለ። አመቺ ቢሆንም አካባቢን ለመጠበቅ ጥሩ አይደለም። ውድ ስለሆነ ብዙዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በየወሩ የመግዛት አቅም አይኖራቸውም። በመሆኑም ለረዥም ጊዜ ምፍትሄ ሊሆን አይችልም። በመፀዳጃ ቤት ከውሀ ጋር ሊለቀቅና ሊቃጠል አይችልም ፓዶች ሲሰሩ ጥቅም ላይ የዋሉት ኬሚካሎች ለገላ/ሰውነት መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ

ልጃገረዶች ሊያውቁት የሚገባ ነገር ቢኖር በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት መቅረት እንደሌለባቸውና ተጠሪ ሴቶች በትምህርት ቤት ውስጥ ሊረዷቸው የሚችሉ መሆናቸውን ነው። ተግባር 4 ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ እንደገና ጥቅም ላይ ፓድ አሠራርን ወይም አዘገጃጀትን ይመለከታል።

ክፍለ ጊዜ 3:- የወር አበባ ዑደት

ብዙ ጊዜ ሴቶች የወር አበባቸው መቼ እንደሚመጣ አያውቁም። በአጋጣሚ የወር አበባቸው በትምህርት ሠዓት ቢመጣባቸው በቂ ዝግጅት ላይኖራቸው ስለሚችል ከትምህርታቸው ሊሰናከሉ ይችላሉ። ቀጥሎ የቀረቡትን የወር አበባን የሚመለከቱ መሠረታዊ መረጃዎች መረዳት የወር አበባቸው መቼ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ይረዳቸዋል።

1. በሁሉም ሴቶች መካከል ልዩነት ያለ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ የወር አበባ ዑደት 28 ቀናት ነው። ጤናማ የወር አበባ ዑደት ከ21 እስከ 35 ቀናት ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ የቀናት ብዛት ከወር ወር ሊለያይ ይችላል።
2. የራሳቸውን የወር አበባ ዑደት እንዲናገሩ ጥያቄ መጠየቅ። የወር አበባ ከጀመረበት ቀን እስከሚቀጥለው የወር አበባ ጊዜ ያሉትን ቀናት እንዲቆጥሩ ማድረግ። ይህም የወር አበባ ዑደታቸው ምን ያህል ቀናት እንዳለው ያሳያል።
3. ልጃገረዶች የወር አበባ ዑደታቸውን የቀን መቁጠሪያ/ካሌንደር ወይም ምልክቶችን በማስታወሻ ደብተር በመፃፍ ወይም ጠጠሮችን በቦርሳ በማስቀመጥ ወይም የአንገት ጌጥ ዶቃዎችን በመጠቀም ሊደርሱበት ይችላሉ።
4. ልጃገረዶች የወር አበባ ዑደቶችን ለተከታታይ ወራት በመከታተል በእያንዳንዱ ወራት ያሉት ቀናት ተመሳሳይ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
5. የወር አበባ በማያዩበት ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት ካደረጉ የማርገዝ ዕድላቸው ሰፊ መሆኑን ለልጃገረዶች ሊገለጽላቸው ይገባል። ይሁን እንጂ የወር አበባ እያዩም ቢሆን ሊያረግዙ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ ልጃገረገረዶችን በጥብቅ ማስታወስ ተገቢ ነው።
6. ልጃገረዶች የወር አበባ ሲያዩ የፍርሀት ስሜት እንዳያድርባቸው የወር አበባ የተለመደና ጤናማነት የሚሳይ መሆኑንና ሁሉም ልጃገረዶች በዚህ ሁኔታ እንደሚያልፉ እንዲያውቁ ማድረግ ተገቢ ነው።
7. የወር አበባን በተመለከተ የተማሩትን ለሚቀርቧቸውና ለሌሎች ጓደኞቻቸውና ቤተሰቦቻቸው እንዲነግሯቸው ገለፃ ማድረግ።
8. የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓዳቸውን የሚቀይሩበት የጊዜ ብዛት በወር አበባው ክብደት መጠን የሚወሰን መሆኑን ለልጃገረዶች መረጃ መስጠት።
9. ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ ፓዶችን መቀየር በጣም አስፈላጊ ነው።
10. በወር አበባ ወቅት ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ የገላቸውን ክፍል/ብልታቸውን በመታጠብ መጥፎ ሽታና ኢንፌክሽን መቀነስ እንዲችሉ ለልጃገረዶች ገለፃ ማድረግ።
11. በወር አበባ ወቅት የሚከሰት ሽታን ለመከላከል ዶድራንትና መሰል “የሽታ ማጥፊያ/መከላከያ” ምርቶችን በገላቸው ክፍል/ብልቶቻቸው ከመርጨት ይልቅ በውሀ እና በሳሙና ብቻ መታጠብ እንዳለባቸው አስፈላጊውን ምክር መስጠት። እነዚህ የሚረጩ “የሽታ ማጥፊያ/መከላከያ” ምርቶች የጎንዮሽ የጤና ጉዳት (ኢንፌክሽን) ሊፈጥሩና የበለጠ ሽታ እንዲኖራቸው ሊያደርጉ ይችላሉ።

የወር አበባ ዑደት መቼ ሊጀምር እንደሚችል ቀድመው ማወቃቸው በቂ ዝግጅት ለማድረግ እንደሚረዳቸው በመግለጽ ክፍለ ጊዜውን ማጠቃለል። ትምህርት ቤቱ በጣም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የሚጠቀሙበት የወር አበባ ንጽና መጠበቂያ ፓድ እንደሚያዘጋጅ (በትክክል ካዘጋጀ ብቻ) ማስታወስ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ ራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ አለባቸው። በምንም ዓይነት ሁኔታ ቢሆን በወር አበባ ምክንያት ልጃገረዶች ከትምህርት ገበታቸው ሊቀሩ እንደማይገባ በጥብቅ ማሳሰብ ተገቢ ነው።

ክፍለ ጊዜ 4:- መሠረታዊ የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ

ከወር አበባ ጤና አጠባበቅ በተጨማሪ ልጃገረዶች ካልተፈለገ እርግዝና እና በግብረ ሥጋ ግኙነት ሊተላለፉ ከሚችሉ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት (ኢንፌክሽን) ራሳቸውን መከላከል እንዲችሉ ስለ ሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ ማወቅ አለባቸው። ቀጥሎ ከተማሪዎች ጋር ሊካሄድባቸው የሚገቡ መሠረታዊ መረጃዎች ቀርበዋል። መረጃዎችን ማንኛውንም ሰው በማሳተፍ ውይይት ማካሄድ በተጠሪ ሴቶች መረጃው እንዲነገራቸው ማድረግ

በጣም የተሻለ ነው:: ውይይቱን በተመለከተ የሚከተሉትን ሁለት ቀላል ጥያቄዎች በመጠየቅ መጀመር:: ሁሉም ተሳታፊዎች በውይይቱ የሚሳተፉት ለመማር መሆኑን ተረድተው ጥሩ ስሜት (ምቾት) የተሰማቸው መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

1. ስለ እርግዝና (ነፍሠ ጡርነት) ምን ታውቃላች?
2. በግብረ ሥጋ ግኙነት ሊተላለፉ የሚችሉ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት (ኢንፌክሽን) እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምን ታውቃላችሁ?

የተለመዱ በግብረ ሥጋ ግኙነት ሊተላለፉ ስለሚችሉ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት (ኢንፌክሽን) አባባልና ልምዶች ፈ ታሪኮና እምነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል:: :

1. የሚከተሉትን አባባልና ልምዶች ከተነበበላቸው በኋላ እውነት ወይም ሀሰት መሆናቸውን እንዲናገሩ መጠየቅ::
2. የውይይቱ ተሳታፊዎች እውነት ወይም ሀሰት መልስ ከሰጡ በኂላ ለምን እውነት ወይም ሀሰት እንዳሉ ምክንያት እንዲያቀርቡ ማድረግ::
3. የእውነታው አጠቃላይ ገለፃ ሁሉም ተሳታፊዎች የተረዱት መሆኑን ማረጋጋጥ ይገባል:: አንድ ተማሪ የእውነታውን የተወሰነ ክፍል ምክንያት ከሰጠ ምላሹን ለሁሉም ተማሪዎች በማሰራጨት የተሟላ ገለፃ ለሌሎች እንዲሰሙትና እንዲረዱት ማድረግ::

አባባልና ልምዶች	አውነታ
አንዲት ልጃገረድ በመጀመሪያ ቀን የግብረ ስጋ ግንኙነት ብታደርግ ወይም ብትፈጽም ልታረግዝ አትችልም	ሀሰት፡- አንዲት ልጃገረድ በመጀመሪያ ቀን የግብረ ስጋ ግንኙነት ልታረግዝ ትችላለች
ክብረ ንጽህና ያላቸው ልጃገረዶች ወይም ሴቶች ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሊይዛቸው አይችልም	ሀሰት፡- ክብረ ንጽህና ያላቸው ልጃገረዶች ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሊይዛቸው ይችላል:: ኤች አይ ቪ በሰውነት ውስጥ ያለ ፈሳሽ ደምን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ ይችላል::
ኤች አይ ቪ በአስማት ወይም በእርግማን ሊተላለፍ ይችላል	ሀሰት፡- በአብዛኛው ኤች አይ ቬ የሚተላለፈው በደሙ የኤች አይ ቪ ቫይረስ ያለ ሰው በሚያደርገው ጥቃቄ በጎደለው ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው:: መታቀብ ኤች አይ ቪን በጣም ተመራጭ መንገድ ነው:: ውጤታማ የኮንዶም አጠቃቀም ደግሞ ሌላው ውጤታማ የኤች አይ ቪ መከላከያ መንገድ ነው::
የወሊድ መቆጣጠሪያ እንክብሎች በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ ከሚችሉ ኢንፌክሽኖች እና ኤች አይ ቪ ሊከላከሉ ይችላሉ	ሀሰት፡- በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ ከሚችሉ የጎንዮሽ የጤና ጉዳቶች (ኢንፌክሽኖች) እና ኤች አይ ቪ መከላከል የሚቻለው በመታቀብ እና በውጤታማ የኮንዶም አጠቃቀም ብቻ ነው::
የተወሰኑ የወሊድ መቆጣጠሪዎች መካንነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ	ሀሰት፡- ምንም ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ መካንነትን አያመጣም:: የማህፀን ቱቦ በቀዶ ጥገና ካልተዘጋ በስተቀር መካንነት አይኖርም::

አባባልና ልምዶች	እውነታ
በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ የሚችሉ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት (ኢንፌክሽኖች) መካንነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ	**እውነት፡-** በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ የሚችሉ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት (ኢንፌክሽኖች) በቀላሉ ሊድኑ የሚችሉ ቢሆንም የተወሰኑ በየግብረ ሥጋ ግኙነት ሊተላለፉ የሚችሉ ኢንፌክሽኖች ሳይታከሙ ለረዥምጊዜ ከቆዩ መካንነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ። በጣም ጠቃሚው ጉዳይ በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ በሚችሉ ኢንፌክሽኖች መያዝዎን ከተጠረጠሩ ወደ ህክምና ጣቢያዎች በፍጥነት መሄድ ነው።
ወንዶች ሴተኛ አዳሪ ናቸው ብለው ልጃገረዶች እንዳያስቧቸው ወንዶችን ኮንዶም ተጠቀሙ ብለው መጠየቅ የለባቸውም	**ሀሰት፡-** አንዲት ልጃገረድ የግብረ ስጋ ግንኙነት ለማድረግ ከወሰነች በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ ከሚችሉ ኢፌክሽኖች፣ ኤች ኤ ቪ እና ካልተፈለገ እርግዝና ራሷን ለመከላከል መወሰን አለባት። ወንዶች ልጃገረዶች ራሳቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉትን ጥረት የማይደግፉ ከሆነ የልጃገረዶቹ የጓደኛ ምርጫ ትክክለኛ አይደለም።

1. ስለ ሥነ ተዋልዶ አጠባበቅ በርካታ አባባሎች መኖራቸውን እና ሌሎች ወጣቶች የሚሉትን ሁሉ ማመን እንደሌለባቸው በመግለጽ ክፍለ ጊዜውን ማጠቃለል።
2. ከተጠሪ ሴቶችና ከጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች መረጃዎች ለማግኘት እንዲችሉ ልጃገረዶችን ማበረታታት።
3. ዝግጁ ሳይሆኑ ማንም ሰው ገፋፍቶ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ ሊያስገድዳቸው እንደሚገባ በጥብቅ ሊነገራቸው ይገባል። ዝግጁ ሳይሆኑ ማለት የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያስከትለውን አደጋ ማወቅ እና ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት መቀበል ማለት ነው።
4. ተማሪዎች የተማሩትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲወያዩበት ማበረታታት።

ተግባር 3 ማጠቃለያ:- ተግባርና ኃላፊነቶች

ትክተታዊ ሴቶች

1. በሦስቱ የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ክፍለ ጊዜያቶች ላይ ሥልጠና መስጠት
2. እያንዳንዱ ትክተታዊ ሴት የሁሉንም ልጃገረዶች ተሳታፊነት ለማረጋገጥ በተለያየ ጊዜ ክፍለ ጊዜያት በመያዝ ውይይት ማካሄድ አለባቸው። በተለያየ ምክንያት በውይይት ጊዜ ያልተሳተፉ ወይም ክለሳ ማድረግ የሚፈልጉ ልጃገረዶች ስለሚኖሩ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ላይ ከአንድ ጊዜ በላይ ውይይት ሊካሄድ ይገባል።

ተገቢ ምክር

የወር አበባ ልጃገረዶችን የሚያሳፍር ስሜት ሊሰማቸው ስለሚችል ሰፊ ትኩረት መስጠት አለበት።

መምህራን

1. ልጃገረዶች የወር አበባ ንጽህና እንዲጠብቁ መደገፍና በትምህርት ሠዓት ወደ መፀዳጃ ቤት በፈለጉበት ጊዜ ፈቃድ እንደሚሰጣቸው ለተማሪዎች ግልጽ ማድረግ።
2. የተማሪዎችን የግል ፍላጎት ማክበርና ከክፍል መውጣት የሚፈልጉ ልጃገረዶች ነፃነት እንዲሰማቸው ማድረግ።

ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

1. ተጠሪ ሴቶች ወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ክፍለ ጊዜያትን በማደራጀት ተግባር እገዛ ማድረግ።
2. ወላጆችና ወተመህ በክፍለ ጊዜያት ላይ በቂ መረጃ እንዲኖራቸውና በተቻለ መጠን በርካታ ሴት ተማሪዎች በውይይት መሳተፋቸውን ማረጋገጥ።

4. የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ ለሴት ተማሪዎች መስጠት

የሚወገድ ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የማይውል የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ ውድ ስለሚሆን ለሁሉም ሴት ተማሪዎች መስጠት አይቻልም። ተማሪዎች እና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ እንዲያዘጋጁ ትምህርት ቤቱ ድጋፍ መስጠት። በጣም ቀለል ያለ ሂደት መከተል ይቻላል። ለመጀመሪያ ጊዜ አዘገጃጀቱን የሚያሳይ ከአሁን በፊት የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ የመስፋት ልምድ ያለውን ግለሰብ ማግኘት ያስፈልጋል።

ተግባር 4 ማጠቃለያ: ተግባርና ኃላፊነቶች

ተጠሪ ሴቶች

1. ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓድ አዘገጃጀት ላይ ሴት ተማሪዎችን መደገፍና ምክር መስጠት።
2. ሴት ተማሪዎች እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓዶች ለመጠቀም በራሳቸው እንዲተማመኑ ማበረታታት

ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

- ለሴት መምህራን/ተማሪዎች እገዛ ማድረግና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓዶችን ለማዘጋጀት የሚረዱ ቁሳቁሶችን ማሟላት።

ተገቢ ምክር

ተማሪዎች እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓዶችን የሚጠቀሙ ቢሆንም በድንገት አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ እንዲጠቀሙበት አንድ ጊዜ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ፓዶች ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ይህም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ይረዳል።

5. የወር አበባን በተመለከተ በማህበረሰቡ ላይ ግንዛቤ መፍጠር

የወር አበባ በልጃገረዶች ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሰው እንደ መጥፎ ነገር ይታያል። እናቶች በወር አበባ ላይ አሉታዊ አመለካከት ስላለቸው ከልጆቸው ጋር በጉዳዩ ላይ አያወሩም። የወር አበባ “እርግማን” ወይም “ቆሻሻ መሆን” ነው የሚል የተሳሳተ እምነት እናቶች አላቸው። በተለያዩ የውይይት መድረኮች ስለ ወር አበባ በግልጽ እንዲናገሩ ማድረግ የማፈር ስሜታቸውንና የተሳሳተ እምነቶች ለመቀነስ ይረዳል።

ቀጥሎ በወር አበባ ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ የተወሰኑ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል



የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድረ ገጽ ተመልከቱ http://menstrualhygieneday.org/about/why-menstruationmatters/

በግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባዎች ወቅት ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ስጡ:

1. ብዙ ልጃገረዶች በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ቤት ይቀራሉ። ይሁን እንጂ በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት እንደሌለባቸው ማስገንዘብ ይገባል።
2. የወር አበባ ተፈጥሯዊ ስለሆነ በምንም ምክንያት አሳፋሪ ሊሆን አይገባም።
3. እናቶች ከሴት ልጆቻቸው ጋር የወር አበባን በተመለከተ መነጋገር አለባቸው። እናቶች ስለ ወር አበባ ትክክለኛ መረጃ ከሌላቸው ከተጠሪ ሴቶችመረጃ ማግኘት እንዲችሉ ሊነገራቸው ይገባል።
4. ወንዶች የወር አበባን በተመለከተ በፍጹም ሊቀልዱ አይገባም።
5. ትምህርት ቤቱ በወር አበባ ወቅት ልጃገረዶችን ለመርዳት ላከናወነው መልካም ተግባር ትኩረት መስጠት ወይም አጉልቶ ማሳየት አስፈላጊ ነው።
6. መረጃዎችን የማስተላለፍ ሂደት የፈጠራ ችሎታን መጠቀም ይጠይቃል። ለአብነት በጭውውት፣ በጥያቄና መልስ እና የአንድ ለአንድ ውይይት በማካሄድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቻላል። ይህን ርዕሠ ጉዳይ ማንም ሳያፍር ወይም ቅር ሳይሰኝ ውይይቱ እንዴት መካሄድ እንዳለበት ሊያውቅ ይገባል። ልጃገረዶች ከእናቶቻቸው፣ ከህቶቻቸው፣ ከአክስቶቻቸው እና ከሴት አያቶቻቸው ጋር የወር አበባን በተመለከተ በቤት ውስጥ በግልጽ እንዲነጋገሩ መበረታታት አለባቸው።

ተግባር 5 ማጠቃለያ: ተግባርና ኃላፊነቶች

ተጠሪ ሴቶች

- *ከማህበረሰቡ ጋር ለመነጋገር ወይም ለመወያየት የሚያስችሉ አጋጣሚዎች መፈለግ::*

ርዕሠ መምህራንና ምክትል ርዕሠ መምህራን

- ተጠሪ ሴቶች የወር አበባን በተመለከተ ከማህበረሰቡ ጋር ለሚያካሂዱት ውይይት እገዛ ማድረግ::

ክለሳ እና ማጠቃለያ

ሴት ተማሪዎች የወር አበባ ዑደታቸውን በአግባቡ እንዲቆጣጠሩና ከትምህርት ቤት መቅረታቸውን ለመቀነስ ተጠሪ ሴቶች እንዲረዷቸው መምራት የሚያስችሉ ቁልፍ ደረጃዎችን አካቷል:: ለብዙ ጊዜያት ሴት ተማሪዎች በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዴት እንደሚቀሩ አያውቁም ነበር:: ብዙ ልጃገረዶች በተለይም ከወንድ መምህራን ጋር ስለወር አበባ ለማውራት ወይም ለመነጋገር ያፍራሉ:: ስለ ወር አበባ መናገርን ለማስቀረት ሲሉ ልጃገረዶች ከትምህርት ቤት የቀሩበትን ምክንያት ሌላ እንደሆነ አድርገው ለመምህራን ሊነግሯቸው ይችላሉ:: በመሆኑም አሁን የሚደረገው አነስተኛ አስተዋጽኦ የሴት ተማሪዎች በትምህርት ቤት አዘውትሮ መገኘት እና ውጤታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽላል::

እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ፓዶች አሠራር

አስፈላጊ ቁሳቁሶች:

1. የወረቀት ንድፍ
2. ከጥጥ የተሠራ ጨርቅ (ያልደመቀ ወይም ጥቁር ቢሆን ይመረጣል)
3. የበግ ፀጉር (በጥቁር ለስላሳ ጨርቅ ወይም በጥጥ መተካት ይቻላል)
4. መርፌ (ለመስፋት የሚያገለግል)
5. መርፌ ቁልፍ ወይም የወረቀት መርፌ/ስፒል
6. ጠቆር ያለ ቀለም ያለው ክር
7. ንጹህ ፕላስቲክ
8. ከብረት የተሠራ ጥንድ መቆንጠጫ
9. ማርከር

***መመሪያዎች* (አሰራር ቅደም ተከተሎች):**

የወረቀት ንድፍ መስራት:

- *መጀመሪያን ድፉን መሳልና "የፓድ ንድፍ" ከክንፍ መሠሎች ጋር ቀጥሎ ከሚታየው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቆርጦ ማውጣት::* **ቁመቱ 26 ሳንቲ ሜትር፣ ስፋት 23 ሳንቲሜትር፣ ክንፎች ከ8 ሳንቲ ሜትር ያነሠ**



- ሬክታንግል መሳልና “የኪስ ንድፍ” ቆርጦ ማውጣት። ቁመቱ 13 ሳንቲ ሜትር፣ ስፋት 12 ሳንቲ ሜትር
- ሁለት “የፓድ ንድፎች” እና ሁለት “የኪስ ንድፎች” ከጥጥ ከተሰራው ጨርቅ አስደግፎ መገልበጥ።
- 22 ሳንቲ ሜትር በ22 ሳንቲ ሜትር የሆኑ ሁለት ካሬዎችን በበግ ፀጉር (ወይም የበግ ፀጉር የማይገኝ ከሆነ ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ መጠቀም ይቻላል) ላይ መሳል።
- ሁሉንም የጨርቅ ቁርጥራጮች ቆርጦ ማውጣት። ማጣበቂያው ባለበት በኩል እስከ መጋጠሚያው ማዕከል ድረስ በመቁረጥ ክፍት እንዲሆን በማድረግ አንድ ፕላስቲክ መቁረጥ። የተቆረጠውን ፕላስቲክ እንደ ፓዶች ተመሳሳይ በሆነ ቁመትና ስፋት እንዲጋጠም ማድረግ (ይህ ከክንፎቹ መብለጥ የለበትም)። ሁለቱን ኪሶች ከስፋቱ ወይም ከወርዱ ግማሽ ራቅ ብሎ ማጠፍ።
- በሁለቱ “የኪስ ንድፍ” ጫፍ ላይ በ½ ሳንቲ ሜትር ክፍተት በመስመር የልብስ መስፊያ ክር በመጠቀም መስፋት።
- የጨርቁን ተደራቢዎች ማገጣጠም/ማገናኘት። ከታች ወደ ላይ ፕላስቲክ ፓድ (1)፣ ሁለቱን “የኪስ ንድፍ” እና ፓድ (2) ማገናኘት። የሁለቱ ኪሶች የተሰፋው ጠርዝ ወደ ፓዱ መሀከል ማመልከት አለበት።
- የፓዱን የላይኛውና የታችኛውን ጠርዝ በስፒል ወይም በመርፌ ቁልፍ ማያያዝ። በምንም መልኩ ስፒል ወይም መርፌ ቁልፉ ቀዳዳ ሊፈጥር ስለሚችል በፓዱ መሀከል ላይ መያያዝ የለበትም። የፓዱ ሁሉም ጫፎች ሳይዛነፉ መገጣጠም አለባቸው።
- ¼ ኢንች ክፍተት በመተው የፓዱን ጫፎች ብቻ የልብስ መስፊያ ክር በመጠቀም መስፋት። በላይኛውና በታችኛው ክፍተቶች በኩል መሰፋት የለበትም። በክንፉ አካባቢ ፈሳሽ ካልሰረፀ መልካም ነው።
- ክፍተቱን በመጠቀም የውስጠኛውን አካል ወደ ውጭ መገልበጥ። የወር አበባ መምጠጫውም መካካል ላይ መሆን ይኖርበታል።
- ፓዱ ለጥ ያለ እንዲሆን መገጣጠሚያዎችን ማለስለስ። በ1/4 ኢንች ክፍተት ወደ መግቢያው በመስመር የልብስ መስፊያ ክር በመጠቀም መስፋት።
- ኪሶችን ወደ ላይ መገልበጥ። ይህ ገጽ የፓዱ ውስጣዊ ክፍል ይሆናል።
- የብረት መደሻ በመጠቀም የብረት መቆንጠጫዎችን ከክንፉ ጋር ማገናኘት። መቆንጠጫዎች ከጠርዞቹ 1/2 ኢንች በመራቅ በመሀከል ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ። የብረት መቆንጠጫ ማግኘት ካልተቻለ የፕላስቲክ መጠቀም ይቻላል። እነዚህ ነገሮች በልብስ ስፌት ቁሶች ሊገኙ ይችላሉ። ፓዱ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሟል። አሁን በመስመር እንሰፋለን።

ንጣፎችን መስራት:

ሁለቱን ንጣፎች (22 ሳንቲ ሜትር በ22 ሳንቲ ሜትር የሆኑ ካሬዎች) ጠርዞቻቸው እንዲጋጠሙ በማድረግ በአንድ ላይ ማስቀመጥ። በካሬዎች የውጫዊ ጠርዝ በኩል ጠቆር ባለ ክር መስፋት።

ንጣፎችን ከኪሶቹ ጋር እንዲገጥሙ በማድረግ ማጠፍ። አሁን ፓዱና ንጣፎች ተሰርተው ተጠናቀዋል። ንጣፎችን በየጊዜው ለመቀያየርና ለማጠብ ቢያንስ ከአንድ በላይ መስራት ያስፈልጋል።

የአስተጣጠብ መመሪያ ወይም የአሰራር ቅደም ተከተል:

ሁለቱም ፓዶችና ንጣፎች እንደማንኛውም ልብስ በንጽህና መስጫዎች እና በሳሙና ሊታጠቡ ይችላሉ። ንጣፎች ብዙውን የወር አበባ ደም ስለሚመጡ በተደጋጋሚ መቀየርና መታጠብ አለባቸው። ባክቴሪያዎችን መግደል እንዲቻል በፀሀይ እንዲደርቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

ተቀጽላ -1 የዳሰሳ ጥናቱ/ፍተሻ ግኝቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሔ ሀሳቦች
የተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥ	• የወላጅ/አሳዳጊ ድጋፍ ማጣት • በቂ የጥናት ጊዜ አለመኖር በተለይም ለልጃገረድ ተማሪዎች • የቤተሰብ ኢኮኖሚ ችግርና የቤተሰብ ተጽእኖ • የወላጆች/አሳዳጊዎች ሞት • የቤተሰብ ጋብቻ መፍረስ/መለያየት • ቤተሰባቸውን ለመደገፍ በገቢ ማስገኛዎች ለመሳተፍ መፈለግ • ጥሎሽን በመፈለግ ያለዕድሜ ጋብቻ መፈፀም • ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ያለ ርቀት • ከጤና ጋር የተያያዙ ችግሮች • በገጠር ማህበረሰብ አካባቢ አርአያ/ሞዴል የሆኑ ሴቶች አለመኖር • በአካዳሚ ጉዳይ ከትምህርት ቤት መሰናበት • በትምህርት ጠቀሜታ ላይ ባለ ግንዛቤ የአቻዎች ተጽእኖ • በአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች ለአብነት ሂሳብ፣ እንግሊዝኛ፣ ፊዚክስ ላይ ከባድ ትምህርቶች ናቸው የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ መኖር • የአቻ ግፊትና በትምህርት ቤት አካባቢ የቪዲዮ ቤቶች፣ ወዘተ መኖር • ስለ የወደፊት ህይወት ተስፋ ቢስ መሆን • የተማሩ ሰዎች አለመቀጠር (ሥራ ማጣት) • የምክር አገልግሎት አለመኖር • የመምህራን ባህሪያት • የመማሪያ ቁሳቁሶች አለመሟላት • የንጽህና መጠበቂያ ክፍሎች አለመኖር • በአንድ ክፍል ብዙ ተማሪዎች መብዛት/መጨናነቅ • የሥነ ሥርዓት ጉዳዮች- በትምህርት ቤት መጥፎ ባህሪያት መንፀባረቅ • የምግብ እጥረት	• ወላጆች ልለጆቻቸውን እንዲያጠኑ ማበረታታት አለባቸው • ርዕሠ መምህራን ከወላጆች ጋር በመስራት ህፃናት ለጉዳት እንዳይጋለጡ ደህንነታቸውን መጠበቅ • ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች እንዲቀንስና ያሉትም እንዳለ እንዲቀጥሉ ወተመህ ከርዕሠ መምህራን ጋር በቅንጅት መስራት አለባቸው • የተማሪዎች ባህሪይን በተመለከተ ትምህርት ቤቱ ከወላጆች መገናኘትና መነጋገር አለበት • ወላጆች የልጆቻቸውን አካዳሚያዊ እና የባህሪይ መሻሻል ወይም ተገቢ ያልሆነ ባህሪይ በቅርብ መከታተክ አለባቸው • ወላጆችና ተማሪዎች ያለ ዕድሜ ጋብቻንና ውጤታማ መማርን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረግ አለባቸው • የተማሪዎችን መማር ውጤታማ ለማድረግ ትምህርት ቤቱ ምን እየሰራ እንደሆነ መከታተል • የተማሪዎችን የማቋረጥ ምጣኔ ለመቀነስ በማህበረሰቡና በትምህርት ቤቱ መካከል ቅርብ ግንኙነት መመስረት • ትምህርት ቤቶች በመምህራን አማካኝነት የተማሪዎችን በትምህርት መገኘት በመከታተል • የትምህርት ቤቶች አቋራጭ ተማሪዎች አስመልክቶ ለተማሪዎች ምክር መስጠት • ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አካዳሚያዊ ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ ማበረታታት • የማህበረሰቡና ትምህርት ቤቶች ውጤታማ ለሆኑ ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት መስጠት • ትምህርት ቤቶች ዝቅተኛ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች ድጋፍ ማድረግ • ሴት ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለወላጆቻቸው ምክር መስጠት::

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሄ ሀሳቦች
የማንበብና የመፃፍ ክህሎቶች ደረጃ ዝቅተኛ መሆን	♦ የእንግሊዝኛ ቋንቋ በማንበብና በመፃፍ ለተወሰኑ ተማሪዎች ከባድ ስለሆነ ♦ የተወሰኑ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን በአግባቡ ማስተማር አለመቻል ♦ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመምህራን አካዳሚያዊ ብቃት አናሳ መሆን ♦ የተወሰኑ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ልምድ ደካማ መሆን ♦ በአንድ ክፍል ውስጥ በርካታ ተማሪዎች በመኖራቸው የመምህራን በግል ደረጃ ተማሪዎችን የመደገፍ ሁኔታ አናሳ መሆን ♦ የተማሪዎች መፃህፍትና የተጨማሪ የንባብ መፃህፍት እጥረት ♦ በትምህርት ቤቶች የቤተ መፃህፍትና የንባብ መፃህፍት እጥረት ♦ በቤት ውስጥ ተዘውታሪ የቤት ሥራ ጫና በተለይም በልጃገረድ ተማሪዎች መብዛት ♦ የጥናት ጊዜ አለመኖር ♦ የማጠናከሪያ ትምህርት አለመኖር ♦ ደካማ አፈፃፀም ላላቸው ተማሪዎች የሚደረገው ድጋፍ አናሳ መሆን ♦ የትምህርት መስጫ ቋንቋው ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ወደ አማርኛ መለወጥ (አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ባልሆነባቸው አካባቢዎች)	♦ የተወሰኑ ተማሪዎች በአፍ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ስለሚወዱ መበረታታት አለባቸው ♦ በትምህርት ቤት ውስጥ የአቻ ለአቻ የድጋፍ ሥርዓትን ማጠናከር ♦ አስፈላጊ የማጣቀሻ እና ተጨማሪ የንባብ መፃህፍት ማሟላት ♦ ቤተ መፃህፍት፣ የማንበብና መፃፍ ኮርነሮች ክበባት በትምህርት ቤት ውስጥ ማቋቋም (መፃህፍት ለመዋስ የሚያስችል ተለዋጭ ቤተ መፃህፍትማዘጋጀት) ♦ መምህራን ለተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ማበረታታት ♦ የተማሪዎችን መማር ለማሻሻል ተነሳሽነት ያላቸው መምህራን እንዲኖሩ ማድረግ ♦ የማንበብና መፃፍ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ለየት ያለ ድጋፍ መስጠት ♦ የተማሪዎችን በሂሳብና በፊዚክስ ትምህርት ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ለማስወገድ መስራት ♦ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለውን አዎንታዊ ግንኙነት ማሻሻል
የትምህርት ቤት አጠቃላይ ከባቢ ለመማር ምቹ አለመሆን	♦ በትምህርት ቤት ዙሪያ መጥፎ አካባቢ መኖር (እንደ ቁማር፣ ቪዲዮ ቤቶች፣ የጫት ቤቶች፣ የአልኮል መጠጦች እና የዕጽ ሱቆች) ♦ የመጠጥና የመታጠቢያ ውሀ አለመኖር ♦ በወር አበባ ወቅት ለልጃገረዶች አገልግሎት የሚሰጥ መፀዳጃ ቤት እጥረት ♦ ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ የመፀዳጃ ቤቶች እጥረት ♦ የመማሪያ ክፍል እጥረት በመኖሩ ምክንያት የተማሪዎች መጨናነቅ መፈጠር ♦ የተማሪ መማሪያ፣ የተማሪ መምህር እና የተማሪ መፃህፍት ጥምርታ በጣም ከፍተኛ መሆን ♦ የትምህርት ቤት የመማሪያ ቁሳቁስ አለመሟላት	♦ ቁማር፣ ቪዲዮ እና የአልኮል መጠጥን ከትምህርት ቤት ከባቢ እንዳይኖሩ ለመከላከል መስራት ♦ ትምህርት ቤቶች ለመማር -ማስተማር ስራ ምቹ አካባቢ እንዲሆኑ አልሞ መስራት ♦ ከቀበሌ አስተዳደርና ከፖሊስ ጋር በቅርብ በመስራት ትምህርት ቤቱን ከጎጂ ልማዶች መከላከል ♦ ጠንካራ የትምህርት ቤት መመሪያ በማውጣት ከአልኮሆል ሱሰኝነት ጉዳትና አደጋ ተማሪዎችን መከላከል ♦ የገቢ ማሳደጊያ መርሀ ግብሮችና የገቢ ማስገኛ ተግባራትን በመፍጠር የትምህርት ቤቱን መሠረተ ልማት ማሻሻል (የውሀ አቅርቦት፣ ለወንዶችና ለልጃገረዶች ለየብቻ መፀዳጃ ቤት፣ ቤተ- መፃህፍት፣ የንባብ ካምፕማሻሻል

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሄ ሀሳቦች
	• የላብራቶሪ፣ ኬሚካልና ቁሳቁሶች እጥረት • የመጫወቻ ሜዳዎች አለመኖር • ተማሪዎች ለመማር ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆን • አሉታዊ የሆነ የቤተሰብ ጫና • የመምህራንና ተማሪዎች ተጠያቂነት አለመኖር • ወላጆች/አሳዳጊዎች ለትምህርት የሚሰጡት ትኩረት አናሳ መሆን • የተጨማሪ መጻህፍት እጥረት • የመምህራን የማስተማር ክህሎት ደካማ መሆን • ንጹህ የመማሪ ክፍል አለመኖር • የተማሪ መፃህፍት አለመኖር • ጥራት ያለው የመማር ማስተማር ሂደት አለመኖር • የተሟላ የመምህራን ተነሳሽነት አለመኖር • በትምህርት ቤት ውስጥ ቁጥጥርና ድጋፍ አለመኖር • የአካል ጉዳት ላላቸባው ተማሪዎች ተስማሚ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች አለመኖር • የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች የተለየ አያያዝ አለመኖር • ትምህርት ቤቶችና የመመሪያ ክፍሎች ለአካል ጉዳኞች ምቹ አለመሆን	• በወር አበባ ወቅት የሚኖረውን ከትምህርት ቤት መቅረት ለመቀነስ ተጨማሪ ክፍሎችና መፀዳጃ ቤት ለልጃገረዶች መገንባት • የተማሪዎችን አካዳሚያዊ ብቃት ለማሻሻል ከማህበረሰቡና ከወላጆች ጋር የቅርብ ግንኙነት እና አጋርነት መመስረት • ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የጉዳታቸውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የተለየ እገዛ/አያያዝ መስጠት/ማድረግ • በሚመለከተው የትምህርት ጽህፈት ቤት በኩል መደበኛ ቁጥጥር እና የድጋፍ ክትትል ማድረግ • የመምህራንን አቅም፣ ተነሳሽነት እና የማስተማር ሥነ ዘዴን ማጠናከር • የመምህራንን በትምህርት ቤት መገኘትን መቆጣጠር እና በብዛት ከትምህርት ቤት እንዳይቀሩ ማረጋገጥ
የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎች (ተግዳሮቶች)	• ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ መፀዳጃ ቤቶች አለመኖር • ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድጋፍ የሚሰጡ መምህራን እጥረት • የአካል ጉዳት ላላቸባው ተማሪዎች ተስማሚ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች አለመኖር • የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች የተለየ አያያዝ አለመኖር:: • የመመሪያ ክፍሎች ለአካል ጉዳኞች ምቹ አለመሆን • ትምህርት ቤቶች ሲሰሩ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረጉ አለመሆን	• ተስማሚ የመማሪያ ቁሳቁሶች፣ ለመስማት አጋዥ የሆኑ መሳሪያዎች፣ የአይን መነፀር፣ ንጹህ የመጠጥ ውሀና የመፀዳጃ ቤቶች ችግሮችን መቅረፍ • ለሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ማቅረብ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑ • የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ችግር መለየት እና ፍላጎታቸውን መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ • የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ትምህርት ቤቶችን በተገቢ ሁኔታ ማደራጀት

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሄ ሀሳቦች
	• ትምህርት ቤቶችና ከባቢያቸው ለመማር ምቹ አለመሆናቸው • ትምህርት ቤቶች ከማህበረሰቡ ርቀት ያላቸው መሆን	• ህፃናት ያለባቸውን ጉዳት መሠረት በማድረግ ፍላጎታቸውን መረዳት • ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የመማር መሻሻል የመከታተል ኃላፊነት መውሰድ • መምህራን የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ችግር በመረዳት ችግራቸውን መሠረት ያደረገ ደጋፍ መስጠት
ቤተሰብ ሚዛናዊ ያልሆነ የወንዶችና የልጃገረዶች አያያዝ	• ወላጆች ልጃገረዶችን ተዘውታሪ የቤት ውስጥ ሥራ (ማብሰል/ወጥ መስራት፣ ማጽዳት እና በማንኛውም የቤት ውስጥ ሥራ) ያዟቸዋል:: ወንዶች ግን ለመጫወትና ለጥናት ነፃ ጊዜ ያገኛሉ:: • ሥራ ያልያዙ ተመራቂዎች መኖር ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ አለመበረታት • ወንዶች ብቻ ወደ ትምህርት መላክ አለባቸው እንዲሁም ትምህርት በቅድሚያ ለወንዶች መሰጠት አለበት ብለው የሚያምኑ ቤተሰቦች መኖር • አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ለወንዶች በትምህርት ቤት መገኘትና መማር ቅድሚያ የሚሰጡና ሴቶችን ግን ከአላስፈላጊ እርግዝና ለመከላከል እንዲያገቡ ነው የሚመርጡት • ልጃገረዶች ወደ ቤተ መፃህፍት ለመሄድና የማጠናከሪያ ትምህርት እንደ ወንድሞቻቸው ለመውሰድ ሙሉ ነፃነት የላቸውም • የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት ስለ ልጃገረዶች ትምህርት ጠቀሜታ ግንዛቤ የላቸውም::	• ቤተሰቦች ወንዶችና ልጃገረዶች በእኩል መንገድ መያዝ አለባቸው:: ለወንዶችና ልጃገረዶች እኩል ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል • ቤተሰቦች በትምህርት ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል • ትምህርት ቤቶችና የማህበረሰብ መሪዎች ትምህርት ለአገር ግንባታ እና የራሳቸውን የወደፊት ህይወት በአግባቡ ለመምራት ያለውን ጠቀሜታ ለወላጆች መረጃ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው:: • አባቶችና እናቶች በቤት ውስጥ ለወንዶችና ለሴቶች የተለያየ አያያዝ እያደረጉ ስለሆነ ተማሪዎች ራሳቸው በጉዳዩ ላይ ከወላጆቻቸው ጋር መወያየትና ስለ ትምህርት ጥቅም ሊገልጹላቸው ይገባል::

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሄ ሀሳቦች
ያለዕድሜ ጋብቻ	• በገጠር አካባቢዎች ልጃገረዶች ብዙ ጊዜ 18 ዓመት በታች ዕድሜያቸው ስለሚያገቡ ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ አልቻሉም • እናቶች ያለዕድሜ ጋብቻ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የገለጹ ቢሆንም አባቶች ግን ያለዕድሜ ጋብቻ ልማድ በመደበኛነት ተግባራትን የማከናወን መንገድ መሆኑን ተስማምተዋል • አብዛኛዎቹ የማህበረሰብ አባላት ያለዕድሜ ጋብቻን አይደግፉም። ይሁን እንጂ በተወሰኑ ቤተሰቦች ለክብር እና ለጥሎሽ ሲባል ያለዕድሜ ጋብቻን ይፈጽማሉ • ወላጆች ልጃገረዶች ከመደበኛ ጋብቻ በፊት ሊያረግዙ ይችላሉ ብለው ስለሚያስቡ ያለዕድሜ ጋብቻን የማይጎዳ ስልት አድርገው ይወስዳሉ • ማህበረሰቡ ያለዕድሜ ጋብቻን በህዝባዊ ስብሰባዎች መቃወም ይፈልጋል። እንዲሁም ልጆቻቸውን አሉታዊ ተጽእኖውን (የትምህርት ዕድል ማግኘት) ለህጻናት ያስተምራሉ።	• ያለዕድሜ ጋብቻን ለማስቀረት ብዙ ሥራ መሥራትን ይጠይቃል። ትምህርት ቤቶችና የማህበረሰብ መሪዎች ይህን ስህተት የሚፈጽሙ ወላጆችን በተገቢ ሁኔታ መንቀፍ አለባቸው። እነዚህን ዓይነት ወለጆች የግድ በህግ አግባብ ሊጠየቁ ይገባል። • በገጠር አካባቢ ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል ማህበረሰቡ፣ ወላጆች፣ የህግ አካላት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ማህበራት እና ፖሊስ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል። • ርዕሠመምህራን፣ወተመህእና የሥዓተ ፆታ/የልጃገረዶች ክበባት ያለ ዕድሜ ጋብቻ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ጋርግንዛቤ ኖራቸው ይገባል። ከጅምሩ ሊካላከሉት ይገባል። ተፈጽሞ ቢገኝ ለመንግስታዊ ተቋማት ጥቆማ መስጠት አለባቸው። • ትምህርት ቤቶች የማግባባትና የቅስቀሳ ሥራ የቅድሚያ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል።
የትምህርት ቤት ማህረሰብ ግንኙነት አናሳ መሆን	• ብዛት ቁጥር ያላቸው የማህበረሰብ አባላትና ወላጆች ከትምህርት ቤቶች ጋር መልካም ግንኙነት አላቸው። • የተወሰኑ የማህበረሰብ አባላትና ወላጆች በህፃናት ትምህርት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ከትምህርት ቤቶች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም። • ወላጆች ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱት ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ በምዝገባ ወቅት እንደ አሳዳጊ ፊርማ ለመፈረም ብቻ ነው። • በአንዳንድ ማህበረሰቦች ትምህርት ቤቱን ለማገዝና ተማሪዎችን ከአላስፈላጊ አደጋ ለመከላከል ትምህርት ቤቶች ከማህረሰቡና ከቀበሌ አመራሮች ጋር ጠንካራ ግንኙት አላቸው።	• የመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማ እንዲሆን ትምህርት ቤቱና ማህበረሰቡ ተቀራርበው መስራት አለባቸው። • ትምህርት ቤቶች ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር በኃይል ጥቃቶች አሉታዊ ተጽእኖ ላይ የግንዛቤ ማዳበሪያ ስራ መስራት አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ በሴቶች ላይ የኃይል ጥቃት በሚፈጽሙት ላይ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ መምከር። • ለተማሪዎች፣ ለወላጆች፣ ለማህበረሰቡ አባላትና ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ በትምህርት ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤ መፍጠር። • ወላጆች እና ማህበረሰቡ ከትምህርት ቤቶች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ትምህርት ቤቶች መደበኛ የውይይት መድረክ ማደራጀት አለባቸው።

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሄ ሀሳቦች
ለአቅመ አዳም በድረሱ ልጃገረዶች ላይ የሚደርስ ጥቃት	• አስገድዶ መድፈር፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ድብደባ እና የመማሪያ ቁሳቁሳቸውን በኃይል መቀማት፣ • ሴት ተማሪዎች ብዙ በወንድ ተማሪዎችና የሥነ ምግባር ችግር ባለባቸው ተማሪዎች ጥቃት ያጋጥማቸዋል፣ • አንዳንድ አባቶች የድብደባና የአካል ቅጣት በመፈፀም በሴት ልጆቻቸው ላይ ጥቃት ያደርሳሉ፣ • የልጃገረድ ተማሪዎች ምሳ በኃይል ቀምተው የሚበሉ ወንድ ተማሪዎች አሉ፣ • ትምህርት ቤቶች ሁልጊዜ ድህንነታቸው አስተማማኝ አይደለም። የተወሰኑ ሴት ተማሪዎች በመምህሮቻቸውና በወንድ ተማሪዎች ይዘለፋሉ/ ይሰደባሉ፣ • ልጃገረዶች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ በመንገድ ላይ በወንድ ልጆች ወይም በትልቅ ወንዶች ወይም ማንነታቸው በማይታወቁ አንግዳ መንገደኞች ጥቃት ይደርስባቸዋል፣ • ብዙ ጊዜ ጥቃት የሚደርሰው ተማሪዎች ወደ ትምህርት ሲሄዱና ከትምህርት ቤት መልስ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ነው። • ውንዶችና ሴቶች ላይ ጥቃት የሚደርስ ቢሆንም ሴቶች በጥቃቱ ለአደጋ ተጋላጭ ናቸው። • የባህሪይ ችግር የጥቃት ወንጀል ለመፈፀም እንደምክንያት ተጠቅሷል። • የአካልና የሥነ ልቦና ስድቦች በትምህርት ቤት ወስጥና በትምህርት ቤቱ አካባቢ የተለመደ ነው። • ሴቶችን ማስፈራራት፣ የትምህርት ቁሳቁሳቸውን መቀማትና መሳደብ፣	• የትኛውም ቦታ ለልጃገረዶች ደህንነት ተስማሚ እንዲሆን ማህበረሰቡ ጥንቃቂ ማድረግ፣ • ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ሲከሰት ልጃገረዶች ሪፖርት እንዲያደርጉ ማብቃት ወይም ኃላፊነት መስጠት እና ትምህርት ቤቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣ • ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጃገረዶችን ከጥቃት ለመከላከል ከወላጆች፣ ከቀበሌ አመራሮችና ከፖሊስ ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግ፣ • የልጃገረዶችን ጥቃት ለመከላከል የተማሪዎችን፣ የወላጆችንና የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ • ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር በየጊዜው ሳይስተጓጎል የሚካሄድ የውይይት መድረክ ማደራጀትና ማመቻቸት፣ • የአመራርና የምክር አገልግሎት እና የሥነ ሥርዓት እርምጃ በትምህርት ቤት ውስጥ ማጠናከር፣ • የሥርዓተ ፆታ/የልጃገረዶች ክበባትን ማጠናከር፤ • ትምህርት ቤቶች ሴት ተማሪዎችን ከጥቃት ለመከላከል ከማህበረሰቡና ከፖሊስ ጋር በትብብር መስራት፣ • ማህበረሰቦች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የፍትህ አካላት፣ ፖሊስ፣ እና ወላጆች ለማንኛወም ጥቃት ምላሽ መስጠት አለባቸው፣ • ትምህርት ቤቶችና ቤተሰቦች ማንኛውንም ጥቃት ለፖሊስና ለህጋዊ የፍትህ አካላት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፣

የመማር መሰናክሎች	በተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች	የመፍትሄ ሀሳቦች
ለአቅመ አዳም በደረሱ ልጃገረዶች ወይም ለአደጋ ተጋላጭ ተማሪዎን ለመርዳት ተስፋ ሰጪ አገልግሎት አለመኖር	• ትምህርት ቤቶች ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች ለመርዳት የሚያችላቸው የተለያዩ አገልግሎቶች የላቸውም::	• የማህበረሰብ ወይይት በተለይም በትምህርት ቤቶች እና በወላጆች መካከል ማካሄድ፣ • ለልብስ፣ ለምግብ፣ ለቤት ኪራይ/ለመጠለያ እና ለትምህርት ቁሳቁሶች የሚሆን ድጎማ ማድረግ፣ • ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጃገረዶችን ለመርዳት የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ግናዛቤ ማሳደግ፣ • ተጨማሪ አጋዥ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፣ • ለተሻለ አፈፃፀም እና ውጤት አጋዥ የሆኑ ጥናቶችን መደገፍ፣ • የትምህርት ጠቀሜታን አስምክቶ ለተማሪዎች ምክር መስጠት፣ -+ • በቤት ውስጥ የሥራ ጫናን መቀነስና ወላጆች ለልጃገረዶች በቂ የጥናት ጊዜ እንዲሰጡ ማድረግ፣
ለአደጋ በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች ደጋፍ አለመኖር	• ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች አነስተኛ የሚባለው ድጋፍ አለመኖር (ምግብ፣ ልብስና የትምህርት መሳሪያዎች/ቁሳቁሶች)፣ • ልዩ ፍላጎት ትምህርት ላላቸው ህፃናት (የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ለአብነት የአካል ጉዳት፣ የአእምሮ ውስንነት እና የመማር ውስንነት ያለባቸው) እገዛ/ድጋፍ አለማድረግ፣ • በድርቅና የርስ በርስ ግጭች ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ህፃናት፣ • በክፍተኛ ደረጃ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑና ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ/ኤድስ ያጡ ህፃናት፣ • የተማሪዎች የመምህራንነ፣ የወላጆችንና የወተመህን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ መፈለግ፣	• የትምህርት መሳሪዎች/ቁሳቁሶች ማቅረብ/መስጠት፣ • ተጨማሪ የንባብ መፃህፍትን/ጽሁፎችን ማቅረብ፣ • ለማንባብና ለመፃፍ የሚሆን ጊዜ ማመቻቸት፣ • በቤት ውስጥ ከፍተኛ የሥራ ጫና ላለባቸው ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ የማካካሻ ድጋፍ መስጠት፣ • የንባብ ቁሳቁሶችን ማቅረብና ቤተ መፀሀፍትን በወንበርና ጠረጴዛ ማደራጀት፣ • ለተማሪዎች ውጤታማነትና ስኬት ለመደገፍ የመምህራንን አቅም መገንባት፣

Reference Materials

1. Assessment of Learning Disabilities: Cooperation Between Teachers, Psychologists and Parents- African Edition.2011.
2. Convention on the Rights of the Child. September 1990, in accordance with article 49.
3. Dropout Risk Factors and Exemplary Programs – A Technical Report. National Dropout Prevention Center/Network at Clemson University and Communities in Schools, Inc. May 2007.
4. Education Crisis Response Project –Facilitator's Guide – Social and Emotional Learning. Creative Associate International. August 2015.
5. Ethiopian Education Cluster- Education in Emergency Strategic Organizational Plan. 2017.
6. Federal Democratic Republic of Ethiopia – General Education Quality Improvement Program for Equity (GEQIP-E). Document of the World Bank- for official use only- Report No: 121294 –ET. 2017.
7. Learning Training Sessions – Positive Discipline Training Manual.
8. Minimum standards for Education: Preparedness, Response, Recovery. INEE, 2012.
9. Ministry of Education -Ethiopian Education Sector Policy and Strategy, 1994.
10. Ministry of Education -General Education Quality Improvement Package.1999 E.C
11. Ministry of Education – Governing Guideline for the Implementation of School Improvement program. Revised. Addis Ababa. May 2011.
12. Ministry of Education - Practical Teacher's Manual for Inclusion of Students with Disabilities at Classroom level.2017.
13. Ministry of Education -School Improvement Program Frame Work. Revised, May 2011.
14. Preventing School Dropout - Early Warning System –Programming Guide; Creative Associate International. Washington, DC. August 2015.
15. Preventing School Dropout- Enrichment Program, Programming ide. 2015.
16. Training for primary School Teachers in Crisis Context, Module 2 - Child Protection, Wellbeing and Inclusion Summary.
17. NESCO, 2009.
18. UNICEF - The Fight Against Discrimination. Paris. 2009.
19. UNICEF, 2009/2010.
20. Universal Design for learning to help All Children to Read; Promoting Literacy for Learners with Disabilities: Toolkit for International Education Stakeholders. First edition.
21. World Bank - African Social Sector Strategy.Washington D.C. 2009.
22. World Bank, 2010.
23. World Bank - Out-of-School Youth in Sub-Saharan Africa -A Policy Perspective. 2015.
24. *https://en.wikipedia.org/wiki/At-risk_students.*

25. *https://www.st-andrews.ac.uk/vulnerablestudentspolicystatement.*
26. *https://www.positivediscipline.com.*
27. https://www.positivediscipline.com.
28. *https://supportiveschooldiscipline.org/learn/reference-guides/positive-approaches-school-discipline.*
29. *https://www.bing.com/positive discipline in schools' article form.*
30. *https://www.unicef.org/disabilities.*
31. *http://www.pbs.org/parents/education/learning-disabilities/inclusive-education/*
32. *https://sites.highlands.edu/student-support-services/disability*-

የሞጁሉ አጠቃላይ እና ዝርዝር የሰልጠና ዓላማዎች

ይህ ሞጁል የተዘጋጀው የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች የአሰልጣኞች ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንን፣ ወላጅ-መምህር-ተማሪ ህብረት ተወካዮችን፣ የሥርዓተ ፆታ አስተባባሪዎችን በሪድ- II ፕሮግራም የትምህርት ቤት አመራርን አቅም የመገንባት ስልጠናን በመጠቀም በሥራው ውጤታማ እንዲሆኑ በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችን ለማሰልጠን ነው፡፡

ዓላማውም የህፃናትን መሠረታዊ የአፍ-መፍቻ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ከማሻሻል በተጨማሪ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን ድጋፍ በማድረግ የትምህርት ውጤታቸውን ለማሻሻል፣ የማቋረጥና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን ለመከላከል ነው፡፡ እያንዳንዱን ሞጁል ውጤታማ ማድረግ የሚያስችሉ መሠረታዊ ስልቶች ደግሞ በሰነዱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ከላይ የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት በእያንዳንዱ ሞጁል አሰልጣኖች የሥልጠናውን ይዘትና ከትምህርት ቤት አመራር ጥበብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በብቃት ለማስተላለፍ የሚያግዙ መመሪያዎች ቀርበዋል፡፡

ሞጁል 1፡- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት

የአቀራረብ ዘዴዎች፡- የባለሙያዎች ውይይቶች፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ ጥያቄና መልስ፣ የጥያቄ ካርዶች፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለፃና ዋና ዋና ማጠቃለያዎችን መስጠት

የተሰጠ ጊዜ፡- 2 ሰዓት

ዝርዝር የስልጠናው ዓላማዎች

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ስልቶችና ዘዴዎች በክፍል ውስጥ እንዲተገበሩ የሚያስችል ስልጠና ለትምህርት ቤት አመራር አካላት ይሰጣሉ፣
- ተማሪዎች በየቀኑ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት/አለመገኘታቸውን በመከታተል የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች በመደገፍ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ያደርጋሉ፣
- በትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን የቀሪ ሁኔታ የሚከታተል ቡድን በማደራጀት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አዘውትረው እንዲገኙ ያደርጋሉ፡፡

ሞጁል 2፡- የመጀመሪያ ደረጃ ልዩታ

የአቀራረብ ዘዴዎች፡- የባለሙያዎች ውይይቶች፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ ጥያቄና መልስ፣ የጥያቄ ካርዶች፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለፃና ዋና ዋና ማጠቃለያዎችን መስጠት፤

የተሰጠ ጊዜ፡- ½ ሰዓት

ዝርዝር የመማር ዓላማዎች

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- የክፍል ስም ጠሪ መምህራን በክፍል ውስጥ የተለየ የትምህርት አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች እንዲለዩ በማስገንዘብ በዚሁ መሠረት መምህራን ተማሪዎቹን እንዲደግፏቸው ያደርጋሉ፡፡
- የእያንዳንዱን ተማሪ መሠረታዊ የመማር ክህሎት በመገንዘብ ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለይቶ ወደ ከፍተኛ የመማር ክህሎት ከመሸጋገራቸው አስቀድሞ ትርፍ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ እገዛ ያደርጋሉ፡፡
- ተማሪዎች የአፍ መፍቻና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፊደላትን በአግባቡ እንዲያነቡ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

ሞጁል 3:- ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻ

የአቀራረብ ዘዴዎች፡- የባለሙያዎች ውይይቶች፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ ጥያቄና መልስ፣ የጥያቄ ካርዶች፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለፃና ዋና ዋና ማጠቃለያዎችን መስጠት

የተሰጠ ጊዜ፡- 1½ ሰዓት

ዝርዝር የመማር ዓላማዎች

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- ወላጆችና አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን በትክክለኛው ዕድሜና ጊዜ ትምህርት ቤት እንዲያስገቡ፣ያበረታታሉ፡፡
- አዲስ ገቢ፣ ነባርና አቋራጭ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የማምጣት ዘመቻን ማስጀመርና ተግባራዊ ማድረግ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት መጥተው እንዲመዘገቡ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት የግንዛቤ ማዳበር ሥራ ይሠራሉ፡፡

ሞጁል 4:- ለህፃናት ምቹና ተስማሚ የትምህርት ቤት አካባቢ

የአቀራረብ ዘዴዎች፡- የባለሙያዎች ውይይቶች፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ ጥያቄና መልስ፣ የጥያቄ ካርዶች፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለፃና ዋና ዋና ማጠቃለያዎችን መስጠት ይሆናሉ፡፡

የተሰጠ ጊዜ፡- 2½ ሰዓት

ዝርዝር የመማር ዓላማዎች

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- ለህፃናት ምቹና ተስማሚ የትምህርት ቤት አካባቢ መፍጠር ለችግር የተጋለጡና ችግር ላይ ያሉ ህፃናት አካላዊ ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ አጠቃላይ ደህነታቸው የሚጠበቅ እንደሆነ የሚሰማቸውና እንችላለን ብለው የሚያስቡ ተማሪዎች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡
- ተማሪዎች በተለይም ሴቶች አዘውትረው በትምህርት ገበታ ላይ በመገኘት ውጤታቸው እንዲሻሻል ምቹና ተስማሚ የትምህርት ቤት አካባቢ ይፈጥራሉ፡፡
- ስደተኞች በሰፈሩባቸው ቦታዎች (refugee camps) እና አካባቢያዊ በሆኑ የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ተፈናቃይ የሆኑ ህፃናት፣ የአርብቶ አደር ልጆች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናትና ወጣቶች በተገቢው ዕድሜያቸው ወደ ትምህርት ቤት መምጣታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

ሞጁሉ 5:- ግብረ-ገብነት እና የትምህርት ቤት ህግና ደንብ

የአቀራረብ ዘዴዎች:- የባለሙያዎች ውይይት፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች

የጥያቄና መልስ ክፍል; የጥያቄ ካርድ ; የሚና ጨዋታ፣ ገለጻና ዋና ዋና ማጠቃለያዎች መስጠት

የተሰጠው ጊዜ: -1½ hours

ዝርዝር የመማር አላማዎች

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች:-

- ሁሉም የትምህርት ቤቶች አመራሮች ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ እንዲከታተሉ የሚነቃቃ ጥሩ የትምህርት አካባቢ መፍጠር ላይ መሰረት በማድረግ ስለ ግብረገብነት ግንዛቤ ያዳብራሉ:: :
- የተማሪዎችን በራስ መተማመንና የትምህርት ውጤት ለማሻሻል ይችላሉ፤ የተከበሩና ከሁከት ነጻ የሆኑ ደህንነታቸው የተጠበቁ የትምህርት አካባቢዎች ያደራጃሉ::

ሞጁሉ 6:- የማህበራዊ ስሜቶች ትምህርት

የአቀራረብ ዘዴዎች:- የባለሙያዎች ውይይት፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ የጥያቄና መልስ ክፍል; የጥያቄ ካርድ፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለጻና ዋና ዋና ማጠቃለያዎች መስጠት

ሰአት:-1:30

ዝርዝር የመማር አላማዎች

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች:-

- የማህበራዊ ስሜት ትምህርት(ማስት) ጽንሰ ሃሳብን በመገንዘብ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የትምህርት አቀባበል እንዲሻሻል ይረዳሉ::
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በየዕለቱ ስለሚያጋጥሟቸው ጉዳዮች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛሉ::
- ውጤታማ ራስን የመምራት ዘዴዎችን በማስተማር ህፃናትን በተለይም የወጣት ሴቶችን አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ይገነዘባሉ፤ ድጋፍ ያደርጋሉ::
- የትምህርት ቤቱ አመራሮች ህፃናት በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ሃላፊነት እንደሚሸከም አካል ተግባርና ሃላፊነቶችን እንዲረዱ ያደርጋሉ::
- በህጻናት ደህንነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችንና መፍትሄዎችን እንዲሁም የወንዶችና የሴቶች ልዩ ችግሮችንና ፍላጎቶችን በተጨማሪም በችግር ጊዜ የሚሰጥ ድጋፍን ይለያሉ::

ሞጁል 7:- አካቶ ትምህርት

የአቀራረብ ዘዴዎች:- የባለሙያዎች ውይይት፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ የጥያቄና መልስ ክፍል፣ የጥያቄ ካርድ፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለጻና ዋና ዋና ማጠቃለያዎች መስጠት

የተሰጠው ጊዜ:- 2 ሰአት

ዝርዝር የመማር አላማዎች:-

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡- :

- የአካቶ ትምህርት ዋና መርሆዎች ላይና አካዳሚያዊ አለመግባባቶችን አለማቀፋዊ በሆነ አሰራር ለማሻሻል የጋራ የሆነ ግንዛቤን ያዳብራሉ፤ አካታች አካባቢዎችን ይፈጥራሉ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፖሊሲና ትግበራን ይቀርፃሉ፡፡
- የአካቶ ትምህርት ተግባራዊ ልምዶች በመምህራን የቅድመ ስራ ላይ ስልጠና ዝግጅት፣ በመምህራን የስራ ላይ ስልጠናና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች የሚያግዝ ሥርአተትምህርት በማዘጋጀት ሂደት እንዴት ግንዛቤ እንደሚያዝባቸውና እንደሚተገበሩ ይለያሉ፡፡
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ጉዳት ከሌለባቸው ጓደኞቻቸው ጋር በሁሉም የትምህርት ቤት ተግባሮች እንዲሳተፉና ያላቸውን ሙሉ አቅም እንዲጠቀሙ ማካተትን ይረዳሉ፡፡
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች መገለልና መከልከል ሳይደርስባቸው ቀጣይ የትምህርት ህይወታቸውን በስኬታማነት እንዲመሩና በማህበራዊ ግንኙነቶች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ የተለያዩ አካታች ልምዶችን ይገነባሉ፡፡
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር እኩል የትምህርት ዕድል እንዳያገኙና የሚጠበቁ የትምህርት ውጤቶችን ለማምጣት እንቅፋት እንዲያጋጥሟቸው የሚያደርጉ በአካቶ ትምህርት ዙሪያ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ያውቃሉ፡፡

ሞጁል 8:- የፆታ እኩልነት ያለባቸው ትምህርት ቤቶችን መመስረት

የአቀራረብ ዘዴዎች:- የባለሙያዎች ውይይት፣ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች፣ ውስን ጥናት፣ የጥያቄና መልስክፍል፣ የጥያቄ ካርድ፣ የሚናጨዋታ፣ ገለጻና ዋና ዋና ማጠቃለያዎች መስጠት

ዝርዝር የመማር አላማዎች:-

ክፍል 1:- ለሁሉም ጾታዎች ምቹ የሆነ የትምህርት አካባቢ ማረጋገጥ

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- የጾታ እኩልነት ያለበት ትምህርት ቤትን መመስረት የሚያስችለው ምን እንደሆነ ይረዳሉ፡፡
- የጾታ እኩልነት ያለበት ትምህርት ቤት የራስ ምዘና የውጤት ካርድና በክፍል ውስጥ የጾታ እኩልነት የክትትል ማስታዎሻ እንዴት እንደሚጠቀሙ ይረዳሉ፡፡
- የጾታ እኩልነትን በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ ለማሻሻል ሊወሰዱ የሚችሉ ርምጃዎችን እንዴት ማዋሃድ እንደሚቻል ይገነዘባሉ፡፡

ክፍል 2:- ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ጥቃቶችን መከላከል

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ኮሚቴ በማቋቋም ሂደት የአፈጻጸም ደረጃዎችን ይረዳሉ፡፡

- ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ኮሚቴ ዋና ሃላፊነቶች ይገነዘባሉ።
- ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ቅሬታን በሚቀበሉ ጊዜ ርህራሄ፣ ብቃትና ምስጢር ጠባቂነት ተፈላጊ ክሂሊች መሆናቸውን ይረዳሉ።
- ከትምህርት ቤት ጋር በተገናኙ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች የተጎዱ ሰዎች እንዴት አገልግሎት እንደሚሰጣቸው ይገነዘባሉ።

ክፍል 3: የሴቶች አመራርን ማበረታታት

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- በትምህርት ቤት ውሥጥ ለይስሙላ ያልሆነ እውነተኛ የሴት አመራር እንዴት እንደሚበረታታ ይገነዘባሉ።
- ከጥሩ አመራርነት ጋር የተያያዙ ጥቂት ዝርዝር ክሂሎችን ይረዳሉ።
- ሴቶች የተሻሉ መሪዎች መሆን እንዲችሉ ለመምራት ግንዛቤ ይጨብጣሉ።

ክፍል 4:- ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን (SRGBV) ለመከላከል የወላጅ የመምህራንና የተማሪዎች ህብረት (ወተመህ) የማህበረሰብ ትውውቅ፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት(FGM /C) እንዲሁም የፆታ እኩልነትን መስበክ

- ሴቶችንና የሴቶችን ትምህርት የሚጎዱ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ የማህበረሰብ ሁነቶች ለማከናወን የሚረዱ ጥቂት ስልቶችን ይረዳሉ።
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት (FGM)፣ ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና (SRGBV) የፆታ እኩልነት አለመኖር እንዴት በሴቶች ትምህርት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ቁልፍ ሃሳቦችን ይገነዘባሉ።

ክፍል 5: የወር አበባ ሑደትና መሰረታዊ የስነ-ተዋልዶ ጤና

ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች፡-

- ልጃገረዶች በወር አበባ ምክንያት ትምህርት እንዳያቋርጡ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይገነዘባሉ።:
- ለሴቶች ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዴት እንደሚደራጅ ይረዳሉ።
- በወር አበባ ጊዜ በሚደረግ ጥንቃቄና በተዋልዶ ጤና ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚረዱ ቁልፍ ጉዳዮችንና ስልቶችን ይገነዘባሉ።
- እንደገና አገልግሎት የሚሰጡ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያዎች እንዴት እንደሚዘጋጁ ይገነዘባሉ።

READ II - School Improvement Program Integration & Grant Guidelines

The READ II project, funded by USAID/Ethiopia, has a goal supported by three intermediate results: IR 1. Improved classroom reading and writing instruction; IR 2. Strengthened community engagement in education activities, and IR 3. Improved leadership, management, and delivery capacity at each administrative level.

READ II's objective is also supported by three cross-cutting and complementary components:

- Interventions that can prepare a range of vulnerable and at-risk students to succeed;
- Implementation of a structured gender approach to increase girls' and boys' grade retention and grade progression at key grades in targeted regions, zones and woredas.
- Use of a Crisis Modifier to provide educational support and other services for students who are internally displaced by conflict or other emergencies so that they might return back to and succeed in their learning.

The major focus of READ II's SIP grant is to improve cross-cutting issues prepare vulnerable and at-risk students to succeed and improve their learning and the learning outcomes.

Schools are expected to promote effective learning and retention of at-risk and vulnerable students. To this effect, schools should primarily identify problems related to at-risk and vulnerable students and design strategies to support these group particularly adolescent girls and prioritize each school domain and set goals;

- to improve their school performance, with a special focus on improving the quality of teaching and learning.
- to allow schools to improve their teaching and learning environments. that contains gender-focused activities and benefits girls.

Each school will use the grant to improve school performance specific with reading proficiency and support activities for girls.

- Create favorable condition and environment of education for students whereby developing their interest in education and improving their capacity through integrating READ II SIP interventions to student success and support toolkits (SSST) and SIP school grant provision to improve cross-cutting issues prepare vulnerable and at-risk populations to succeed

READ SIP Grant Management

- READ II SIP grants are payments made to government project schools, based on an assessment of school priority plans submitted to READ II through Woreda Education Offices (WEOs). READ II School Grants are to be spent and administered by each school's Parent, Teacher, and Student Association (PTSA)

- READ II SIP Grants are not meant to replace any existing and/or ongoing funding that is provided to the school by government, other partners, parents or the community. READ II SIP Grants are an additional contribution.
- Each school will use the existing PTSA to manage the READ II School Grant and establish READ II SIP grant sub-committee should have five members who can identify at-risk students' areas of support (at least 50% of committee members must be women and students).
- Members of this committee are drawn from teachers, administration staff, students, parents and the community chaired by the School Director. For READ II activities, School Improvement Committees should also engage the Gender Club Coordinators and any other individuals who participated in the READ II SSST training.
- Each school will submit a priority plan to the Woreda Education Offices.
- PTSAs in schools will play a key role in managing READ II SIP Grants. They will actively participate in planning and implementation and report to WEOs and READ II. They should keep all the relevant documents of READ II SIP Grant implementation.
    - At each school, a READ II School Grants Notice Board must be placed in a public place and made accessible to parents and community members, with information about the READ II School Grants Program, when and how much was received, and for what major areas are used.

Specific Roles and Responsibilities of School Improvement Committees

- School improvement committee has a responsibility in **developing, reviewing, and revising the school improvement plan** for the purpose of improving student performance for all student populations with respect to the student achievement and any other appropriate performance including considering special needs populations.
- Design and implement a system to enable the school community to participate in the school improvement planning.
- Monitor closely the school improvement activity plan and performances and provide the necessary assistance and support.
- READ II requires all schools improvement committees which receive school grants **to engage actively to improve their school performance in supporting vulnerable and at-risk students**. For READ II's school grant, this Committee is responsible to prepare the school grant application, involve school stakeholders, implement activities, monitor progress, and share updates and final results of school grant activities.
- School Improvement Committees are accountable to the School Directors and PTSA Chairpersons.
- Submit annual report to the school community on the school improvement performances undertaken by the school and notify the local community about the status of the school based on the result of the evaluation.

- Increasing the awareness of parents and the community about education through different means whereby making it possible for them to have sense of belongingness for the education task;

READ II Major Components Integrated to SIP Planning

The following major areas should be considered during SIP integration school level planning.

- In each school, a set of 'student services', that support students' life skills development and promote a healthy and safe school environment, will be offered;
- SIP integration should emphasize code of conduct, abolishing corporal punishment, creating child friendly school environment, supporting vulnerable and at-risk students to succeed, improving language of instruction, and other school support services like remedial/tutorial classes;
- Work towards increasing student enrollment, re-enrollment (re-entrant) and increasing retention and student survival rate;
- Conducting enrollment and re-enrolment campaign to increase access in READ II target schools encouraging parents to re-enroll their children, including girls and the disable children;
- Identifying vulnerable and at-risk students and design support interventions to minimize student dropout and to be successful in their learning through launching first response activities to increase awareness, attendance, engagement, and performances;
- Ensuring the formulation of plan to identify children with special needs and addressing of their needs;
- Integration of early warning system (EWS) through tracking student attendance for remedial actions for their learning successes;
- Identifying vulnerable and at-risk students particularly adolescent girl's priority needs and design strategies to support them for success;
- Encourage students to participate in Gender/Girls' Clubs, extracurricular activities and other relevant clubs to develop their social and emotional learning and other positive habits and cultures;
- Provision of supplementary after learning classes, catchup and enrichment classes to support student success for effective learning and to increase their learning potentials;
- Provision of special support for disable students - disability accommodation interventions;
- Schools to closely work with READ II local implementing partners (LIPs) for the success of community outreach program to mobilize parents and communities to focus on student attendance, engagement, performances through increasing their reading and writing capacities;

- Establishing a set of 'student services' that support students' life skills development and promote a healthy and safe school environment, will be offered;
- Encourage students in participation to fight against traditional and cultural practices that hinder the education of girls like early marriage, and female genital circumcisions (FGM) and related matters;
- Strengthening school- parent/community relationships to effectively implement school annual work plans on how to improve school and involve them in the process.
- Disseminating best practice within and from the surrounding schools or within the cluster schools;

Responsibilities of WEOs, Cluster Supervisors, and READ II staff

Woreda Education Offices, Cluster Supervisors, and READ II staff will lead the following illustrative technical activities:

Task 1: Support school-communities to develop and implement priority plans;

Task 2: Conduct cluster-based workshops with stakeholders to guide planning, intervention selection, and grant allocation;

Task 3: Conduct monitoring visit with stakeholders;

Task 4: Disburse the approved READ II school grant to each school as per thresholds;

Task 5: Monitor the submission of timely accomplishment report including financial reports/ narratives.

READ II — School Improvement Grant Allocation Action Plan

School Name	____________			Budget Year : ____________			
Woreda	____________	Number of Students		Male ________ Female ________ Total________			
Zone	____________	Number of Teachers		Male ________ Female ________ Total ________			
Region	____________	School Bank Account Number		____________	Name of the Bank & Location____________		
The list of main activities to support At-risk students with major emphasis to adolescent girls							
Activity in teaching and learning	Responsible Bodies	Budget (Birr)	Timeline	Activity in supporting at-risk students and girls focused	Responsible Bodies	Budget (Birr)	Timeline

Total Budget in Birr ____________ (________________________________)

Name of the School Director ____________________ Date __________

Name the PTSA Chairperson ____________________ Date __________ School Seal

Approved by ______________ (Woreda Education Officer) Date __________ WEO Seal